# ኢፕድ አዲስ ዘመን

ሐሙስ

84ኛ ዓመት ቁጥር 009 መስከረም 9 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## ብሔራዊ ትርክት - አሰባሳቢው ጥላ

ተስፋ ፈሩ

ሙአዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት "የትርክት ዕዳና በረከት" በሚል ርዕስ በቅርቡ ባሳተሙት መጽሐፋቸው፤ ትርክት ሁን ተብሎም ይሁን በተለምዶ በዓላማ የሚዘጋጅ ንግርት መሆኑን ገልጸዋል።

ሙዓዘ ጥበባት ዳንኤል እንደሚሉት፤ ትርክት ብዙ ጊዜ ታሪክን፣ እምነትን፣ ባህልን እና አመለካከትን የሚይዝ ሲሆን፤ የሚነገርበት ምክንያትም አለው። የሚዘጋጀውም ለዚያ ምክንያት ሲባል ነው። የሚካተቱት ከተዘጋጀበት ዓላማ ጋር የሚሄዱ ሃሳቦችና ታሪኮች ናቸው።

ብዙ ጊዜ የትርክቶች በጎነትና እኩይነት በትርክት ቀራፂዎቹ እጅና ፍቃድ ወይም ቁጥጥር ስር ሊወድቅ እንደሚችል የሚያመላክቱት ፀሐፊው፤ በበጎ ዓላማ ከተዘጋጁ በአንድ ሀገር ሕዝቦች መካከል መግባባትና አንድነት እንደሚፈጥሩ ሁሉ፣ በዕኩይ ዓላማ ከተዘጋጁ ደግሞ መቃቃር በመፍጠር የግጭት አዙሪት ውስጥ ያስገባሉ ነው የሚሉት።

ለአንድ ወገን ዓላማ የተቀረፀ፣ ልዩነትን እና ብዝሃነትን ያልተቀበለ፤ ማቀራረብና ማግባባት ዓላማው ያልሆነ ኅብረ ብሔራዊነትን የማይፈጥር ትርክት፣ ባለፉት ዘመናት ኢትዮጵያን ብዙ ፈትኗታል። ብዙ ዋጋም አስከፍሏታል ሲሉም ያክላሉ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድም (ዶ/ር) በተለያዩ መድረኮች ስለ ኢትዮጵያ ታላቅ ትርክት መገንባት እንደሚገባና የጋራ ገዥ ወይም ታላቅ ትርክት መገለጫው ሚዛናዊነት፣ ህብረ ብሔራዊ አንድነት፣ ፍትሐዊ የሕዝብ ተጠቃሚነት እንዲሁም አብሮነት መሆኑን ሲናገሩ ይደመጣል።

ኢትዮጵያን በህብረ ብሔራዊነት ወደ ከፍታ ለማሻገር ከራስ ባለፈ ለሌሎች ማሰብ፣ በጋራ ትናንት እና በጋራ ነገ


ብሔራዊ ትርክት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ከአሰባሳቢ ትርክቶች መካከል አንዱ የዓድዋ ድል ነው፤








ፎቶ ዳኜ አበራ

አቶ መንሱር ደሴ

### ኢትዮጵያ በአፍሪካ የአካባቢ ሚኒስትሮች ልዩ ጉባኤ የመሪነት ሚናዋን ተወጣለች


ገጽ 2





## ዲጂታላይዜሽን የዘመኑ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሽ ሞተር

ሳሙኤል ወንደሰን

ዜና ትንታኔ

ኢትዮጵያ በሳይንስና ቴክኖሎጂው እንዲሁም በዲጂታል ኢኮኖሚው ተጨባጭ ለውጥ ለማስመዝገብ በማለም መንገድ ጠራጊ በሆኑት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ልዩ ልዩ መመሪያዎች ላይ በትኩረት እየሠራች መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ።

በተለይ በዘርፉ ልዩ ክህሎት ያላቸው ወጣቶችንና ታዳጊዎችን ለማብቃት የሚያስችሉ የልህቀት ማእከላትም


ዲጂታሳይዜሽን የዘመኑ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## በትምህርት ዘመኑ የተሻለ ውጤት የማስመዝገብ ውጥን

አማን ረሺድ

ዜና ሀተታ

ተማሪዎች የተሻለና ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት በማግኘት በትምህርታቸው ስኬታማና ውጤታማ እንዲሆኑ የእያንዳንዱ መምህርና የትምህርት ዘርፉ አስተዳደር የማይተካ ድርሻ አለው፡፡ ለትምህርት ውጤት መረጋገጥ የመምህራን፣ የተማሪዎችና የትምህርት ሥራ ባለሙያዎች ሚና ከፍተኛ መሆኑ ይገለጻል፡፡ የዛሬ ተማሪዎች የነገ ሀገር ተረካቢና ገንቢ ዜጎች እንዲሆኑ በዘርፉ የሚገኙ ተዋንያን ለአዲሱ የትምህርት ዘመን የተለያዩ ዝግጅቶችን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

መምህራንን የማጣቀሻ መጽሐፍትን ማዘጋጀት፣ ተማሪዎች እውቀትና ችሎታቸው እንዲጎለብት ትኩረታቸውን ንባብ ላይ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ በ2017 የትምህርት ዘመን የተሻለ ውጤት እንዲመዘገብ ትምህርት ቤቶች፣ መምህራን እና ተማሪዎች ዝግጅት ምን እንደሆነ አስተያየታቸውን ሰጥተውናል፡፡

በ2017 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ተማሪዎች የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ የዝግጅት ሥራ መሥራታቸውን


በትምህርት ዘመኑ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory



Tel:- 0940 505050 – 0940 606060 – 0940 909090 – 0940 808080 -0920 656565



አቶ መንግስቱ ቀኘ

## ተቋሙ 875 የአስተዳደራዊ በደል መዝገቦች ላይ ውሳኔ አሰጥቷል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በ875 የመልካም አስተዳደር በደል ጥያቄ መዝገቦች ላይ ውሳኔ ማሰጠቱን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የሕግና አስተዳደር በደል ምርመራ መሪ ሥራ አስፈጻሚ መንግስቱ ቀኘ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ተቋሙ በ2016 በጀት ዓመት ከመረመራቸው አንድ ሺህ 081 የመልካም አስተዳደር ቅሬታዎች ውስጥ 875 መዝገቦች ውሳኔ እንዲሰጣቸው አድርጓል።

በ2016 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የይዞታ መብት ጥያቄን፣ ከሥራ ያለአግባብ መባረርን፣ የጡረታ መብት አለማክበርን በተመለከቱና ከተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ጋር የተያያዙ አንድ ሺህ 081 የመልካም አስተዳደር ቅሬታዎችን በመመርመር 875 መዝገቦች ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ የማድረግ ሥራ አከናውኗል ብለዋል።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት 3 ሺህ 720 አቤቱታቸውን ተቀብሎ ለመመርመር ታቅዶ በተሠራ ሥራም አንድ ሺህ 972 ቅሬታዎችን መቀበል ተችሏል፤ ከተስተናገዱ አንድ ሺህ 972 ውስጥ 781 ጥቆማዎች ተቋሙ ከተሰጠው ስልጣን ውጪ በመሆናቸው አስፈላጊው የሕግ ምክር በመስጠት መሸኘታቸውን ተናግረዋል።

356 የሚሆኑት አቤቱታዎች ደግሞ ደረጃቸውን ጠብቀው የቀረቡ አይደሉም ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ 835 ጥቆማዎች ደረጃቸውን የጠበቁና በተቋሙ ስልጣን ስር የሚታዩ በመሆናቸው ምርመራ ተደርጎባቸዋል ሲሉ አብራርተዋል።

ምርመራ ከተደረገባቸው 835 ጥቆማዎች በተጨማሪ ከ2015 በጀት ዓመት በዞሩ 246 መዝገቦች በጥቅሉ አንድ ሺህ 081 መዝገቦችን በማጣራት 875 ቅሬታዎች ላይ ውሳኔ አሰጥቷል፤ቀሪ 206 መዝገቦች ወደ 2017 በጀት ዓመት መዞራቸውን አብራርተዋል።

44 ሺህ 912 ሰዎች በአንድ ሺህ 972 ቅሬታዎች ውስጥ መካተታቸውንም አውስተው፤ከሥራ ያለ አግባብ መባረር 634፣ከጡረታ አለመከበር 75፣ ከይዞታ አለመከበር 513፣ አገልግሎት አለማግኘት 375፣ የካሳ ጥያቄ 10፣ትምህርት ዕድልን በተመለከተ 11፣የመረጃ ጥያቄ 10፣ ልዩ ልዩ ጉዳዮች 344 በአጠቃላይ አንድ ሺህ 972 ጥቆማዎች ወደ ተቋሙ መምጣታቸውን አስታውሰዋል።

ተቋሙ በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሠረት መንግሥት በአስፈጻሚ አካላት የሚፈፀሙ አስተዳደራዊ በደሎችን በሚደርሰው ጥቆማ መሠረት ምርመራ በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጡ የማድረግ ሥራ እየሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

በፍርድ ቤት የታዩና ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን፣ከሀገር ማስከበር፣ ከፀጥታና ከደህንነት፣ ከሃይማኖት ተቋማት፣ከኦዲት ሥራ ጋር በተያያዙ አስተዳደራዊ በደሎች እንዲሁም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔዎች በሰጠባቸው መዝገቦች ላይ ተቋሙ የማየት ስልጣን የለውም ብለዋል።

በመንግሥት ሥራ አስፈጻሚ አካላት የሚፈፀሙ አስተዳደራዊ በደሎች መታረማቸውን ቁጥጥርና ክትትል የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በ2017 በጀት ዓመት 3 ሺህ 800 አስተዳደራዊ ቅሬታዎችን በመቀበልና ተገቢውን ምርመራ ለመሥራትና ውሳኔ ለማሰጠት ታቅዷል ሲሉ ጠቁመዋል።

# ኢትዮጵያ በአፍሪካ የአካባቢ ሚኒስትሮች ልዩ ጉባኤ የመሪነት ሚናዋን ተወጥታለች

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በ10ኛው ልዩ የአፍሪካ የአካባቢ ሚኒስትሮች ልዩ ጉባኤ የመሪነት ሚናዋን መወጣቷን የፕላንና ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በሚኒስቴሩ የአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ ስምምነትና ስትራቴጂክ አጋርነት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ መንሱር ደሴ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ 10ኛው የአፍሪካ የአካባቢ ሚኒስትሮች ልዩ ጉባኤ እ.አ.አ. ከነሐሴ 30 እስከ መስከረም 6 ቀን 2024 በኮቲዲቯር፣ አቢጃን ተካሂዷል።

ኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት በሆነችበት ልዩ ጉባኤ የመሪነት ሚናዋን በአግባቡ መወጣቷን ገልጸው፤ በልዩ ጉባኤው የአቢጃን ዲክላሬሽን ማጽደቅን ጨምሮ ከአየር ንብረት ለውጥ፣ በረሃማነት ከመከላከልና ድርቅን ከመቋቋም ጋር የተያያዙ አራት ውሳኔዎች መተላለፋቸውን አስታውሰዋል።

የፕላንና ልማት ሚኒስትር ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር) ኢትዮጵያን ወክለው ጉባኤውን በፕሬዚዳንትነት መምራታቸውን አቶ መንሱር ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለውጥና በአካባቢ ጉዳዮች እያከናወነቻቸው ያሉ ተጨባጭ ተግባራትን በልዩ ጉባኤው ለተሳታፊዎች ማጋራቷን አንስተው፤ በርካታ ሀገራት የኢትዮጵያን ተግባር አድንቀው ከሀገራችን ጋር አብሮ በትብብር ለመሥራት ፍላጎታቸውን አሳይተዋል ብለዋል።

በጉባኤው የመሬት መራቆት፣ በረሃማነትንና ድርቅን



አቶ መንሱር ደሴ

ለመከላከል በትብብር መሥራት እንደሚገባ አጽንኦት እንደተሰጠው ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ልዩ ጉባኤው እንዲዘጋጅ ከተወሰነ ጊዜ አንስቶ የጉባኤው ሴክሬታሪያት ከሆነው የተባበሩት መንግሥታት የአካባቢ ፕሮግራም ጋር አስፈላጊውን መመሪያ በመስጠት የሰነድና የሎጂስቲክስ ዝግጅት ስታደርግ መቆየቷንም አስታውሰዋል።

ከዋናው ጉባኤ ጎን ለጎን ሌሎች የጎንዮሽ ምክክርና ውይይቶች መደረጋቸውን ጠቁመው፤ መድረኩ ኢትዮጵያ በሀገር አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ በአካባቢና በአየር ንብረት ለውጥ ጉልህ አስተዋጽኦ ያላትን መሪነት ያስጠበቀችበት እንደሆነም አስታውቀዋል።

በ10ኛው የአፍሪካ የአካባቢ ሚኒስትሮች ልዩ ጉባኤ የተደረሱ ውሳኔዎችን የወቅቱ የጉባኤው ፕሬዚዳንት በሆነችው ኢትዮጵያ በኩል ለአፍሪካ መሪዎች ለውሳኔ እንዲቀርብ መጠየቁንም አመላክተዋል።

የአፍሪካ የአካባቢ ሚኒስትሮች ጉባኤ፣ የአፍሪካ የተደራዳሪዎች ቡድን፣ የአፍሪካ የአየር ንብረት ለውጥ የመሪዎች ኮሚቴና የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ግንኙነትን ማጠናከር የሚያስችል ግልጽ የአስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት እንደሚያስፈልግ ውሳኔ መተላለፉንም አቶ መንሱር ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከ10ኛው የአፍሪካ የአካባቢ ሚኒስትሮች ልዩ ጉባኤ ጎን ለጎን የሁለትዮሽና ሌሎች የአጋርነት ማጠናከሪያ ውይይቶችን በማካሄድ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር የተያያዙ አጋርነቶችን ማጠናከሯን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በቀጣይነት የአፍሪካ የአካባቢ ሚኒስትሮች ጉባኤ ውሳኔዎችን ማስፈጸምና ጉባኤው ከሌሎች የአካባቢ ቡድኖች ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳልጥ ሥርዓት ለመዘርጋት እንደምትሠራ ገልጸዋል።

10ኛው የአፍሪካ የአካባቢ ሚኒስትሮች ልዩ ጉባኤ እ.አ.አ. ነሐሴ 24 እስከ ጳጉሜን 1 ቀን 2016 ዓ.ም በኮቲዲቯር፣ አቢጃን መካሄዱ ይታወሳል።

ኢትዮጵያ ከነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ ጉባኤውን እየመራች ሲሆን፤ ለሁለት ዓመታት የመሪነት ሚናዋ በ2017 ዓ.ም ያበቃል።

# በትግራይ ክልል የተከሰተውን የወባ በሽታ ለመግታት ኅብረተሰቡ ራሱን መከላከል ይጠበቅበታል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል የተከሰተውን የወባ በሽታ ለመግታት ኅብረተሰቡ ውሃ ያቆሩ ቦታዎችን በማፋሰስና አጎበር በመጠቀም ራሱን ከበሽታው መከላከል ይጠበቅበታል ሲል የክልሉ ጤና ቢሮ አስታወቀ።በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች የተከሰተውን የወባ በሽታ ለመከላከልም ትኩረት እንደሚያስፈልገው ተጠቁሟል።

በቢሮው የበሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ቡድን መሪ አቶ አረጋይ ገብረመድህን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ 70 በመቶ የክልሉ ማህበረሰብ የወባ በሽታ ተፅእኖ ውስጥ ይገኛል። ይህን ችግር ለመቅረፍ በአካባቢው የሚገኝ ውሃ ያቆረ ቦታ የትንኝ መራቢያ እንዳይሆን እያፀዳ ራሱን ከበሽታው መከላከል አለበት። በተጨማሪም ኅብረተሰቡ የወባ በሽታ ምልክት ሲታይበት በፍጥነት ወደ ጤና ተቋም በመሄድ ህክምና ማግኘት ይኖርበታል።

አስተባባሪው እንዳሉት፤ የወባ በሽታ በሁሉም የክልሉ ወረዳዎች እየተስፋፋ ይገኛል። በተለይ በአስር ወረዳዎች ተምቤን ቀይሕ ተኸሊ፣ ደቡብ ራያ ጨርጨር፣ ሰሜን ምዕራብ አስገደ፣ አድያቦ፣ዓዴት እና ሌሎች አካባቢዎች እየተስፋፋ ነው።

በጦርነቱ ምክንያት በክልሉ የሚገኙ የተጎዱት የጤና ተቋማት በሚፈለገው ደረጃ ማስተካከል ባለመቻሉ ፣በቂ መድኃኒት ባለመኖሩ እና በባለሙያ እጥረት በሽታው ከባድ ደረጃ ላይ እንዲደርስ አድርጎታል ብለዋል። በተጨማሪም የመከላከያ አጎበርና የሚረጭ የወባ መከላከያ ኬሚካል አለመኖሩን ጠቅሰዋል።

ኅብረተሰቡ በሽታውን መከላከል እንዲችል ቀደም ሲል አጎበር የነበራቸው በአግባቡ እንዲጠቀሙ ተናግረዋል። ከቤት ውጪ ሲያመሹ የወባ ትንኝ ልትነድፋቸው ስለ ምትችል በጊዜ እንዲገቡ እና በተለይ እናቶች እና ሕፃናት በተገኘው ጨርቅ ሙሉ ሰውነታቸውን ተሸፍነው እንዲተኙ መክረዋል።

በመሆኑም ኅብረተሰቡ በጤና ዙሪያ መረጃ የሚያስተላልፉ ሚዲያዎችን በንቃት እንዲከታተል እና በአካባቢው የሚገኝ ውሃ ያቆረ ቦታ የትንኝ መራቢያ እንዳይሆን እያፀዳ ራሱን ከበሽታው እንዲከላከል



አሳስበዋል። በተጨማሪም ኅብረተሰቡ የወባ በሽታ ምልክት ሲታይበት በፍጥነት ወደ ጤና ተቋም በመሄድ ህክምና እንዲያገኝ አስረድተዋል።

በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች የተከሰተውን የወባ በሽታ ዘለቄታዊ መፍትሄ እንዲኖረው በመንግሥት እና በግብረ ሰናይ ድርጅቶች ልዩ ትኩረት ያስፈልገዋል ያሉት አስተባባሪው፤ በሽታውን ለመግታት የሚያስፈልጉ ግብአቶች አጎበር፣የሚረጭ ኬሚካል እንዲሁም በቂ ባለሙያ እና የጤና ተቋም ለማሟላት እገዛ እንዲደረግ ጥሪ አቅርበዋል።

# በአማራ ክልል ከሁለት ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ ሁሉን አቀፍ መንገድ ሊገነባ ነው

## -15 ሺህ ኪሎ ሜትር መንገድ ለመጠገን ታቅዷል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በ2017 በጀት ዓመት ከሁለት ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ የጠጠር፣የአስፓልትና ድልድዮችን ያካተተ ሁሉን አቀፍ መንገድ ለመገንባት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን የክልሉ መንገድ ቢሮ አስታወቀ፡፡ በበጀት ዓመቱም 15 ሺህ ኪሎ ሜትር ጉዳት የደረሰበትን መንገድ ለመጠገን መታቀዱ ተጠቁሟል፡፡

የአማራ ክልል የመንገድ ቢሮ ኃላፊ ጋሻው አወቀ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤በአማራ ክልል የገጠሩንና የከተሜውን ማህበረሰብ በማገናኘት የገበያ ትስስር ለመፍጠር፤ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቁርኝትን ለማሳደግ የሚያስችል የመንገድ መሠረተ ልማት ለመገንባት እየተሠራ ነው፡፡ በዚህም በ2017 በጀት ዓመት ሁለት ሺህ 200 ኪሎ ሜትር  የጠጠር፣አስፓልትና ድልድዮችን ያካተተ ሁሉን አቀፍ መንገድ ለመገንባት ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡

በክልሉ በ2016 በጀት ዓመት የገጠሩን ማህበረሰብ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ፤ ከተሜውን ከገጠሩ ማህበረሰብ ለማስተሳሰር የሚያስችል አንድ ሺህ 97 ኪሎ ሜትር የጠጠር መንገድ ለመሥራት ታቅዶ በተደረገ ክንውን 705 ኪሎ ሜትር  የመንገድ ጥገናና 265 ኪሎ ሜትር መንገድ የመገንባት ሥራ ተሠርቷል ያሉት ኃላፊው፤



ጋሻው አወቀ (ዶ/ር)

የጥገናና የግንባታ ሥራው የተሠራው ከማህበረሰቡ በተዋጣ 931 ሚሊዮን ብር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም የክልሉን የመንገድ መሠረተ ልማት በማሳደግ ማህበረሰቡን በኢኮኖሚ፣በማህበራዊ ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ባለው ሥራ  139 ኪሎ ሜትር መንገድ በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የመገንባት ሥራ ተከናውኗል ያሉት ጋሻው (ዶ/ር)፤ የዜጎችን የመሸጋገሪያ ድልድይ ችግር ለመፍታት 92 ድልድይ ለመሥራት ታቅዶ በተሠራ ሥራ 74 ድልድዮችን በማጠናቀቅ ለአገልግሎት ክፍት ተደርገዋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በአማራ ክልል በተያዘው በጀት ዓመት ሁለት ሺህ 200 ኪሎ ሜትር ሁሉን አቀፍ መንገድ በመገንባትና 15 ሺህ ኪሎ ሜትር በመጠገን የገጠሩን ማህበረሰብ ከከተሜው የማገናኘት ሥራ ይሠራል፤ ይህም የክልሉን የንግድ የትስስር አድማስ ያሰፋል፤ ማህበራዊ ቁርኝትም ያሳድግል ብለዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ የታቀደውን ሁለት ሺህ 200 ኪሎ ሜትር ሁሉን አቀፍ መንገድ ግንባታና  15 ሺህ ኪሎ ሜትር መንገድ ጥገና እውን ለማድረግ አንድ ነጥብ 5 ቢሊዮን ከማህበረሰቡ ለመሰብሰብ እንደታቀደ ገልጸው፤ የክልሉ መንግሥትም እቅዱን ውጤታማ ለማድረግ አንድ ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር መበጀቱን አብራርተዋል፡፡

የክልሉ ማህበረሰብ የመንገድ መሠረተ ልማትን በማስፋፋት ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማምጣት በንቃት እየተሳተፈ መሆኑን ገልጸው፤ የክልሉ መንግሥትም የማህበረሰቡን የመንገድ የልማት ጥያቄ ለመመለስ ጠንካራ ሥራ እየሠራ ነው፤ይህም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል፡፡




ፎቶ ገበበ ገብሬ

# የኢሬቻበዓልን ከማክበር ባለፈ የገበያ ትስስር የሚፈጠርበት እንዲሆን እየተሠራ ነው

## - በአዲስ አበባ “ኢሬቻ ኤክስፖ 2017” የተሰኘ አውደ ርዕይ ይካሄዳል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የኢሬቻ  በዓልን ከማክበር ባለፈ የገበያ ትስስር የሚፈጠርበት እንዲሆን እየተሠራ ነው ሲል የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡

ቢሮው በትናንትናው እለት ለመገናኛ ብዙኃን በሰጠው መግለጫ፤ በአይነቱ ለየት ያለ “ኢሬቻ ኤክስፖ 2017” የተሰኘ ታላቅ ዓመታዊ ዓውደ ርዕይ ከመስከረም 18 ቀን እስከ መስከረም 24 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል  እንደሚካሄድ  ገልጿል፡፡

የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ደራራ ቱለማ  በወቅቱ በሰጡት መግለጫ፤  ኢሬቻ የክረምት ወቅት አልፎ አዲስ ዓመት ሲጀመር የሚከበር ታላቅ የምስጋና በዓል ነው።

ቢሮው የኦሮሞን ባህልና ታሪክ አጉልቶ ለማሳየት ከተለያዩ አካላት ጋር እየሠራ መሆኑን ገልጸው፤ የኦሮሞ ሕዝብ መገለጫ የሆነውን የኢሬቻ በዓል ከማክበር ባለፈ የገበያ ትስስር የሚፈጠርበትና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው የጎላ እንዲሆን እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በዚህም  ቢሮው ከመስከረም 18 እስከ 24 ቀን 2017 ዓ.ም የሚቆይ “ኢሬቻ ኤክስፖ 2017” የተሰኘ አውደ ርዕይ ከሀገሬ ኢቨንትስ ኤንድ ፕሮሞሽን ጋር በመሆን ማዘጋጀቱን ገልጸዋል።

አቶ ደራራ፤ “ኢሬቻ ኤክስፖ 2017” የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚያሳትፍ፣ እንዲሁም ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ታዳሚ የሚሆኑበት በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነ እና በሚቀጥሉት ዓመታት ግን በቋሚነት የሚዘጋጅ ዓመታዊ ሁነት መሆኑን አንስተው፤ ኤክስፖው ወሳኝ ኢኮኖሚያዊ እድሎችን የሚፈጥር ደማቅና ሰፊ ዝግጅት መሆኑን ጠቁመዋል።

በዘንድሮ ኢሬቻ በዓል ከ10 ሚሊዮን ሰዎች በላይ እንደሚሳተፉ ይጠበቃል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

የሀገሬ ኢቨንትስ ኤንድ ፕሮሞሽን ኃላፊ ሃወኒ እሸቱ በበኩላቸው፤ ኤክስፖው ኢሬቻ ከበዓል በተጨማሪ በኢኮኖሚ ላይ ያለውን አስተዋጽኦ የሚያሳይ መሆኑን ገልጸዋል።

በኤክስፖው ከባህላዊ ኤግዚቢሽኖች እና ትርኢቶች እስከ የእደ ጥበብ ወርክሾፖች፣ የአገልግሎትና ምርቶች ባዛር እና የማህበረሰብ ተሳትፎ ክፍለ ጊዜዎችን ጨምሮ በርካታ  ተግባራት የሚቀርቡበት  ነው ያሉት ኃላፊዋ፤ የንግድ፣ የባህል አልባሳትና ጌጣጌጥ፣ የእጅ ሥራዎች፣ የባህላዊ ምግቦች፣ የሙዚቃ ኮንሰርት፣ የፓናል ውይይትና ሌሎችም ዝግጅቶች እንደተካተቱበት ጠቅሰዋል።

በኤክስፖው ከ200 ሺህ በላይ የማህበረሰብ ክፍሎች እንደሚሳተፉበትና ከ250 በላይ የንግድ ድርጅቶች ምርትና አገልግሎታቸውን  ያቀርቡበታል ተብሎ እንደሚጠበቅ ጠቁመዋል።

# የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ብዙ ሳይፈጥን በጣም ሳይዘገይ ተግባራዊ ይደረጋል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ትግበራው ብዙም ዘግይቶ የሕዝብን አመኔታ እንዳያጣ በጣም ፈጥኖ ተገቢ ውይይት ሳይደረግበት ወደ ትግበራ እንዲገባ አይደረግም ሲል ፍትሕ ሚኒስቴር ገለጸ።

የፍትሕ ሚኒስቴር እና የሽግግር ፍትሕ የባለሙያዎች ቡድን  በትግበራው ዙሪያ ከጋዜጠኞች ጋር ውይይት አካሂደዋል።

በፍትሕ ሚኒስቴር የሰብአዊ መብት የድርጊት መርሀ ግብር ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አወል ሱልጣን፤ ትግበራው ብዙም ዘግይቶ የሕዝብን አመኔታ እንዳያጣ፤ በጣም ፈጥኖ ተገቢ ውይይት ሳይደረግም ወደ ትግበራ እንዲገባ አይደረግም ብለዋል።

ትግበራው ሕዝባዊ ገጽታ እንዲላበስ፣ ገለልተኛ፣ ግልጽ፣ አሳታፊ እና አካታች እንዲሆን ሁሉም ሊተባበር እንደሚገባ ገልጸው፤ ሀገርን የማዳን፣ ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት ችግርና ጨለማ ማሸጋገሪያ ድልድይ እንደመሆኑ ሀገር ወዳድ ሁሉ ለትግበራው ትኩረት ሊሰጥ  መተባበር እንደሚገባም አቶ አወል አሳስበዋል።

ኅብረተሰቡ በባለቤትነት ሊሳተፍ፣ መገናኛ ብዙኃንም አሳማኝ እና ተጨባጭ መረጃ በማቅረብ ለትግበራው ስኬታማነት ትብብር ሊያደርጉ እንደሚገባቸውም አመልክተዋል።

በቀጣይ 25 የሚደርሱ ሀገር አቀፍ ውይይቶች እንደሚካሄዱ እና እስከ አምስት ወራት ድረስ ለትግበራው አስፈላጊ ሕጎች ለምክር ቤቱ እንደሚቀርቡም ነው የገለጹት።

በቀጣይ አራት የፍትሕ ተቋማት እንደሚቋቋሙ፣ ምርመራና ክሱ በአዲስ ተቋም እንዲመራ በመወሰኑ ልዩ የዐቃቤ ሕግ ተቋም እንደሚቋቋም፣  ክሱ በልዩ ችሎት እንዲታይ እንደሚደረግም ተጠቁሟል።

አምስት የሚሆኑ አዳዲስ ሕጎች ይወጣሉ። የሕጎቹን መጽደቅ ተከትሎም አስፈላጊ ተቋማቱ እንዲቋቋሙ ይደረጋል ብለዋል።

የሽግግር ፍትሕ የባለሙያዎች ቡድን አባል አቶ ሲሳይ አስፋው በበኩላቸው፤ ትግበራው ያለጣልቃ ገብነት እየተካሄደ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

የሽግግር ፍትሕ ተግባራዊ ለማድረግ አምስት ዋና ዋና ምክንያቶች መኖራቸውንና ሀገራዊ አውድ በተለይም ባለመረጋጋት ውስጥ፣ በእርስ በእርስ ግጭቶች የተፈጸሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች አሉ። ለእነዚህ ዜጎች ማካካሻ በመስጠት መፍትሄ ማበጀት ስለሚያስፈልግ ነው ብለዋል።

የቀጠሉ የትጥቅ ትግሎችን መፍትሄ ለመስጠት ስለሚያስችል ተግባራዊ ማድረጉ አስፈላጊ መሆኑ እንደታመነበትም ጠቁመዋል።

በሂደቱ ተጠያቂነትን ለማስፈን ከመደበኛ ከፍትሕ ሥርዓቱ ይልቅ በሽግግር ፍትሕ መፍትሄ በመስጠት ወደፊት ለመሻገር ያስችላል። ለፖሊሲ ቀረጻው 80 የሚደርሱ የምክክር መድረኮች መካሄዳቸውንም ተናግረዋል።

ሀገራዊ ግንባታን ለማረጋገጥ፣ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን የሚረዳ መሆኑን በመታመኑ መሆኑን ጠቁመው፤ ትግበራው ለሰብአዊ መብቶች መከበር እና ለሕግ የበላይነት መከበር  ወሳኝ መሆኑ እንደታመነበትም ነው የተናገሩት።

በተጨማሪም የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽንና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጸሙ የጦር ወንጀሎች፣ ሰዎችን ማፈናቀል፣ አስገድዶ መድፈር፣ በሰው መብት ላይ የሚፈጸሙና ጉልህ የሆኑ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ላይ ሁሉን አካታች የሕግ ተጠያቂነት እንዲሰፍን ያቀረቡትን መሠረት ማድረጉን ተናግረዋል።

የፕሪቶሪያው ስምምነትም የሽግግር ፍትሕ ተግባራዊ በማድረግ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን ማመልከቱንም ጠቁመዋል።

በርካታ ሀገራት ሂደቱን በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ እንዲተገበር ወስነው ተግባራዊ ማድረጋቸውን በመጠቆምም፤ ኢትዮጵያም ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በፖሊሲ እንዲተገበር ወስና እንቅስቃሴ መጀመሯን ተናግረዋል።

ጉልህ በሆኑ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ላይ ያተኩራል ያሉት አቶ ሲሳይ፤ የወንጀል ተጠያቂነት እንዲሰፍን ይደረጋል። ለሁሉም ጥሰትና ግጭት ምክንያት የነበሩ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የመብት ጥሰቶችን ሽፋን እንዲያገኙ በማድረግ እውነት የማፈላለግ ተግባራዊ እንደሚሆንም ነው ያነሱት።

በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የወንጀል ተሳትፏቸው ጉልህ ያልሆኑ ሰዎች በተጠና መልኩ፣ በሕግ በተቀመጠ አሰራር የምህረት ተጠቃሚ የሚሆኑበት አሰራር የሚዘረጋ መሆኑንም ነው የገለጹት።

ለተጎጂዎች ማካካሻ እንደሁኔታው ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሥርዓት ፖሊሲው ማመልከቱንና ሕገ መንግሥቱ ከጸደቀበት ከ1987 ዓ.ም አንስቶ የተፈጸሙትን እንዲያካትት ውሳኔ ላይ መደረሱንም ነው የገለጹት።

ዜና

# በትምህርት ዘመኑ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የደጅ አዝማች በላይ ዘለቀ 2ኛ ደረጃና የብሔራዊ ቤተ መንግሥት አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ገልጸዋል።

የደጅ አዝማች በላይ ዘለቀ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አዲስዓለም ታዬ እንዳሉት፤ በ2017 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ተማሪዎች የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ከወላጆች፣ ከመምህራንና ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመወያየት የዝግጅት ሥራዎች ተከናውነዋል።

በትምህርት ቤቱ በባለፈው የትምህርት ዘመን 94 በመቶ የሚሆኑ ተማሪዎች የክፍል ውጤታቸው ከግማሽ በላይ መሆኑን ገልጸው፤ በ2017 የትምህርት ዘመን ውጤቱን በማሻሻል 97 በመቶ የሚሆኑ ተማሪዎችን ለማሳለፍና ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ታቅዷል ይላሉ።

የመማር ማስተማር ሥራዎችን የሚያሳልጡ የተማሪዎች የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም)ና የትምህርት ቁሳቁሶችን የማሟላት ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቁመው፤ የተማሪ ወላጆች በትምህርት ቤት ሁለንተናዊ ልማት ሥራዎች ላይ በመሳተፍ እቅዱ እንዲሳካ መሥራት እንደሚገባቸውም ይገልጻሉ።

ከትምህርት ባለፈ ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ሥነምግባር የተላበሱ ዜጎች እንዲሆኑ እየሠራ እንደሚገኝ ርዕሰ መምህር አዲስዓለም ይናገራሉ። ትምህርት ቤቱ በባለፈው የትምህርት ዘመን የነበሩ ክፍተቶችን በማረም ጠንካራ ጎኖችን በማስቀጠል የተሻለ ውጤት እንዲመዘገብ እንደሚሠራ ያስረዳሉ። የተወሰኑ የትምህርት ግብዓቶች እጥረት መኖሩን ገልጸው፤ ለማሟላት ከትምህርት ቢሮ ጋር እየተሠራ ይገኛል ነው ያሉት።

የብሔራዊ ቤተ መንግሥት አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር መንግሥቱ ታደለ በበኩላቸው፤ ትምህርት ቤቱ በትምህርት ዘመኑ ከተማ አቀፍ ፈተና የሚወስዱ የ6ኛ እና የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ እንዲችሉ በልዩ ትኩረት እየሠራ ይገኛል ይላሉ።

ለመማር ማስተማር ሥራው የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ቀደም ብለው ለተማሪዎች እንዲደርሱ ተደርገዋል ያሉት ርዕሰ መምህር መንግስቱ፤ በቀጣይ ተማሪዎች የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ የማጠናከሪያ ትምህርት ለመስጠት ታቅዷል ።ለዕቅዱ ስኬታማነትም የትምህርት ጥራትን የሚያረጋግጥ ውጤት እንዲመዘገብ የትምህርት ቤት አስተዳደር፣ መምህራን፣ ተማሪዎች እንዲሁም ወላጆች ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባም ያስገነዝባሉ።

መምህር ደረጀ አባቡና መምህርት ኩሪ ለገሠ የትምህርት ቤቶቹ መምህራን ሲሆኑ፤ ተማሪዎች በዓመቱ መጨረሻ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ትምህርታቸውን በርትተው ማጥናትና በጥሩ ሥነ ምግባር መከታተል እንደሚገባቸው ይገልጻሉ። በተጨማሪም በመምህራኖቻቸው የሚሰጡትን እውቀቶች ወደ ውጤት ለመቀየር ወላጆች ልጆቻቸውን መደገፍና ማበረታታት ይገባቸዋል ነው ያሉት።

የትምህርት ቤቶቹ ተማሪዎች የሆኑት ተማሪ ቃልኪዳን ክብሩና ተማሪ ሀያት ዚያድ በበኩላቸው፤ በባለፈው ዓመት የተሻለ ውጤት በማስመዝገብ ወደ ቀጣይ የክፍል ደረጃ ማለፍ እንደቻሉ ገልጸው፤ በዚህ ዓመትም ጠንክረው ለመማርና የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ መዘጋጀታቸውን ነው የነገሩን። ሌሎች ተማሪዎችም በየትምህርት ቤቶች ከሚገኙ ጎበዝ ተማሪዎች የሚከተሉትን መንገድ በመከተል ውጤታማ እንዲሆኑ ከወዲሁ ተግተው ትምህርታቸውን ሊማሩ ይገባል ሲሉ ምክራቸውን ለግሰዋል።

# ዲጂታላይዜሽን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ወደ ሥራ ለማስገባት የሚሠሩ በርካታ መሬት ላይ የወረዱ ሥራዎች ይታያሉ። ይህንን የተግባር ሥራ በሚፈለገው ፍጥነትና የጥራት ደረጃ ለመሥራት ደግሞ መንግሥት የተለያዩ ስትራቴጂዎች በመንደፍ ሥራ ላይ አውሏል።

ከእነዚህ ውስጥ "ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ» አንዱ ነው። ይህን ተከትሎም በርካታ የመንግሥት አገልግሎቶች በኦንላይን እየተሰጡ ነው። በትሪሊዮኖች የሚቆጠር የገንዘብ ዝውውርና ግብይትም በኦንላይን በመከናወን ላይ ይገኛል።

ኢትዮ ቴሌኮም በ2016 በጀት ዓመት ብቻ በቴሌብር አማካኝነት ከአንድ ነጥብ ስምንት ትሪሊዮን ብር በላይ ዝውውር መደረጉን አስታውቋል፡፡ የቴሌብር ደንበኞች ቁጥርም 47 ነጥብ 55 ሚሊዮን መድረሱን የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሬህይወት ታምሩ ገልጸዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ የኩባንያውን የ2016 በጀት ዓመት አፈጻጸም ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ በሰጡበት ወቅት፤ ኢትዮ ቴሌኮም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ገቢራዊ በማድረግ ለዲጂታል ኢትዮጵያ ግንባታ የመሪነት ሚናውን እየተወጣ መሆኑን አብራርተዋል።

ለአብነትም የቴሌብር አገልግሎት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ሁለት ነጥብ 55 ትሪሊዮን ብር ግብይት መፈጸሙን አንስተው፤ አሁን ላይ የቴሌብር ተጠቃሚዎች ቁጥር 47 ነጥብ 5 ሚሊዮን መድረሱንና በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ብቻ አንድ ነጥብ ስምንት ትሪሊዮን ብር ግብይት መከናወኑን ነው ያስረዱት።

ቴሌ ብር ለዜጎች የሚሰጠውን አገልግሎት በማቀላጠፍ የዲጂታል ኢትዮጵያን ግንባታ እያገዘ መሆኑን ገልጸው፤ ኢትዮ ቴሌኮም የ2016 በጀት ዓመት እቅዱን በስኬት ማጠናቀቁን የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ 462 አዳዲስ የሞባይል ጣቢያዎች ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ነው የጠቆሙት።

በዚህም የዲጂታል ኢትዮጵያ ግንባታ እውን ማድረግ የሚያስችሉ ውጤቶች መገኘታቸውንና ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል ነው ያሉት። ኢትዮ ቴሌኮም 86 ሚሊዮን ደንበኞችን ማስተናገድ የሚያስችል የሞባይል ኔትወርክ አቅም መገንባቱን በመጠቆም የ4G አገልግሎት 34 ነጥብ ስድስት በመቶ ደርሷል።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በ124 ከተሞች የ4G አገልግሎት በመስጠት የ4G ተጠቃሚ ከተሞችን ቁጥር 424 ማድረስ መቻሉን ገልጸው፤ ከዚህም ባለፈ 132 የገጠር የሞባይል ጣቢያዎች ከ2G ወደ 3G አገልግሎት ማደጋቸውን ጠቅሰው፤ በአምስት ከተሞች የ5G አገልግሎት ማስፋፊያ መደረጉንና በሂደት ላይ ያሉ መኖራቸውን ያብራራሉ፡፡

በአጠቃላይ የሞባይል ኔትወርክ ተደራሽነት በቆዳ ስፋት 85 ነጥብ አራት በተጠቃሚዎች ደግሞ ከ99 በመቶ በላይ መድረሱን ጠቁመዋል፡፡ይህም ኢኮኖሚን ሆነ አገልግሎት አሰጣጡን ለማቀላጠፍ ከፍተኛ ሚና መጫወቱን እንደሚያሳይ ያመለክታሉ፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክም በበጀት ዓመቱ ከተከናወኑ የገንዘብ ዝውውሮች 72 በመቶ በዲጂታል የባንክ አማራጮች እንደተከናወነ ጠቁሟል። በዚህም ከአንድ ነጥብ 56 ቢሊዮን በላይ ግብይት ወይም ከ31 ነጥብ ስድስት ትሪሊዮን ብር በላይ የገንዘብ ዝውውር የተፈጸመ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ከአንድ ነጥብ 19 ቢሊዮን ወይም 72 በመቶ የሚሆነው ግብይት በዲጂታል የክፍያ አማራጮች የተከናወነ መሆኑን ከባንኩ የተገኘ መረጃ ያሳያል።

ባንኩ በ2016 በጀት ዓመት 135 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር አጠቃላይ ገቢ ማግኘቱን የገለጸ ሲሆን፤ ይህም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር በ13 በመቶ ዕድገት ማሳየቱን ገልጿል። በዚህ ዓመት ከታክስ በፊት 25 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ትርፍ ማግኘቱን የገለጸው ባንኩ፤ ይህም በባንኩ ታሪክ ከፍተኛው ሆኖ መመዝገቡን አስታውቋል።ይህም አሠራሩን ዲጂታላይዝድ በማድረጉ የተገኘ ውጤት እንደሆነ ይጠቅሳል፡፡

ኢትዮጵያ በቅርቡ ያደረገችውን የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያ ተከትሎ በዓለም አቀፍ ገበያዎች ውስጥ ትልቅ ድርሻ እንዲኖራት ይጠበቃል። ለዚህ ደግሞ የዲጂታል ኢኮኖሚ ማደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ።

የቴክኖሎጂ ባለሙያው አቶ ዳንኤል አድነው እንደተናገሩት፤ በሀገሪቱ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን እቅድ እድገትና ውጤት እየታየ ነው። ባለፉት ሦስት ዓመታት በሀገሪቱ ትልልቅ የዳታ ሴንተሮች እንዲገነቡ ተደርጓል። ይህም በቴክኖሎጂ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ወጣቶች ተጠቃሚ አድርጓል ነው ያሉት።

በዚህም የሀገር ውስጥ የኦንላይን ገበያ እየተስፋፋ መጥቷል። ይህም በዲጂታላይዜሽንና በቴክኖሎጂው ዘርፍ ከተገኙ ስኬቶች ውስጥ እንደሚጠቀስ ገልጸው፤ ዘርፉ ለበርካቶች የሥራ እድል እየፈጠረ መሆኑን በቀላሉ የገበያ ሥርዓቱን በመመልከት ማወቅ እንደሚቻል ያብራራሉ።

ይህም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከማሳደግ ባለፈ የሀገርን የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥና ለማስጠበቅ እድል እንደሚሰጥ ተናግረው፤ በተለይ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተጀመረው የአምስት ሚሊዮን ኮደርስ የኦንላይን ትምህርት ወደፊት የሀገሪቱን የሳይበር ደህንነት ለማስጠበቅ የሚኖረው ፋይዳ ትልቅ መሆኑን ነው ያመለከቱት።

ኢትዮጵያን ዲጂታል እናደርጋለን ሲባል በርካታ የፕሮግራም ወይም የኮዲንግ እው ቀት ያላቸው ሰዎች ያስፈልጋሉ ማለት ነው። ለዚህም አሁን ላይ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉ ከሆነ ወደፊት ከአሁኑ የተሻለ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የቴክኖሎጂና የዲጂታል ዘርፉ ላይ ዘግይታ የተቀላቀለች ቢሆንም ፈጣን የሆነ የትራንስፎርሜሽን ሥራ እየተከናወነ በመሆኑ ጊዜው እሩቅ እንደማይሆን ይጠቁማሉ።

# ብሔራዊ ትርክት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አጀንዳዎች መሰባሰብ እና አርበኛ መሆን እንደሚገባም ያነሳሉ።

ለመሆኑ ባለፉት ስድስት ዓመታት አሰባሳቢ ብሔራዊ ትርክትን ለማጠናከር ምን ተሰርቷል?

በአዲስ አበባ እና በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስተምሩት የፖለቲካ ተመራማሪው ሙሉጌታ ደበበ (ዶ/ር) ብሔራዊ ትርክት የአንድ ሀገር ሕዝብ በጋራ የሚኖረው እሴት፣ ግንዛቤ እና አስተሳሰብ ነው ይላሉ።

ዶክተር ሙሉጌታ እንደሚሉት፤ ብሔራዊ ትርክት ስንል ኢትዮጵያ ሳይሆን ኢትዮጵያዊነት ማለታችን ነው። ጥቃቅን ልዩነቶችን ትተን የጋራ በሆኑ ነገሮች ላይ ስንሰባሰብ የሚመጣ ጥላ ነው።

ኢትዮጵያ የውጭ ወራሪዎችን ከመመከት አንጻር በምሥራቅ አፍሪካ ስትጫወት የነበረው ሚና ቀላል አይደለም። በቀጥታና በጎረቤቶቿ አማካኝነት በውክልና የሚመጡባትን ሃይማኖታዊ እና ጎሳዊ ግጭቶችን የመፍጠር ሙከራዎችን ሁሉ ተቋቁማ የኖረች ታላቅ ሀገር ናት። ይሄ በራሱ ትልቅ ትርክት ነው። ኢትዮጵያ ታላቅ ሀገር ነበረች፤ አሁንም ታላቅ ናት ወደፊትም ደግሞ እጅግ ታላቅ ሀገር እናደርጋታለን የሚለው አመለካከት የጋራ ትርክታችን ነው።

እያንዳንዱ ሥርዓት የራሱ ትርክት እንዳለው የሚያነሱት የፖለቲካ ተመራማሪው፤ የኢህአዴግ እና የደርግ ሥርዓቶችም የየራሳቸው ትርክት ነበራቸው። በተለይም በዘመነ ኢህአዴግ የነበረው ትርክት አሁን ላለንበት ዘመን በከፍተኛ ደረጃ ደንቃራ ሆኗል። አመለካከት፣ እንደ ሕዝብ ጠቅላላ ከሥነ ምግባር እና ከወጣቱ የመማርና ሀገር ከመለወጥ አቅም አንጻር በጣም ብዙ ጣጣዎች መጥተዋል ነው የሚሉት።

ባለፉት ስድስት ዓመታት አጋር ብለን የምንፈርጀው ሕዝብ ሳይኖር ሁሉም ሕዝቦች የሚሳተፉበት፤ በጋራ የምናድግበት እና ወደ ብልጽግና የምናመራበት ሀገር ነው ያለን የሚል አመለካከት እየተገነባ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ ይሄ አመለካከት እስከሚሰርጽ ድረስ ፈተናው ቀላል እንደማይሆን ይገልጻሉ።

ከለውጡ ወዲህ አሰባሳቢ ብሔራዊ ትርክትን ለማጠናከር ብዙ እየተለፋ መሆኑን የሚናገሩት ዶክተር ሙሉጌታ፤ ብሔራዊ የሆነው ብልጽግና ፓርቲ መመስረቱ በራሱ አንድ ፋይዳ አለው ብለው እንደሚያስቡ ይናገራሉ።

አንዱ ብሔር በቁጥር ስላነሰ እና ስለበዛ ወይም ጉልበት ስላለውና ስለሌለው ልዩነት ሳይደረግበት ሁሉም እንደ አቅሙ የሀገሪቱ ባለቤት ሆኖ የሚሄድበት ሁኔታ ተፈጥሮ ፌዴራሊዝሙ በትክክል መሬት የሚይዝበት መንገድ መኖሩ ጥሩ ነው ሲሉም ያክላሉ።

ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀምሮ በየጊዜው በሚፈጠሩ የተለያዩ ሁነቶች ብሔራዊ ትርክት እና አንድነት እንዲጎላ እየተደረገ መሆኑን የሚያመላክቱት የፖለቲካ ተመራማሪው፤ ታላቁ ቤተመንግሥት አንድነት ፓርክ ተብሎ ተሰይሟል፤ እንዲሁም ፊት ለፊቱ የሚገኘው ትልቅ አረንጓዴ ስፍራ ወዳጅነት አደባባይ ተብሏል፤ በእነዚህ ሁሉ መንገዶች ብሔራዊ ትርክትን ማጉላትና የሰፈር ጉዳዮችን የማኮሰስ ሥራ እየተሠራ ነው። ውጤቱ በአጭር ጊዜ የሚታይ ባይሆንም አዝማሚያው ወደ ጥሩ አቅጣጫ እየሄድን እንደሆነ ያሳያል ብለዋል።

አያይዘውም፤ አንዱ ሌላው ላይ ተጽዕኖ ሳያደርግ ሁሉም የሚሳተፍበት የጋራ ሥርዓት ለመመስረት በሚደረገው ጥረት ችግሮቻችንን እየፈታን እየሄድን ነው ብዬ አስባለሁ። ሌሎች ሀገሮችም በተመሳሳይ መንገድ ብዙ ሃይማኖታዊ ችግሮችን፣ የኢኮኖሚ ልዩነቶችን፣ የእውቀት መራራቅን እና ብሔር ተኮር ፈተናዎችን አልፈው ነው መደማመጥና ማደግ ደረጃ ላይ የደረሱት። እኛም ወደዛ የምንገባ ነን ብዬ አምናለሁ ይላሉ።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ቋሚ ተጠሪ ተስፋዬ በልጂጌ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ህብረብሄራዊ ሆኖ ሁሉንም ማንነቶች ይዞ ጠንካራ ሀገር ለመገንባት የሚያስችለው ብሔራዊ ትርክት ነው። ብሔራዊነት ላይ በጋራ መሥራት አለብን የሚል አቅጣጫ ይዘን ነው የለውጡን ጉዞ የመራነው ይላሉ።

በአንድ በኩል ህብረብሔራዊነትን ወይም ብዝሃነትን የማይቀበል እሳቤ የተሸከመ ትርክት የሚያራምዱ አሉ። ይህ ትርክት ከኢትዮጵያ ባህሪ ያፈነገጠ ነው። ኢትዮጵያውያን የተለያየ ቋንቋ፣ ባህል፣ ወግና ማንነት ይዘን ኢትዮጵያ የምትባል ትልቅ ሀገር በአፍሪካ ቀንድ ፈጥረናል።

በሌላ በኩል በብዝሃነታችን ምክንያት እምብዛም አንድ የሚያደርገን ነገር የለም፤ ከአንድነት ይልቅ የየራሳችን ነጠላ ውጤት ይበልጣል ብለው የሚያስቡ ወገኖች አሉ። ይህ ትርክት ኢትዮጵያውያን በዘመናት ሂደት የገነቡትን እና ያጎለበቱትን የጋራ ሀገራዊ እሴት ስለሚንድ ከፋፋይና ነጣጣይ ነው፤ ለሀገር ግንባታ የማይጠቅምና የሚያሳንሰን ነው ብለዋል።

የለውጡ መንግሥት አቋም ሁለቱም ጽንፍ የያዙ የግራና ቀኝ አመለካከቶች ለኢትዮጵያ እንደማይጠቅሙ በመረዳት የሚጠቅመን ህብረብሔራዊነትን የሚቀበል፣ ኢትዮጵያዊ አንድነታችንንም ይዞ የሚነሳ በንዑስ ማንነቶችና በሀገራዊ አንድነት መካከል ሚዛን ሆኖ ጠንካራ ሀገር መገንባት የሚያስችል አካሄድ መከተሉን ገልጸዋል።

"ጠቅላይ ሚኒስትሩ በጻፉት የመደመር መጽሐፍም ብሔራዊነትን የሚመለከት ሃሳብ ተካቷል። እኛ እንደ ብልፅግና ፓርቲ ስንመሰርትም አንዱ ማዕከላችን ብሔራዊነት ነበር። የመንግሥት ፖሊሲዎችና የዕቅድ አቅጣጫዎችም የተቃኙት በዚሁ መንገድ ነው" የሚሉት የመንግሥት ተጠሪው፤ በብልፅግና ፓርቲ ውስጥ ከላይኛው አመራር ጀምሮ እስከ ታች አባላት ድረስ እሳቤው ዋነኛ የንቅናቄ ማዕከል እንዲሆን ተደርጓል። በተጨማሪም ሕዝባዊ መሆን ባሉባቸው ጉዳዮች ላይ ለሕዝቡ ቀርቦ ውይይት ሲካሄድበት ከርሟል። በመገናኛ ብዙኃንም ጠንካራ ሀገራዊ ትርክት እንዲኖር ለማድረግ ብዙ ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል ነው የሚሉት።

በሌላ በኩል የከረረሙ ችግሮችን ለመፍታት ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን እንዲቋቋምና ወደ ሥራ እንዲገባ መደረጉን የሚጠቁሙት ዶክተር ተስፋዬ፤ ኮሚሽኑ ከትርክት እና ከታሪክ ጋር የሚያያዙ አለመግባባት እንዲፈጠር ምክንያት የሆኑና ኋላቀር ከሆነው የፖለቲካ ባህላችን ጋር የሚያያዙ፣ በየጊዜው ሀገራችንን ለትርምስ፣ ለግጭት እና ለጦርነት እየዳረጉ የመጡ ጉዳዮችን ቁጭ ብለን በመነጋገር እንድንፈታ የሚያደርግ መሆኑን ይገልጻሉ።

ካለፉት ጊዜያት ጋር የሚያያዙ ቁርሾዎች የሚፈቱበት የሽግግር ፖሊሲ ተቀርፆ ወደ ሥራ እየተገባ እንደሚገኝም የሚያመላክቱት የመንግሥት ተጠሪው፤ የተዛባውን ትርክት ለማስተካከል ባለፉት ስድስት ዓመታት የተጀመሩት ተከታታይ ሥራዎች የሚፈለገውን ውጤት እንዲያስገኙ ኢትዮጵያውያን በጋራ መቆም አለብን ብለዋል።

ለሁላችንም የምትሆን ሀገር ለመገንባት የተስተካከለ ትርክት መያዝ እንደሚያስፈልግ ማመን አለብን። ምክንያቱም አጀንዳው ከአንድ የፖለቲካ ቡድን ወይም በአንድ ወቅት ከሚኖር መንግሥት ጋር የሚያያዝ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው ሲሉም አሳስበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሚኒስቴሩ ተግባር በፈተና የወደቁ ተማሪዎችን በመቶኛ ከመግለጽ የዘለለ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል!

ትምህርት ከፊደል ቆጠራ በዘለለ፣ በአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ለውጥ እና ዕድገት ውስጥ ዜጎችን ከፍ ያለ ድርሻ እንዲኖራቸው የሚያስችላቸውን የእውቀት፣ የክህሎት፣ የሥነምግባርና የአመለካከት ከፍታን የሚያጎናጽፍ መሳሪያ ነው፡፡ ኢትዮጵያም እንደ ሀገር በዚሁ አውድ ውስጥ ለመራመድ የሚያስችሏት ዜጎች ባለቤት ለመሆን ባላት መሻት ምክንያት፤ ዘመናዊ ትምህርትን ተግባራዊ ማድረግ ከጀመረች ለአንድ ምዕተ ዓመት የተጠጋ ታሪክ አላት፡፡

ይሄ ሂደት ደግሞ በብዙ ስኬቶችም፣ በብዙ ፈተናዎችም የታጀበ ነበር፡፡ በተለይም አንዴ በትምህርት ተደራሽነት፣ ሌላ ጊዜ በትምህርት ጥራት ችግር ምክንያት በሚፈለገው ልክ ተተግብሮ፤ የሚፈለገውን ያህል ሀገርን በሁሉም መስክ የሚያራምድ ትውልድን በሙላት መፍጠር አስችሏል ብሎ አፍ ሞልቶ የሚያናግር አይደለም፡፡

ለምሳሌ፣ በንጉሳውያኑ ዘመን በነበረው አካሄድ፣ የትምህርት ጥራት አለው ሊባል ቢችልም፤ ከትምህርት ተደራሽነት አኳያ ግን በእጅጉ ውስንነት ያለው ስለነበር፤ ዜጎች ውስጥ ያለውን አቅም በትምህርት አዳብሮ የሚፈለገውን ከፍታ ማምጣት አስችሏል ለማለት አያስችልም፡፡ ምክንያቱም፣ ለትምህርት ቅርብ የነበሩት ያሳዩትን አቅም፤ በብዙ እጥፍ ትምህርት ያልደረሳቸው ዜጎች መግለጥ የሚችሉበት ሰፊ እድል ይኖር ነበርና፡፡

በደርግ ዘመን የነበረው አካሄድም በአንድ በኩል የትምህርት ጥራትን፤ በሌላ በኩል ተደራሽነትን ለማስፈን የተሞከረበት ነበር፡፡ ሆኖም በሁለቱም በኩል ያለው ጉዞ በሚፈለገው ልክ ያልደረሰ፤ በብዙ ፈተናዎች መካከል እንዲራመድ የተገደደ ስለነበር፤ የታሰበውን ያህል ውጤት አምጥቷል ለማለት አያስደፍርም፡፡

ይሁን እንጂ በእነዚህ ሁለት ሥርዓቶች የነበረው ውስንነት እንዳለ ሆኖ፤ በትምህርት አውድ ውስጥ ያለፉ ዜጎች ከትምህርት ማግኘት የሚገባቸውን ነገር በልኩ ተገንዝቦ ወደተግባር በመለወጥ ረገድ እምብዛም እንከን ነበረባቸው የሚያስብሉ አይደሉም፡፡

ከዚህ መንገድ በተቃራኒው ግን በዘመነ ኢህአዴግ የነበረው የትምህርት ጉዞ፤ ከትምህርት ጥራት ይልቅ ለትምህርት ተደራሽነት ትኩረት በመስጠቱ፤ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ትምህርት ቤቶችንና በርካታ ዩኒቨርሲቲዎችን መገንባት ቢቻልም፤ በዚህ ልክ የሚገለጽ የበቃ የሰው ኃይል ከማፍራት አኳያ የበዛ ችግር ያለበት ሆነ፡፡ ይልቁንም ትምህርት ፊደል መቁጠሪያ (እሱም ያልተሳካለት)፣ ተማሪ የመባያ የምስክር ወረቀት መቀበያ ሆኖ ተከሰተ፡፡

ይሄ ሲሆን ደግሞ ተማሪ የተባለው ኃይል የሚፈለገውን እውቀት ሳይጨብጥ በኩረጃ ላይ ተመስርቶ ከፍተኛ ትምህርት የሚደርስበት፤ ከከፍተኛ ትምህርትም ቢሆን የሚፈለገውን ክህሎት ሳይጨብጥ ተመርቆ በሥራ መስክ ላይ በመሠማራት ውጤታማ ተግባርን መከወን የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሶም ታየ፡፡ ይሄ ደግሞ እንደ ሀገርም፣ እንደ ማኅበረሰብም ከፍ ያለ ውድቀትን የጋበዘ ሆነ፡፡

ይሄን ችግር በመገንዘብም ከ2010 ሀገራዊ ለውጥ ማግስት የፖሊሲ ለውጥ በማድረግ ጭምር የትምህርት ተደራሽነትን ከጥራት ጋር ለማስተሳሰር የሚያስችል አሠራር ተዘረጋ፡፡ ትውልዱ በእውቀትም፣ በክህሎትም፣ በአመለካከትና ሥነምግባርም ብቁ ሆኖ እንዲወጣ የሚያስችል የትምህርት ፍኖተ ካርታም ተግባራዊ ተደረገ፡፡ የፈተና ሥርዓቱ ላይ ያለውን ክፍተት ከመድፈን አኳያም በተለይ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሰጥ ተደረገ፡፡ ይሄ መደረጉ ደግሞ በትምህርት ሥርዓቱ ላይ ያለውን ከፍ ያለ ስብራት አግጥጦ እንዲወጣ አደረገው፡፡

በዚህ መልኩ ከሦስት ዓመታት በላይ የተጓዘው የትምህርት ዘርፉን ስብራት ለይቶ የማከም ጉዞ ግን፤ ዛሬም ላይ ይሄ ነው የሚባል ለውጥ ሳይታይበት በየዓመቱ ፈተና ያላለፉ ተማሪዎች ቁጥር በመቶኛ እያሰሉ በማቅረብ የታጀበ አካሄድ ላይ ተቸክሎ ቆሟል፡፡ ምክንያቱም ዛሬም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከተፈታኝ ተማሪዎች 97 በመቶዎቹ አላለፉም ከሚለው የመጀመሪያ መግለጫው፤ ዘንድሮ ከተፈታኝ ተማሪዎች 94 ነጥብ ስድስት በመቶዎቹ አላለፉም የሚል መጠነኛ የቁጥር ማሻሻያ ላይ ደርሶ ከመገለጥ የዘለለ የሚጨበጥ ርምጃ አልታየበትም፡፡

ይሄ ደግሞ ፖሊሲ ለውጡና አዲስ የትምህርት ፍኖተ ካርታም ቀርጾ ላለፉት ሦስትና አራት ዓመታት እየተገበረ እንዳለም ሆነ፤ የትምህርት ጥራትና ተደራሽነትን አጣምሮ በዘርፉ ውጤት ማሳየት ሥራው እንደሆነ አንድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ቆም ብሎ ራሱን እንዲፈትሽ፤ እየተመዘገበ ባለው ውጤትም ተማሪዎችን ተጠያቂ ሊያደርግ ሳይሆን የራሱን የሥራ ውጤት ሊገመግምበት የሚገባው ነው፡፡

ምክንያቱም፣ የትምህርት ውድቀትም ሆነ ውጤት የመጀመሪያው ጉዳይም፣ ሥራም የትምህርት ሚኒስቴር ነውና፡፡ ሆኖም ዛሬ ላይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በትምህርቱ ዘርፍ የተፈጠረው ስብራት የሚያስደነግጠው ሳይሆን፤ በስብራቱ ምክንያት በተፈጠረ ችግር በየዓመቱ ከተፈታኝ ተማሪዎች መካከል ከ94 በመቶ የሚልቁት ፈተና ማለፍ አለመቻላቸውን፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ትምህርት ቤቶች ምንም ተማሪዎች አለማሳለፋቸውን፤ እና መሰል ጉድለቶችን ከመናገር በላይ የማስተካከሉ ኃላፊነት በትምህርት ሚኒስቴር ጫንቃ ላይ የወደቀ ኃላፊነት ነው፡፡

በመሆኑም፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ፣ ከእስከዛሬው ጉዞው ትምህርት ወስዶ፤ በቀጣይ መሰል ሪፖርት ሕዝብ ፊት ይዞ ላለመቅረብ የሚያስችለውን የቤት ሥራ ከወዲሁ ወስዶ መሥራት ይኖርበታል፡፡ ለዚህ ደግሞ ተማሪዎችን ማሳለፍ ያቃታቸው ሺህዎቹ ትምህርት ቤቶችን ችግር ቀርቦ መረዳትና መፍታት፤ ከመምህራን፣ ከተማሪዎች፣ ከወላጆችና ሌሎችም ለውጤቱ መነሳትም ሆነ መውደቅ ድርሻ ካላቸው አካላት ጋር ተቀራርቦ መሥራት ይኖርበታል፡፡ ጥቂትም ቢሆኑ የተጀማመሩ መልካም ሥራዎችን ማስፋትና አጠናክሮ ማስቀጠልም ይጠበቅበታል፡፡

ምክንያቱም፣ የበርካታ ተማሪዎች መውደቅ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን ጨምሮ የዘርፉ ተዋንያን ውድቀት መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ይሄ ደግሞ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተማሪዎችን በፈተና የመውደቅ ዜና ከመግለጽ የተሻገረ ከፍ ያለ የቤት ሥራ እንዳለበት የሚያመላክት ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የበለጠ ትኩረት ለትምህርት ሥርዓቱ ስብራት!

**አዶኒስ (ከሲኤምሲ)**

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ውጤት ሲገለጽ "መርዶ" ሆኖ የሚከርመው የተማሪዎች ውጤት ጉዳይ ነው ።ችግሩ ለምን በየዓመቱ አነጋጋሪ ይሆናል ? ውጤት ሲወጣ ብቻ ለምን ችግሩን ጮክ ብለን እንነጋገርበታለን።

ከችግሩ ስፋት እና ጥልቀት ፣ እያስከተለ ካለው እና ሊያስከትም ከሚችለው ሀገራዊ አደጋ አኳያ ፣ ችግሩ ፖለቲካዊ ፣ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ፈተናዎችን ይዞ መምጣቱ ተገማች ነው። ከዚህ የተነሳም ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ማፈላለጉ ለነገ የሚባል የቤት ሥራ አይደለም።

የተማሪዎች ውጤት ማጣት ውድቀቱ የዛ ወይም የዛች ተማሪ ብቻ ነው እንዴ? አይደለም !። እንደ ሀገር ስናየው የወደቀው ሀገር ነው። እንደመምህር ስናየው የወደቀው ስንት ዓመት ሙሉ "ሲያስተምር የከረመው" መምህር ነው።

የወደቀው ስንት ዓመት ሙሉ መከራውን ሲያይ ፣ ከሌላው ገንዘብ ከፍሎ ልብስ አልብሶ ፣ ቀለብ ሰፍሮ፣ ጎንበስ ቀና ብሎ አሳድጎና አስተምሮ የልጁን ውጤት የሚጠብቀው ወላጅ ነው። የወደቀው ምንም ተማሪ ሳያሳልፍ የቀረው ትምህርት ቤት ነው። የወደቀው 12 ዓመት ሙሉ የደከመበት ልፋቱ በማይሆን ውጤት የደመደመው ተማሪ ነው።

የተማሪዎች መውደቅ ላይ ድርሻ የሌለው የለም ብል በድፍረት መናገር ይቻላል። ምክንያቱም በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ለተማሪዎች የትምህርት ላይ ቆይታ በርካታ አሻራቸውን ያኖሩና የሚያኖሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በርካታ ናቸው። ስለዚህ ውድቀቱ የሁሉም ነው። እናም አሁን ምን ይሁን ? ተማሪዎችን ወደ ውጤታማነት እንዴት እንመልስ በሚለው ዙሪያ ላይ ጊዜ ማጥፋት አያስፈልግም ?

አሁን ለተማሪዎች ውጤት በዚህ ልክ ማሽቆልቆል ምክንያት መደርደር ጊዜው አይደለም። ጊዜው እንዴት አድርገን የትምህርት ጥራትን እናስጠብቅ በሚለው ዙሪያ ላይ መምከር ነው። ሁሉም የድርሻውን መወጣት አለበት። ተማሪው ደብተር ይዞ ትምህርት ቤት ስለዋለ ብቻ ተምሯል ማለት አይደለም።

መማር ያለበትንና በትምህርት ደረጃው ማወቅ የሚገባውን እውቀት ጨብጧል ወይ የሚለውን መመለስ ያለበት ራሱ ተማሪው ነው። ከመምህሩ ያገኘውን እውቀት በሚገባው ልክ አጥንቶና ተረድቶ ገብቶታል ወይም ነገ ለሚቀመጥበት ፈተና ብቁ ዝግጅት እያደረገ ነወይ ብሎ ራሱን መጠየቅ ያለበት ተማሪው ነው።

ተማሪ የትኛውም ትምህርት ቤት ቢገባ የትኛውም አዋቂ የተባለ መምህር ቢያስተምረው የራሱ ቁራጥነትና ጥረት ካልታከለበት ውጤት ያመጣል ብሎ መጠበቅ ሞኝነት ነው። ለተማሪው ውጤታማ መሆን ደግሞ ተማሪው ብቻ ወሳኝ እንዳልሆነም መረዳት ያስፈልጋል።

ሥራውን በኃላፊነት ስሜት የሚሰራ መምህርነት ሥራ(ደመወዝ ማግኛ) ሳይሆን ሙያ ነው፤ ተማሪ መቅረጽ ነው ብሎ በእውነት ስለእውነት ለተማሪ ውጤት የሚሰራ መምህር ሊኖረን ይገባል። አሁን አሁን የሚታዩ አብዛኛው መምህራን ሙያውን የደመወዝ ማግኛ ብቻ ያደረጉ የሚመስሉ ናቸው፤ብዙም ሙያዊ ኃላፊነት ሲሰማቸው አይታዩም።

ሲመቻቸው ክፍል ይገባሉ፤ ገብተውም ተማሪ ይወቅ አይወቅ ፣ ትምህርቱን ይከታተል አይከታተል ጉዳያቸው ሳይመስላቸው የቆይታቸውን ክፍለ ጊዜ በዋዛ ፈዛዛ አሳልፈው ይወጣሉ። በማይመለከታቸው ፖለቲካ ውስጥ የሚዳክሩ አይጠፉም።

የተጠራቀመ ትምህርት በአንድና በሁለት ክፍለ ጊዜ አካክሰው ብታውቁ እወቁ የሚሉ ብዙዎች ናቸው። በዚህ ሁኔታ ያስተማረ መምህርና በዚህ ሁኔታ ሊማር ክፍል የተገኘ ተማሪ የምንጠብቀውን ውጤት ያመጣል ብሎ ማሰብ “ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ” እንደሚባለው ነው ።

መምህር የቀለም አባት ነው። በቀለምም በስነምግባርም ተማሪን ማረቅና ማሳወቅ ይጠበቅበታል። የሚቀርጸው ተማሪ የነገው ሀገር ተረካቢ መሆኑን መረዳት አለበት። መምህርነት ከደመወዝ በላይ መሆኑን አምኖ መስራት አለበት። ፈቅዶና ወዶ የተሰማራበት ሙያ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

በተማሪዎቹ ላይ የሚገለጸው ውጤት የእሱ የሥራ ውጤት መሆኑን መረዳት ይጠበቅበታል። ጥሩ ውጤት ሲመጣ የልፋቱና የጥረቱ ውጤት በመሆኑ መደሰት፤ የተማሪ ውድቀትም የእሱ አስተዋጽኦ መሆኑን መገንዘብ ይገባል። ውጤት ሲመጣ ማዘን ግን በራሱ ብቻውን ዋጋ የለውምና ለቀጣዩ ሥራ መጠንከር በቆራጥነት መንቀሳቀስ ነው ወሳኙ። ዛሬ ዓለም አንድ ሆኗል። ቴክኖሎጂው ፣ ቋንቋውም ሆነ ሌሎች ጉዳዮች ተወዳድሮ ማሸነፍን ይጠይቃል። ዘመኑ የውድድር ነው። ለዚህ ብቁ የሆነ ዜጋ ማፍራት የሚጠበቀው ከመምህሩ ነው።

አሁንም የተማሪዎች ውጤት መውረድ የተማሪው ፣ የመምህሩ ብቻ ነው ብሎ ማሰብ ስህተት ይሆናል። ምክንያቱም ተማሪው በሰዓቱ ወደ ትምህርት ቤት ሄዶና ተመልሶ ምን እየሰራ ነው? ትምህርት ቤት ሄዶስ ምን ተምሮ መጣ ? ብሎ መከታተልና መቆጣጠር ያለበት ወላጅ ነው።

አንዳንድ ወላጅ ልጁን ውድ ክፍያ የሚከፈልበት ትምህርት ቤት ስላስገባውና አስጠኚ ስለቀጠረለት ብቻ ልጁን ያስተማረ ይመስለዋል። ግን አይደለም ልጁ በወጪው ልክ እየተማረ ነወይ? በሚጠበቅበት ልክ እውቀት ጨብጧል ወይ? ብሎ ክትትል ማድረግ የወላጅ ግዴታ ነው።

ወላጅ ያልተከታተለውን ልጅ መምህር ብቻ ያበቃዋል ብሎ ማሰብ አይቻልም። ብዙ ገንዘብ ስላወጡ ብቻ ልጆቼን አስተምሬያለሁ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። በወራጅ ውሃ ላይ ገንዘብን እንደመነስነስ ይቆጠራል። ሌላው ቀርቶ ለተማሪዎች ውጤት ማሽቆልቆል የአካባቢ ማህበረሰብ ጭምር ተጠያቂነት አለበት።

ተማሪዎች ትምህርት ቤት ብለው ወጥተው በምን አይነት ቦታ በምን አይነት ስነምግባር ውስጥ እያሳለፉ ናቸው የሚለው መጠየቅ አለበት። ምንም አይነት ጉዳይ ከማህበረሰብ እይታ ውጪ ሊሆን አይችልም። ዩኒፎርም የለበሱ ልጆች በየመዝናኛ ፣ በየመጠጥ ቤቱ ፣በየፑል ቤቱ፣ በየሲኒማ ቤቱ ፣ በየስፖርት ውድድር ቤቶች... ይታያሉ።

ሕግ አስከባሪ የሚባለው አካል ጭምር አይቶ እንዳላየ ያልፋል። በእነዚህና በሌሎችም ተደራራቢ ምክንያቶች የተማሪዎች ውጤት ያሽቆለቁላል። ተማሪው ተማሪ መሆኑ ቀርቶ ከስነምግባር ያፈነገጠ ፣ ዋልጌ ይሆናል።

“ከ1300 በላይ ትምህርት ቤቶች ምንም ተማሪ አላሳለፉም” ሲባል ይሄ እንደ ጀግንነት ጆሮ ሰጥተን የምንሰማው ዜና መሆን የለበትም። በጣም አስደንጋጭ እንደ ሀገርም ቆም ብለን የትምህርት ፖሊሲያችንን፣ መምህራኖቻችንን፣ተማሪዎቻችንን ፣ ትምህርት ቤቶቻችንን አይናችንን ከፍተን እንድናይ የሚያስገድደን ይሆናል። ትልቅ ውሳኔንም ይጠይቃል።

ተማሪው እስካሁን ድረስ ክፍል ቆጥሮ እዚህ ደረጃ የደረሰው በኩረጃ ነበር ? በመምህራን ያልሰሩት ውጤት እየተሰጣቸው ነበር? ሌሎች ከክፍል ወደ ክፍል የማዛወሪያ መንገዶች ነበሩ ማለት ነው ብለን እንድንፈትሽ እንገደዳለን። አሁንም በዚህ ውስጥ ተማሪው፣ መምህሩ፣ ወላጅ፣ የትምህርት ቤቱ አስተዳደሮችና የትምህርት ፖሊሲው ሁሉ ይነሳሉ። ይብጠለጠላሉ።

በግለሰብ ደረጃ ድክመት ሊኖር ይችላል። በእዚህን ያህል ትምህርት ቤቶች የተፈተኑ ተማሪዎች በሙሉ ወድቀዋል ማለት ግን ከባድ ነገር ነው። በእኛ ሀገር አልተለመደም እንጂ ይህን ውጤት የሰማና ያየ የሥራ ኃላፊ ፣ መምህር፣ የትምህርት ማህበረሰብ ሥራውን መልቀቅ ነበረበት።

ዘርፉን በኃላፊነት የሚመራው የመንግሥት አካልም አስተማሪ እርምጃ መውሰድ፤ የተጠያቂነት ሥርዓት መፍጠር ይጠበቅበታል። ችግሩ የአንድ ወገን /የተማሪው ብቻ ተደርጎ መወሰድ የለበትም ። ለችግሩ ሁላችንም ባለድርሻ ነን። አሁን ከመወቃቀስ ወጥተን የትምህርት ሥርዓቱን ስብራት እንዴት እንጠግን፤ሀገር እና ትውልድን ከዚህ ችግር እንዴት እንታደግ ለሚለው ትኩረት ሰጥተን በጋራ ልንቀሳቀስ ይገባል።

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

# አሊባባ - የዓለም የችርቻሮ ንግድ ሥርዓትን የቀየረ

ወዲህ ሀገራችን የችርቻሮም ሆነ የጅምላ ንግድን ለውጭ ኩባንያዎች ክፍት ማድረጓን ተከትሎ የቻይናው ግዙፉ የችርቻሮ ኩባንያ የጃክ ማው አሊባባ እህት ኩባንያ አሊኤክስፐረስ ወደ ሀገራችን ሊገባ እንደሆነ እየተነገረ ይገኛል። አሊ ኤክስፕረስ ቻይናው አሊባባ የበይነ መረብ የሸቀጦች የጅምላ መገበያያ ኩባንያ በኢትዮጵያ ለመሠማራት ዝግጅት ላይ መኾኑን በዚያ ሰሞን አዲስ አበባ ላይ ባዘጋጀው የማብሰሪያ መድረክ ይፋ አድርጓል። በኢትዮጵያ ግብይት ለመጀመር ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር ከስምምነት ላይ የደረሰው፣ የአሊባባ ኩባንያ አካል የኾነው አሊ-ኤክስፐረስ የተሰኘው ኩባንያ ነው።

ኩባንያው በኢትዮጵያ ገበያ ውስጥ መሠማራቱ፣ ለሸማቾችና ነጋዴዎች በዓለም ገበያ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለመገበያየትና ኢትዮጵያን ይበልጥ ወደ ዓለም አቀፍ ንግድ ለማስገባት እንደሚያስችል የተመለከተ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ኩባንያው የበይነ መረብ መገበያያ አገልግሎት የሚሰጥበትን ማዕከል አዘጋጅቷል ተብሏል። ካለው ግዙፍ አቅምና ልምድ አንጻር በኢትዮጵያ የችርቻሮ ንግድ ላይ ማርሽ ቀያሪ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል። የሀገራችን ቸርቻሪዎችም አቅማቸውን አስተባብረው ለመፎካከር ሊዘጋጁ ይገባል።

በነገራችን ላይ መስኩ ለውጭ ኩባንያዎችና ዜጎች ክፍት ከሆነ ወራት ያለፉ ቢሆንም አሊ ኤክስፐረስ ወደ ሀገራችን ለመግባት የወሰነው የውጭ ምንዛሬ በገበያ እንዲወሰን ከተደረገ በኋላ ነው። ይህ የገንዘብ ፖሊሲው ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ያለውን ሚና ያሳያል። እኔም ከቻይና ጋር የሚኖረን ወቅታዊ የኢኮኖሚ ግንኙነትን ለመቃኘት ቢያግዝ በሚል አሁናዊ የቻይናን ኢኮኖሚ የሚገመግም ጽሑፍ ላጋራችሁ ወደድሁ።

ወዲያ የቻይና የፋብሪካና የኢንዱስትሪ ምርቶችና ውጤቶች በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ገበያ ፈላጊ አጥተዋል። ረክሰዋል። ኧረ እንዲያውም ጥንባቸውን ጥለዋል እየተባለ በስፋት እየተለፈፈ ነው። የሀገራችን አስመጭዎች ግን ዋጋ እየቆለሉ እጥፍ ስንጥቅ እያተረፉ ሸማች እየገፈፉ ባለበት አሊባባ ሲገባ ምን እንደሚውጣቸው አብረን የምናየው ሆኖ፤ ቻይና የዓለም ገበያ ከሚፈልገው በላይ አምርታ ገበያ አጥታ እንዲያውም አንዳንዶች እንደሚሉት መጣያ አጥታ ባለችበት ነውና አሊባባ የሚመጣው ይሄን መልካም አጋጣሚ ሳያሳልፍ ብሔራዊና የሸማቹን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ መዋዋል ይገባል።

እንደ "ፎሪን አፌርስ" መጽሔት በአንድ ጊዜ የሲአይኤ፣ የኋይታወስ፣ የፔንታገን ቤተኛ የሆነ መጽሔት የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። እንዲሁም ዓለም አቀፍ ግንኙነት የሚቃኝበት፤ ጂኦፖለቲካ የሚተነተንበት፤ የምዕራባውያን ትኩረት የሚመላከትበት ከመጽሔት የተሻገረ ስትራቴጂያዊ ሰነድ ነው። የቻይና ኢኮኖሚ መስቀለኛ መንገድ ላይ ነው። መጀመሪያ ይትበህሉ ፈረንሳይ ስታስነጥስ የተቀረው ዓለም ጉንፋን ይይዘዋል ነበር። ከዛ አሜሪካ ሳም ሲያስነጥስ አሜሪካ ለማለት ነው የተቀረው ዓለም ጉንፋን ይይዘዋል ነበር። አሁን ደግሞ ቻይና ጃፓንን ፈንቅላ ሁለተኛው የዓለማችን ባለ ግዙፍ ኢኮኖሚ መሆኗን ተከትሎ ይትበህሉ ተከትሏታል።

ቻይና ካለፉት አስርት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር ቀርፋፋ የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገበች ነው። በዓለም ላይ ካሉት ትላልቅ ኢኮኖሚዎች አንዷ ሆና ብትቀጥልም፣ ዓመታዊ የሀገር ውስጥ ምርቷ ቀንሷል። ትንበያዎች ቢለያዩም በአጠቃላይ ከ4 እስከ 5 በመቶ አካባቢ ሊቀንስ ይችላል እየተባለ ነው። ኢኮኖሚው ከኮቪድ-19 ተጽእኖዎች በማገገም ላይ ነው። እንደ አገልግሎት እና ማኑፋክቸሪንግ ያሉ ዘርፎች ቀስ በቀስ እያንሰራሩ ናቸው። ይሁን እንጂ በሌሎች ዘርፎች የወረርሽኙ አንኀር አለቀቃቸውም።

የቻይና ኢኮኖሚ ጉልህ አካል የሆነው የሪል ስቴት ሴክተር፣ በንብረት አልሚዎች ከመጠን ያለፈ ብድር ላይ የተወሰደ ባለ እርምጃ እና የቤት ዋጋ ማሽቆልቆሉን ጨምሮ በርካታ ተግዳሮቶች ገጥሟቸዋል። የሸማቾች መተማመን አሽቆልቁሏል። በዚህ የተነሳ ኢንቨስትመንት ተቀዛቅዟል። ቻይና የዓለም አቀፍ የማኑፋክቸሪንግ ማዕከል ሆና ቆይታለች። ነገር ግን ከአሜሪካ እና ከሌሎች ሀገራት ጋር ባለው የንግድ ውጥረት የተነሳ ፈተና ገጥሟታል። የጂኦፖለቲካ ጉዳዮች እና የአቅርቦት ሰንሰለት መስተጓጎል የወጪ ንግድ ዕድገት ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ ቀጥሏል።

በሰው ሠራሽ አስተውሎት AI፣ ሴሚኮንዳክተር ምርት እና አረንጓዴ ቴክኖሎጂዎችን ጨምሮ በቴክኖሎጂ ዘርፎች ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ላይ ትገኛለች።እነዚህ ኢንቨስትመንቶች ተወዳዳሪ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ እና ፈጠራን ለማጎልበት ወሳኝ ተደርገው ቢወሰዱም ከገበያ ፍላጎት በላይ እየተመረቱ መሆናቸው መጋዘን እያጣበቡ ነው። ሌላው የኩባንያዎችና የአካባቢ አስተዳደሮች ዕዳ ቁልል አሳሳቢ ሆኖ ቀጥሏል። ይህንን ዕዳ ለመቆጣጠር እና ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት የተሳካ አይመስልም። ኢኮኖሚያዊ መረጋጋት ተስኖታል።

ለዓመታት ትከተለው የነበረ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ የአረጋውያንና የጡረተኞች ምድር አድርጓታል። ይህ ደግሞ የአምራች ኃይል እጥረት እንዲገጥሟት አድርጓል። ይሄን ክፍተት ለመሙላት አገዛዙ የወሊድ መጠንን ለማበረታታት የተቀናጀ ርብርብ እያደረገ ቢሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤት የሚያመጣ አይመስልም ይላሉ ኢኮኖሚውን በቅርብ የሚከታተሉ ተንታኞች ሰሞኑን የአሜሪካው የውጭ ግንኙነቶች ምክር ቤት ተመራማሪ እና የ "Sovereign Funds: How the Communist Party of China Finances Its Global Ambitions." መጽሐፍ ደራሲ ዞንግዩዋን ዞኢ ሊኡ፤ የቻይና ኢኮኖሚ ቅርቃር ውስጥ ነው ይሉናል።

እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2022 መገባደጃ ላይ ቻይና ከኮቪድ ሙሉ በሙሉ ነፃ የመሆን ወይም "zero COVID" ፖሊሲዋን እርግፍ ማድረጓን ስታውጅ የቻይና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ያንሰራራል ብለው ገምተው ነበር። በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ሳቢያ ለዓመታት ጥርቅም ተደርጎ ከውስጥ ተዘግቶበት የነበረው የአለማችን ሁለተኛው ኢኮኖሚ ሲከፋፈት ፈጥኖ ይነቃቃል ተብሎ ተጠብቆ የነበር ቢሆንም እየሆነ ያለው ግን ከዚህ በተቃራኒው ነው።

ኢኮኖሚው ከማገገም ይልቅ በአለበት መርገጥና መንሸራተት ጀመረ። ኢኮኖሚውን ያስፈነጥራሉ ተብለው ተጠብቀው የነበሩት እንደ ሪል ስቴት ያሉ ዘርፎች ማሽቆልቆሉን ተያያዙት። ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት GDP ዕድገት መንቀራፈፍ፤ የሸማች የሸመታ ፍላጎት ማጣት፤ ከምዕራባውያን ጋር የገባችበት እሰጥ አገባ መባባስ፤ የሪልስቴት ዋጋ መርከስ ትላልቅ ኩባንያዎችን ለኪሳራ መዳረጉ የቻይናን ዕድገት አቀዛቅዞታል። ለበርካታ አስርት ዓመታት ባለ ሁለት አኃዝ ተከታታይ ዕድገት እንዳላስመዘገበች አሁን በአምስት በመቶ እንኳ ለማደግ ተቸግራለች።

ለተከታታይ ዓመታት የሪል እስቴት ኢኮኖሚው ከገባበት ቀውስ መውጣት አለመቻሉ፤ የአረጋውያንና የተጧሪ ሀገር መሆኗ፤ ኢኮኖሚዋ በፕሬዝዳንት ዢ ጅንፒንግ መዳፍ ስር መውደቁ እና በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ወቅት ኢኮኖሚዋን ሙሉ በሙሉ ጥርቅም አድርጋ መዝጋቷ ኢኮኖሚዋን አሽመድምዶታል ይለናል ፎሪን አፌርስ።

ሌላው ለዛሬው ኢኮኖሚያዊ ቀውስ የዳረጋት ትከተለው የነበረው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ከምንም በላይ ኢንዱስትሪው ላይ ያተኮረ መሆኑ ኢኮኖሚያዊ መዋቅሯን ከማጎበጡ ባሻገር እዳ በእዳ አድርጓታል ይሉናል ዞንግዩዋን ዞኢ ሊኡ።

በአጭሩ ይላሉ ጸሐፊው ቻይና የምታመርተው ገበያው ከሚፈልገው በላይ ነው። በዚህ የተነሳም ዋጋ ሲወረድ፣ እዳን መመለስ ፈተና ስለሚሆን ፋብሪካዎች መዘጋትና ሠራተኛ ወደ መበተን ይገባሉ። ይሄ ደግሞ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ መቀዛቀዝ ዳርጓል። ከ2010 ዓ.ም ወዲህ ርካሽ የቻይና የኢንዱስትሪ ውጤት የዓለም ገበያን በማጥለቅለቁ ለዓለም ሳይቀር ስጋት እየሆነ ነው ይሉናል ጸሐፊው።

በአብነትም ባለፈው ዓመት በወርሀ ታኅሣሥ የአውሮፓ ኮሚሽን ፕሬዚዳንት ኡርሱላ ቮን ደር ሌየን ርካሽ የሆነው የቻይና ምርት ቀጣይነት የሌለው የንግድ ጉድለት ከመፍጠሩ ባሻገር ገበያውን በማጥለቅለቁ ሌሎች ሀገራትን ከገበያ እያስወጣ ነው ሲሉ ይከሳሉ። የአሜሪካ የገንዘብ ሚኒስትር እነሱ የትሬዠሪ ሴክሬታሪ ይሏቸዋል ያኔት የለን ባለፈው ሚያዝያ እንዲሁ ቻይና ብረት፣ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪና ሌሎች ምርቶች ላይ ግዙፍ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰሷ ኢኮኖሚያዊ መፈናቀልን እያስከተለ ከመሆኑ ባሻገር ከገበያው የተትረፈረፈ ሸቀጥ እያቀረበች ነው ሲሉ አምርረው ይተቻሉ።

ቻይና ክሱን ደጋግማ ብታስተባብልም ሀቁ ግን ቻይና ዛሬም የዓለምን ገበያ እያጥለቀለቀች ነው። ለፖለቲካዊ አላማ ስትል ሸቀጦችን ከማምረቻ ዋጋቸው ባነሰ እየቸበቸበች ነው። ኮሚኒስት ፓርቲው ፋብሪካዎች ገበያው ከሚፈልገው በላይ እንዲያመርቱ ዛሬም ጫና ያደርጋል። ይህ በአጋጣሚ የተደረገ ሳይሆን የፓርቲው የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ ራዕዩ አካል ነው ይለናል ፎሪን አፌርስ መጽሔት።

አሜሪካን ጨምሮ ምዕራባውያን ኢኮኖሚያቸውን ከቻይና የርካሽ ሸቀጥ ማራገፊያነት ለመከላከል አዳዲስ የንግድ ገደቦችን እየጣሉ ነው። ከዚህም በላይ ቻይናን ከዓለም አቀፍ ገበያው ለመነጠል ተቀናጅተው እየሰሩ ነው። ሆኖም ይህ ውሳኔያቸው የገዛ ኢኮኖሚያቸውን ሊጎዳ ይችላል ይሉናል ጸሐፊው ዞንግዩዋን ዞኢ ሊኡ።

ጸሐፊው በነገራችን ላይ ብለው ሰነድ ያገላብጣሉ። በነገራችን ላይ የቻይና ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ችግር የሚጀምረው የቻይና ዕድገት አባት በመባል የሚታወቁት ዴንግ ዣውፒንግ የስድስት ጊዜ የአምስት የአምስት ዓመት የኢኮኖሚ ዕቅዶችን በ1981 ዓ.ም ይፋ ካደረጉ ወዲህ ይሉናል። ይህ ከ100 ገጾች በላይ የያዘ ዕቅድ ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ ስለ ቻይና ኢንዱስትሪ መስፋፋት፤ ስለ ዓለም አቀፍ ንግድን ማሳደግ፤ በቴክኖሎጂ ስለመዘመን ያወሳል እንጂ ስለ ዜጎች ገቢ መጨመርና ስለ ፍጆታ ግን በአንዲት አጭር አንቀጽ ነው የሚዘለው። የኢኮኖሚው ስብራት የሚጀምረው ከዚህ ነው ይለናል መጽሔቱ። በዓለማችን ቴክኖሎጂው እየዘመነና እየረቀቀ፤ ገበያው ከቀደመው ዘመን የተለወጠ ቢሆንም የቻይና የኢኮኖሚ ዕቅድ ግን ያው የተትረፈረፈ ምርት ማምረትና ገበያው ማጥለቅለቅና መቆጣጠር ላይ ያተኮረ ነው።

አሁን ሥራ ላይ ያለው 14ኛው የአምስት ዓመት ዕቅድ ወይም የ2021-2025 ኢኮኖሚያው ፕላን እንኳ ያው የተትረፈረፈ ምርት ላይና የውጭ ገበያ ላይ የተንጠለጠለ ነው ይሉናል ጸሐፊው። የሀገር ውስጥ ገበያውን የዘነጋና ትኩረት የነፈገ መሆኑ ለውጭ ገበያ ጥገኛ አድርጎታል። የውጭው ዓለም ደግሞ ቅድሚያ ለራሱ ኢንዱስትሪዎች ምርት መስጠት በመጀመሩ እንዲሁም በተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች ለቻይና ምርቶች ፍላጎት እየተቀዛቀዘ መምጣቱ ግዙፉ ኢኮኖሚ ለአደጋ ሊጋለጥ ችሏል።

የቻይና የብረት ምርት ከጀርመን፣ ከጃፓንና ከአሜሪካ አጠቃላይ ምርት ይበልጣል። እንዲሁም የድንጋይ ከሰል፣ የአልሙኒየም፣ የሮቦት ግብዓቶች፣ የኤሌክትሪክ መኪና ባትሪ ምርቷ ከእነዚሁ ሀገራት ይበልጣል። የዓለማችን ገበያ ከሚፈልገው የሶላር ፓናል ከእጥፍ በላይ አምርታለች። ገበያ ግን የላትም። ከ27 እስከ 32 በመቶ የቻይና መኪና አምራቾች ያለ ትርፍ ነው ሽያጭ የፈጸሙት። የምርት መትረፍረፍ ዋጋን እያረከሰው፤ የዋጋ ግሽበቱን ወደ ዜሮ እያወረደው፤ እዳ ጣራ እየነካ፤ የሸማቹ በራስ መተማመን እየቀነሰና ከሸመታ እየታቀበ ስለሆነ የሸቀጦች ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ እንዳይወርድ ወይም ዲኢንፍሌሽን እንዳይከሰት ያሰጋል ይሉናል ጸሐፊው ዞንግዩዋን ዞኢ ሊኡ።

ከገበያው ፍላጎት በላይ ማምረቷ የዋጋ ግሽበቱን ወደ ዜሮ ከማውረዱ ባሻገር፤ በተቃራኒው የዕዳ ክፍያ ምጣኔው ደግሞ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል። ይህ ክስተት ሸማቹ ከሸመታ እንዲቆጠብ ስለሚያደርግ አጠቃላይ ፍጆታ እንዲቀንስ በማስከተልም የሸቀጦች ዋጋ እንዲረክስ ያደርጋል።

የቻይና የበታች ሹማምንት በኮሚኒስት ፓርቲው ከፍተኛ አመራር ሞገስ የሚያገኙት የሚሸለሙትና የሚሾሙት በከተማቸው ወይም በክልላቸው የመንግሥትን የኢንዱስትሪ ፖሊሲ አቅጣጫ የተከተለ ኢንቨስትመንት በእነሱ የብድር ዋስትና ሲያስፋፉ እንጂ አዋጭ ኢንቨስትመንትን በማድረግ ስላልሆነ ከገበያውና ከሸማቹ ፍላጎት በላይ ምርት ሊከማች ችሏል። ባለፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች ደግሞ ለምርቶቻቸው ገበያ ባለማግኘታቸው እዳቸውን መክፈል አልቻሉም።

የአሜሪካው "ዘ ዎል ስትሬት ጆርናል" በሰራው የምርመራ ዘገባ የየአካባቢው አስተዳደሮች እዳ ከ7 እስከ 11 ትሪሊየን ዶላር ሲገመት ከዚህ ውስጥ 800 ቢሊየን ዶላሩ የተበላሸ ብድር ነው ይለናል። በነገራችን ላይ የአካባቢው አስተዳደሮች ዕድ የቻይና ጥቅል ሀገራዊ ምርት GDP ግማሽ ነው ማለት ይቻላል። የቻይና የአካባቢ አስተዳደሮች ከምዕራብ እስከ ምስራቅ ከዢንጂያንግ እስከ ሻንጋይ፤ ከሰሜን እስከ ደቡብ ሔሎንግጂያንግ እስከ ሀይናን የኮሚኒስት ፓርቲውን የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ለማስፈጸም እርስ በርስ ሲፎካከሩ ገበያውን በተመሳሳይ ምርት አጥለቅልቀውት አረፉ።

እንደ አብነት እናንስ ይላሉ የፎሪን አፌርስ ጸሐፊ ዞንግዩዋን ዞኢ ሊኡ፤ ቻይና በየዓመቱ ዓለማችን ከሚያስፈልገው የሶላር ፓናል በእጥፍ ታመርታለች። የቻይና መንግሥት ምክር ቤት 2010 ዓ.ም ላይ እስከ 2020 የጸሐይ ኃይል ወይም ሶላር ፓወር የGDP 15 በመቶ ድርሻ ሊኖረው እንደሚገባ መመሪያ አወረደ። በሁለት ዓመት ውስጥ ከሀገሪቱ 34 ግዛቶች 31ዱ የጸሐይ ኃይል ግብዓት ምርት መናኸሪያ ሆኑ። 100 የግብዓት ማምረቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ገነቡ። ወዲያው ምርቱ ከሀገር ውስጥ ገበያው ፍላጎት በላይ ሆነ። በመቀጠል የአውሮፓንና የአሜሪካን ገበያ ማጥለቅለቅ ጀመሩ። በ2013 ዓ.ም አሜሪካና አውሮፓ ከቻይና በሚገቡ የሶላር ፓናሎችና ሌሎች የጸሐይ ኃይል ማምረቻ ግብዓት ላይ ከፍተኛ ታሪፍ ጣሉ።

ቻይናስ ምን ሞኝ ነው። ይሄን ታሪፍ ለማምለጥ ምርቷን ወደ ካምፓዲያ፣ ማሌዥያ፣ ታይላንድ፣ ቬትናምና ሌሎች ሀገራት አዛወረች። በነሐሴ 2023 የአሜሪካ ኮሜርስ ይሄን የቻይና ሸፍጥ ደረሰበትና አስቆመው። የፎሪን አፌርስ ጸሐፊ ቀጥለዋል። ቻይና በ"2025 ዓ.ም Made in China" በሚለው ስትራቴጂዋ ከ2015 ዓ.ም ለበሮቦቲክስ ትኩረት መስጠት ጀመረች። ይሄ ስትራቴጂዋ እውን እስኪሆን ከጃፓን በላይ የዓለማችንን የሮቦቲክስ ኢንዱስትሪ ሸማች ነበረች።

**ሻሎም ! አሜን።**

# ወቅታዊ

# ‹‹የኢትዮጵያ እና ህንድ ግንኙነት ከ2000 ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ነው››

-ሚስተር አኒል ኩማር ራይ- በኢትዮጵያ የህንድ አምባሳደር እና የአፍሪካ ህብረት ቋሚ ተወካይ

**ኢትዮጵያ እና ህንድ ጥንታዊ የስልጣኔ ታሪክ ያላቸው ሀገራት ሲሆኑ ከሰባት አስርት ዓመታት በላይ የዘለቀ የረጅም ጊዜ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አላቸው። ግንኙነቱ ብዙ ዘርፎችን ማለትም ትምህርትን፣ ጤናን፣ ኢንዱስትሪን እና ንግድን ጨምሮ በጠንካራ መሠረት ላይ ያረፈ ሲሆን አሁን BRICS ሌላው አስፈላጊ የትብብር መድረክ ሆኗል።**

**የዛሬው ወቅታዊ እንግዳ በኢትዮጵያ የህንድ አምባሳደር እና የአፍሪካ ህብረት ቋሚ ተወካይ ሚስተር አኒል ኩማር ራይ ናቸው። የኢትዮጵያ ሄራልድ በሁለቱ ሀገራት መካከል ስላለው ግንኙነት ያላቸውን አስተያየት ለማግኘት ከአምባሳደር ራይ ጋር አጭር ቆይታ አድርጓል። መልካም ንባብ ይሁንላችሁ!**



**ጥያቄ፧- በህንድ እና በኢትዮጵያ መካከል ላለፉት ዓመታት ያለውን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዴት ያዩታል?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** ኢትዮጵያ እና ህንድ ከታዳጊው ዓለም በጣም ጠቃሚ ሀገራት ሲሆኑ ታሪካዊ ግንኙነታቸው ከ2000 ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ነው። ሁለቱም ሀገሮች በሁሉም ዘርፎች ልዩ የሆነ ሞቅ ያለ ግንኙነት አላቸው። እ.ኤ.አ. በየካቲት 2024 በኢትዮጵያ የሕንድ አምባሳደር ሆኜ ከተሾምኩበት ጊዜ ጀምሮ፣ በሁለቱም ሀገራት መሪዎች መካከል ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ሲደረግ ተመልክቻለሁ። እ.ኤ.አ. አገስት 17 ቀን 2024 ህንድ የታዳጊ ሀገራት መሪዎች በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ የጋራ ጥረቶችን ለማጠናከር ለታዳጊ ሀገሮች ተስማሚ የሆኑ መፍትሔዎች የተወያዩበት 'An Empowered Global South for a Sustainable Future' በሚል መሪ ሃሳብ ህንድ '3ኛውን የዓለም ደቡብ ስብሰባን አዘጋጅታለች። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አሊ (ዶ/ር) እና የፋይናንስ ሚኒስትር አህመድ ሺዴ ዶ/ር በመሪዎች ጉባኤ ላይ ተሳትፈዋል። በተጨማሪም በሁሉም ደረጃዎች የቅርብ ግንኙነት እንጠብቃለን፡፡ አሁን ብሪክስ በሁለትዮሽ፣ ክልላዊ እና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ለቀጣይ፣ የሃሳብ ልውውጥ፣ ትብብር እና ቅንጅት እንደ አዲስ መድረክ ሆኖ ብቅ ብሏል።

**ጥያቄ ፡- ኢትዮጵያ ብሪክስን መቀላቀሏ ለራሷ፣ ለሌሎች አባል ሀገራት እና አባል ላልሆኑት ጭምር ያለው ጠቀሜታ ምን ይመስሎታል?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** ብሪክስ ህንድ እና ደቡብ አፍሪካን ጨምሮ በ4 ሀገራት የተመሰረተ ድርጅት ነው። ህንድ መስራች አባል በመሆኗ የታዳጊ ሀገራትን ምኞት የበለጠ ውክልና እንዲገኝ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግም ኢትዮጵያ ህብረቱን ተቀላቅላለች። ኢትዮጵያ በብዙ መልኩ የአፍሪካን ምኞቶች እና ልማት ለማምጣት፣ ለማዘመን እና የሕዝቡን ፍላጎት ለመመለስ የሚያስችል መንገድ ትወክላለች። በዚህች ሀገር ወጣቶች እናምናለን፤ እየተካሄደ ያለው ሁሉን አቀፍ ማሻሻያ የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ገጽታ የመቀየር አቅም እንዳለው እያየን ነው። ብሪክስን በመቀላቀል ኢትዮጵያ የተለያዩ የብሪክስ ሀገራትን በተለያዩ ዘርፎች የተከተሉትን አማራጮችንና የዕድገት ሞዴሎችን ማግኘት ትችላለህ። ኢትዮጵያም ውክልና በማግኘቷ የራሷን እና የምስራቅ አፍሪካን ልማታዊ ፍላጎቶች እና ተስማሚ የሆኑትን ሞዴሎች ተጨባጭ ግምገማ ልታቀርብ ትችላለች።

**ጥያቄ፡- ብሪክስ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ እንዴት እየሄደ ነው? ለምሳሌ በቅርቡ የራሱ ዓለም አቀፍ የክፍያ ሥርዓት ጀምሯል።**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** የብሪክስ ዋና አላማ የእያንዳንዱን ሀገር ጥንካሬዎች በአግባቡ መጠቀም የሚችሉበት እና በማንኛውም ሥርዓት የማይታሰሩበት የኢኮኖሚ አስተዳደር ሥርዓት ሞዴል እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡ ይህም ከአቅማቸው በላይ ነው። የብሪክስ አባል ሀገራት በሀገር ውስጥ ምንዛሬ ለመገበያየት ወይም ወደ ምንዛሪ ልውውጥ ስምምነት ለመግባት እድል ይፈጥራል፡፡ በብሪክስ አባላት መካከልም የንግድ ልውውጥን ያመቻቻል እና የውጭ ምንዛሪ ጥገኝነትን ይቀንሳል፤ ይህም በምንዛሪ አያያዝ ላይ የተሻለ ቁጥጥር እንዲኖር ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ የግብይት ሥርዓቱን ጠንካራ ያደርገዋል። ይህ በሂደት ላይ ያለ ሥራ ነው፣ ወደፊትም ጥሩ እንደሚሆን ይሰማኛል እናም እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራት በቅርብ ጊዜ ብሪክስን ተቀላቅለው ከእንደዚህ ዓይነት ዝግጅቶች ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

**ጥያቄ፡- ኢትዮጵያ በተለይ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎን መሠረት በማድረግ ንግ ድና ኢንቨስትመንትን ቀላል ለማድረግ ርምጃዎችን እየወሰደች ነው፣ በዚህ ላይ ምን አስተያየት አልዎት?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ነፃነት በጣም ወቅታዊ እና ሁሉን አቀፍ ነው። ሀገሪቱ በክፍያ ሚዛኗ ላይ በተወሰነ ችግር ውስጥ እያለፈች የነበረች ሲሆን፥ በክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መሪነት ኢትዮጵያ ይህንን እንደ የሕይወት ዘመን እድል በመጠቀም የኢኮኖሚ መዋቅሩንና የአስተዳደር ሥርዓቱን ለማሻሻል ከፍ ያሉ አጀንዳዎችን እንደ ጀመረች አይቻለሁ። እንዲህ ዓይነቱ የተሃድሶ ሂደት ሰፊ ተፅዕኖ ያለው ሲሆን ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ተጫዋቾች አዳዲስ ዕድሎችን ይፈጥራል እናም ውድድሩ ሁሉም ሰው እንዲያድግ እና እንዲሻሻል የሚያበረታታ ይሆናል፡፡ እንደ ግብርና፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ ባንክ እና ፋይናንስ፣ ማዕድን፣ የአገልግሎት ዘርፍ ወዘተ. የውጭ ባለሀብቶችን የኢትዮጵያን ገበያ ማራኪነት ለማሳደግ እና የኢትዮጵያን ተወዳዳሪነት ለማሻሻል አቅም አላቸው። ህንድም በ1991 (እኤአ) ተመሳሳይ የተሃድሶ ሂደት ውስጥ አልፋለች፡፡ ዛሬም ቀጥሏል። ስለዚህ ነገሩ እየተንቀሳቀሰ ባለበት መንገድ ለኢትዮጵያ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እና ለሀገር ውስጥና ለውጭ ባለሀብቶች ጥሩ ይሆናል የሚል ተስፋ አለኝ።

**ጥያቄ፡-የህንድ ባለሀብቶች ከተሃድሶው ምን ያህል ተጠቃሚ ይሆናሉ?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** ህንድ በኢትዮጵያ ኢንቬስት በማድረግ ሁለተኛ ደረጃ ላይ የምትቀመጥ ስትሆን በብዛት የምንሰማራበት ዘርፍ ጨርቃጨርቅ፤ ብረትና ብረታ ብረት፣ ፋርማሲዩቲካልስ፤ ግብርና እና ልብስ ስፌት ናቸው፡፡ የህንድ ቢዝነስ ፎረም የኢንዱስትሪውን እይታ እና የማሻሻያ ሂደቱን ግብዓቶችን ለመስጠት ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በንቃት እየሰራ ነው። ከአዲሱ ሁኔታ ጋር ለመላመድ እና መረጋጋትን ለማግኘት ለፖሊሲ አውጪዎች ጊዜ እና ቦታ መስጠት እንዳለብን ይሰማኛል። እነዚህ ጉዳዮች ከተስተካከሉ በኋላ የፖሊሲ መረጋጋት ይመጣል።

በህንድ ውስጥ በጣም ብዙ ተቋማት ወይም የንግድ ድርጅቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ትልቁ ታታ ኢንተርናሽናል የግብርና፣ የማዕድን እና ሌሎች የተጠናቀቁ ምርቶችን በተለይም ኢትዮጵያ የዋጋ ተወዳዳሪነት ያላት ዘርፎችን ለመግዛት ይፈልጋሉ። የኢትዮጵያ ምርቶች ወደ ህንድ የሚላኩ ምርቶችን የበለጠ ለማስተዋወቅ «ከኢትዮጵያ ወደ ህንድ ሊላኩ የሚችሉ ምርቶችን» ለይተናል፡፡ የቅባት እህሎች፣ ጥራጥሬ፣ ጥጥ፣ ጀምስቶን እና ቡና በሚል ርዕስ ጥናት አድርገናል። ጥናቱ የኢትዮጵያን ምርቶች በህንድ ገበያዎች ወደ ውጭ የመላክ አቅምን ለማሳደግ የሚያስችል ስትራቴጂ አስቀምጧል።

**ጥያቄ፡- ኢትዮጵያ እና ህንድ በትም ህርት ዘርፍ የሚያደርጉት ትብብር ምን ደረጃ ላይ ደርሷል?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** የትምህርት ሴክተርን በተመለከተ በሁለቱ ሀገራት መካከል በጣም ጠንካራ እና ጥንታዊ ከሆኑ የትብብር መስኮች አንዱ ነው። እና በ1950ዎቹ ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ትምህርት በህንድ መምህራን ይመራ እንደነበር ይታወሳል። ኢትዮጵያውያን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ክህሎት አዳብረዋል፤ አሁን ደግሞ በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የህንድ ምሁራን ተሳትፎ የተገደበ መሆኑን ሳስተውል በጣም ደስ ብሎኛል። ለአጭር ጊዜ ስልጠና 500 እድሎች ለኢትዮጵያውያን እና ከ70 እስከ 80 በላይ እድሎች እንደ ቅድመ ምረቃ፣ ማስተርስ እና ፒኤችዲ ላሉ የረጅም ጊዜ ትምህርት ፕሮግራሞች እንሰጣለን። ትምህርት በሁለቱም ሀገራት መካከል ያለው የቆየ ግንኙነት እና አስፈላጊ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስር ሆኖ ቀጥሏል።

**ጥያቄ፡- ኢትዮጵያ ለአስርት አመታት የዘለቀውን የግጭት እና አለመግባባት ችግሮችን ለመፍታት ሀገራዊ ውይይት በማድረግ ሂደት ላይ ትገኛለች። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ከህንድ ምን ትማራለች?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** ኢትዮጵያ የሥልጣኔ ሀገር ነች፣ ኢትዮጵያውያን በታሪካቸው ይኮራሉ፣ ሀገር ወዳድ ናቸው። የተሻለው መፍትሔ የሚገኘው በኢትዮጵያ መሪነት እና በኢትዮጵያ የሚመራ የእርቅ ሂደት እንደሆነ እንገምታለን። የሀገር ውስጥ ጉዳዮችን በውይይት ገንቢ በሆነ መንገድ ለመፍታት ምንጊዜም ህንድ ደጋፊ ነች፡፡ እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች ወደተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ምክር ቤት በቀረቡባቸው አጋጣሚዎች የኢትዮጵያን አቋም ደግፈናል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ውይይት ሂደት ስኬታማ እንደሚሆን እንጠብቃለን።

**ጥያቄ፡- በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን የኢትዮጵያን ሚና እንዴት ያዩታል?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ቀንድ እና ለአፍሪካ አህጉር ቁልፍ የመረጋጋት ምሰሶ ነች። በቀይ ባህር አስፈላጊ የንግድ መስመር ላይ ስለሚገኝ እና በህንድ ውቅያኖስ በኩል ከህንድ ጋር የሚዋሰን በመሆኑ ሰላም እና መረጋጋት ለሁሉም ሰው ጠቃሚ ነው። ስለዚህ፣ የንግድ መስመሮቹ ክፍት፣ በሚገባ የተደራጁ፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና አስተማማኝ ሆነው እንዲቀጥሉ የሁሉም ሰው ፍላጎት ነው። ኢትዮጵያ፣ የአፍሪካ ህብረት እና የቀጠናው ሀገራት የአፍሪካ ቀንድ ሰላም ሆኖ እንዲቀጥል አስፈላጊ እና ባለድርሻ አካላት ናቸው።

**ጥያቄ፡- አፍሪካ በአጀንዳ 2063 የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና (AfCFTA) ዋና ፕሮጀክት ራሷን በኢኮኖሚ ለማዋሃድ እየጣረች ነው።**

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## ‹‹የኢትዮጵያ እና ህንድ...



ከገጽ 7 የዞረ

**ህንድ በቀጣናው የኢኮኖሚ ቡድን ትግበራ ከኢትዮጵያ እና ከአፍሪካ ጋር እንዴት ትተባበራለች?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** እ.ኤ.አ. በ2023 በህንድ የG20 ፕሬዚዳንትነት ታሪካዊ እና የቆየውን የተዛባ አካሄድ የሚያስተካክል ዲፕሎማሲያዊ ተነሳሽነት በህንድ የተወሰደ ሲሆን ይህም በጂ-20 የአፍሪካ ህብረት ቋሚ አባልነትን የሚያስገኝ ነው። ኢንዶኔዢያ፣ ሕንድ፣ ብራዚል እና ደቡብ አፍሪካ ለመሳሰሉት አራቱ ታዳጊ ሀገሮች የጂ-20 ፕሬዚዳንትነት መስጠቱ እንዲሁ ጥሩ አጋጣሚ ነው። የአፍሪካ ህብረት ይህንን እድል በመጠቀም የአፍሪካ አጀንዳ የ G20 አጀንዳ እንዲሆን እና የአጀንዳ 2063 የአፍሪካ ነፃ ንግድ ቀጠናን ጨምሮ ትክክለኛ የቦታ አቀማመጥ እንዲያገኝ ማረጋገጥ አለበት። ህንድ የG20 አባል ሆና የአፍሪካን ሁሉን አቀፍ ልማት በግብርና፣ በምግብ ዋስትና ጤና፣ በድህነት ቅነሳ፣ በአካባቢ እና በአየር ንብረት ለውጥ አደጋዎችን ማቃለል እና ማስተዳደር እና ሌሎችም ድጋፏን ትቀጥላለች።

**ጥያቄ፡- ኢትዮጵያ የአፍሪካ የፋርማ ሲዩቲካል ማምረቻ ማዕከል ለመሆን እየሰራች ነው። የህንድ ኩባንያዎችን ተሳትፎ እንዴት ያዩታል?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** አራት የህንድ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ በማምረት ላይ ይገኛሉ፣ ነገር ግን በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ ነበር። ነገር ግን ይህ ሁኔታ ከተረጋጋ እነዚህ ኩባንያዎች በሙሉ አቅማቸው መሥራት የሚጀምሩ ይመስለኛል። የክትባት ማምረቻው ኢትዮጵያ የህንድ ባለሙያዎችን የምትጠቀምበት እና ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ክትባቶች የምታመርትበት ዘርፍ ነው። የአቅርቦት ሰንሰለት ለውጥ እና በአፍሪካ አህጉር ውስጥ ያለው የምርት አቅም ጥሩ ይሆናል። ኢትዮጵያ ያገኘችው ጥቅም የአፍሪካ ህብረት የበሽታ መቆጣጠሪያ ማዕከል፣ ወጣት፣ የተማረ እና የሰለጠነ ሕዝብ መኖር ነው። የመድኃኒት ዘርፍ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በዚህ ዘርፍ ህንድን ጨምሮ ለኢንቨስትመንት ምቹ መዳረሻ ለመሆን ያላትን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ በፖሊሲው እና በኢንቨስትመንት ማዕቀፍ ላይ አንዳንድ ለውጦች እንደሚያስፈልግ አምናለሁ።

**ጥያቄ፡- በህንድ እና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን ትብብር በህክምና እንዴት ያዩታል?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** በአንፃራዊነት ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላት ሀገር በመሆኗ ኢትዮጵያ መሠረታዊ የጤና መሠረተ ልማት አውታሮች አሏት ይህም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ እና ተጨማሪ መሻሻል ያስፈልገዋል። አዳዲስ ሆስፒታሎች እየመጡ እንዳሉ እና የህክምና ኮሌጆች ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ዶክተሮች እና እንክብካቤ ሰጭዎችን እያፈሩ እንዳሉ ብዙ ለውጦችን ማየት እንችላለን። ኢትዮጵያም የአህጉሪቱ ምርጥ የህክምና ኮሌጆች ባለቤት ነች። የጤናው ዘርፍ ትብብርን በተመለከተ የህንድ የህክምና ባለሙያዎች በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ በመሄድ የህክምና ተልዕኮዎችን ያደርጋሉ። በቅርቡ የቻንዲጋርህ የሮተሪ ክለብ ለ12 ቀናት የህክምና ሚሽን ያከናወነ ሲሆን ከ150 በላይ ውስብስብ ቀዶ ጥገናዎችን እና ከ500 በላይ ህሙማንን የበጎ አድራጎት አካል በማድረግ የኦፒዲ አገልግሎት ሰጥተዋል። መሰል ተግባራት ለታካሚዎች ቀጥተኛ እፎይታ ለመስጠት እና የኢትዮጵያን የህክምና ባለሙያዎችን ክህሎት ለማሳደግ በግል አካላትም ይከናወናሉ።

**ጥያቄ፤- የጤና ሴክተር ትብብርን ለማሳደግ የህንድ ኤምባሲ ያከናወናቸው ተግባራት ምን ምን ናቸው?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡ -** በህንድ የጂ20 ፕሬዚዳንትነት ጊዜ የህንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ‹‹ለአንድ ምድር፣ አንድ ጤና›› እና በኋላ ላይ "ከድንበር ባሻገር የጤና እንክብካቤ" ጽንሰ-ሃሳብ አስተዋውቋል፡ ፡ ይህም ከጤና ጋር የተዛመዱ ፍላጎቶችን ጥራት እና አቅምን እያረጋገጠ ዓለም አቀፍ ሥነ-ምህዳርን ለማጠናከር ራዕይ ያለው ነው። እና ከፍተኛ ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ለሁሉም የሚል ምርህን የሚከተል ነው። እነዚህ ጽንሰ-ሃሳቦች ከጤና ጋር የተያያዙ ከአፍሪካ ህብረት አጀንዳ 2063 እና የተባበሩት መንግሥታት አጀንዳ 2030 ዓላማዎች ጋር የተጣጣሙ ናቸው።

ከላይ የተገለጹትን ከጤና ጋር የተያያዙ ጽንሰ ሃሳቦችን የበለጠ ለማጠናከር የህንድ ኤምባሲ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በአንድ መድረክ ላይ በማሰባሰብ ሃሳባቸውን እንዲያካፍሉ እና ቅንጅትን ለመፍጠር ለመሥራት የሚያስችል ዝግጅት ጥቅምት 1 ቀን 2024 በአዲስ አበባ እያዘጋጀ ይገኛል። ተሳታፊዎቹ ፖሊሲ አውጪዎች፣ ሆስፒታሎች፣ የባሕል ህክምና ባለሙያዎችን ጨምሮ የህክምና ባለሙያዎች፣ የህክምና ጉዞ ባለሙያዎች፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የሀገር አቀፍ ተወካዮች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ይገኙበታል።

**ጥያቄ፡- በህንድ ውስጥ ፖሊሲ አው ጪዎች እና የጤና ባለሙያዎች በጉዳዩ ላይ የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት እና ከህንድ ተቋማት ጋር ግንኙነት ለመፍጠር የሚሳተፉባቸው መድረኮች አሉ?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** በህንድ ውስጥ በመንግሥት እና በኢንዱስትሪ ደረጃ የተደራጁ ብዙ እንደዚህ ያሉ ዝግጅቶች አሉ። መጪው ክስተት 'Advantage Healthcare India 2024' በታላቁ ኖይዳ ከዲሴምበር 18 እስከ 20 ቀን 2024 የዴሊ ብሔራዊ ዋና ከተማ አካል በሆነው በታላቁ ኖይዳ የታቀደ ነው። ከህንድ ንግድ እና ኢንዱስትሪ ምክር ቤቶች ፌዴሬሽን (FICCI) ጋር በመተባበር ከዓለም ዙሪያ የተውጣጡ የጤና ባለሙያዎች በዚህ ዝግጅት ላይ ይሳተፋሉ፡፡ እናም የህንድን ዓለም አቀፍ ደረጃ የጤና እንክብካቤ እና ደህንነት አገልግሎቶችን ይመሰክራሉ። ይህ በህንድ የተቀበሉትን የጥራት ደረጃዎች፣ የጤና አጠባበቅ ቴክኖሎጂዎች እና አጠቃላይ የጤና እና ደህንነት አቀራረብን እንዲገነዘቡ እድል ይሰጣቸዋል። ይህ ለኢንዱስትሪ እና ለኢንዱስትሪ ትስስር ትልቅ እድል ይሰጣል። ከኢትዮጵያ ጤና ዘርፍ የተውጣጡ ፖሊሲ አውጭዎች፣ የመንግሥት እና የግል ዘርፍ ከፍተኛ የጤና ተቋማት ኃላፊዎች፣ የህክምና ኢንሹራንስ ኩባንያዎች እና የመገናኛ ብዙኃን ተሳትፎን ሙሉ በሙሉ ስፖንሰር ለማድረግ አቅደናል።

**ጥያቄ፡- ህንዳውያን በዓለም ዙሪያ ከፍተኛ የጤና ባለሙያዎች እና ተንከባካቢዎች እንደሆኑ በሰፊው ይታወቃል። በዓለም ዙሪያ የህንድ የጤና ባለሙያዎች እንደዚህ ያለ ታላቅ ስም ያተረፈበት ምክንያት ምንድን ነው?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** የሕክምና ትምህርት ሥርዓት ከመጀመሪያዎቹ ቀናት ጀምሮ በዓለም ላይ ካሉት ምርጥ ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ነው። በህንድ ውስጥ ካሉት በሽታዎች ከፍተኛ ጫና አንጻር የሕክምና ተማሪዎቹ እና የጤና ባለሙያዎች ከበሽተኞች ጋር ለመገናኘት የተሻሉ እድሎችን ያገኛሉ።

ይህ ልዩ ተሰጥኦ ለህንድ ዶክተሮች እና የጤና ባለሙያዎች በዓለም ዙሪያ ባሉ ምርጥ እና ትላልቅ ሆስፒታሎች እና የጤና ሥነ-ምህዳሮች ውስጥ እንዲሰሩ እድሎችን ሰጥቷል። በዚህ ምክንያት የህንድ ዶክተሮች እና የጤና ባለሙያዎች እንደ ዩኤስኤ፣ ዩኬ፣ ካናዳ፣ አውስትራሊያ፣ ሲንጋፖር፣ የአውሮፓ ሀገራት እና የባህረ ሰላጤ ሀገራት እና ሌሎችም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ የሕንድ ዶክተሮች እና የጤና ባለሙያዎችም እንደ የተባበሩት መንግሥታት፣ የዓለም ጤና ድርጅት፣ ዩኒሴፍ፣ የዓለም ባንክ፣ ድንበር የለሽ ዶክተሮች (የድንበር የለሽ ሐኪሞች)፣ ቢል እና ሜሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን፣ ዓለም አቀፍ የህክምና ጓድ፣ ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ ማህበራት ባሉ ድርጅቶች ውስጥ በጣም የተከበሩ እና የተወከሉ ናቸው።

**ጥያቄ፡- የህንድ ጤና ዘርፍ እንዲነ ቃቃ ያደረጉ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** በድህረ-ኮቪድ ዘመን፣ ልክ እንደ ህንድ መንግሥት ሁሉ ግለሰቦችም ለጤና ያላቸው ንቃት ጨምሯል። ይህ በህንድ ውስጥ ያለውን ፍላጎት እና ወጪ ቆጣቢ እና ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የጤና አጠባበቅ ተቋማት አቅርቦትን በከፍተኛ ሁኔታ ገፋፍቶታል። ከፍተኛ መጠን ያለው ኢንቨስትመንቱ የተገኘው ከውጭ ባለሀብቶች እንዲሁም ከግሉ ሴክተር ነው። በቅድመ ወረርሽኙ ዘመን እንኳን ህንድ ለውጭ ሀገር ታካሚዎች ተመራጭ መድረሻ ነበረች ምክንያቱም እንደ፡-

1. ግለሰቦች በዝቅተኛ ወጪ ደረጃ-1 የህክምና አገልግሎት፣ ቴራፒ፣ የቀዶ ጥገና ህክምና ወዘተ ጥቅም ያገኛሉ።

2. ታካሚዎች በፍጥነት ማገገም እንዲችሉ ባሕላዊ የጤና እና በጎነት እውቀቶች ጥምረት መኖሩ

3. ህክምናዎቻቸውን ከመዝናኛ እንቅ ስቃሴዎች ጋር በማጣመር የህንድ ማራኪ ውበት፣ የበለፀገ የባሕል ቅርስ እና የተለያዩ መልክዓ ምድሮች ማጣጣም ይችላሉ።

በአሜሪካን ሜዲካል ማኅበር ባደረገው የወጪ ንጽጽር ጥናት መሠረት፣ የጉልበት ምትክ ቀዶ ሕክምና በዩናይትድ ስቴትስ 40,000 የአሜሪካ ዶላር፣ በታይላንድ 10,000 ዩኤስ ዶላር እና በሲንጋፖር 13,000 ዶላር ያስወጣል። ነገር ግን፣ ተመሳሳይ ቀዶ ጥገና፣ በተሻለ የህክምና እንክብካቤ እና አገልግሎት፣ በህንድ 6,500 የአሜሪካ ዶላር አካባቢ ማግኘት ይቻላል። በህንድ ውስጥ ያለው የኑሮ ውድነትም በጣም ተመጣጣኝ ነው፡፡ ይህም ለረጅም ጊዜ ህክምና ለሚወስዱ ታካሚዎች ወጪ እንዳይከብዳቸው ያደርጋል፡፡ ከሁሉም የዓለም ክፍሎች ወደ ህንድ ዘመናዊ ከተሞች የተሻለ ግንኙነት ለህንድ የህክምና እሴት ጉዞ እድገትም አስተዋጽኦ እያደረገ ነው።

**ጥያቄ፡- በኦክቶበር 01 ቀን 2024 በህንድ ኤምባሲ የተዘጋጀው የኮንፈረንስ ዋና ይዘቶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** ጉባኤው የጤና አጠባበቅ ጉዳዮችን ለመጋራት ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በአንድ መድረክ ላይ ለማምጣት ያለመ ነው። ከኢትዮጵያ መንግሥት ተወካዮች፣ ከአፍሪካ ህብረት፣ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እና በአዲስ አበባ የሚገኙ የተለያዩ ድርጅቶቹ፣ በኢትዮጵያ እና ህንድ የመንግሥት እና የግል ጤና ዘርፍ፣ የፋርማሲ እና የህክምና መሳሪያዎች አምራቾች እንዲሁም የጤና ባለሙያዎችን ለመጋበዝ አቅደናል። ከሁለቱም ሀገሮች በዚህ ኮንፈረንስ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅት በመፍጠር ገንቢ በሆነ መልኩ ለመሰማራት ፍኖተ ካርታ በማዘጋጀት ሁሉም ተጠቃሚ እንዲሆን እንፈልጋለን።

**ጥያቄ፡- በጉባኤው ውስጥ ሰዎች እንዴት መሳተፍ ይችላሉ?**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** ውይይቱና ምክክሩ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራና ውጤቱን ያማከለ እንዲሆን ጥሪውን መሠረት በማድረግ ተሳትፎው እንዲቀጥል ተወስኗል። ተሳታፊዎች ዝርዝራቸውን ለጉባኤው በተዘጋጀ የኦንላይን የምዝገባ ፎርም ሊያቀርቡ ይችላሉ (www.eoiaddisababa.gov.in) ምዝገባው እስከ መስከረም 25/2024 (እኤአ) ክፍት ነው። መሳተፍ የሚፈልጉ ድርጅች እና ግለሰቦች ዝርዝር መረጃቸውን በሚከተለው ቅጽ መሙላትና ማመልከት ይችላሉ https://forms.gle/Qf8Lo3KWCxZpCSPx7 ኮንፈረንሱ በህንድ እና በኢትዮጵያ መካከል በጤናው ዘርፍ ለትብብር አዲስ ፍላጎት እንደሚፈጥር እና ለዓለም አቀፍ ተሳታፊዎች ግንዛቤን ይሰጣል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

**ለቃለ መጠይቁ ስለተባበሩን እናመሰግናለን!**

**ሚስተር አኒል ኩማር ራይ፡-** እኔም አመሰግናለሁ

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የማክሮ-ኢኮኖሚ ማሻሻያውና የኢንዱስትሪ ፓርኮች ተወዳዳሪነት

**አንተነህ ቸሬ**

ከ2010 ዓ.ም ሀገራዊ ለውጥ ወዲህ፣ ባለፉት አምስት ዓመታት፣ መንግሥት ለሀገሪቱ መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ለመፈለግ ያስችላሉ ያላቸውን ዘርፈ ብዙ የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ መርሃ ግብሮችን ተግባራዊ ማድረጉ ይታወቃል፡፡ ከእነዚህ መርሃ ግብሮች አንዱ፣ ሀገር በቀል የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ መርሃ ግብር (Homegrown Economic Reform Program) ነው። የመርሃ ግብሩ ዓላማ አምራች የሆነውን የሰው ኃይል የሚሸከም የሥራ እድል እና የተረጋጋ የማክሮ-ኢኮኖሚ ከባቢ በመፍጠር እንዲሁም የግል ዘርፍ መር (Private Sector-Led) የሆነ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በመገንባት ዘላቂና ፈጣን የምጣኔ ሀብት እድገት ማስመዝገብ ነው፡፡

የኢንቨስትመንት አዋጅና የንግድ ሕግ ማሻሻያዎች፣ ብሔራዊ የንግድና ቢዝነስ ሥራ አመቺነት ማሻሻያ መርሃ ግብር (National Ease of Doing Business Initiative) እንዲሁም ከዓለም አቀፍ የግብይት ሥርዓት ጋር ዘመናዊ ትስስር ለመፍጠር የፋይናንስ ዘርፉ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት እንዲሆን የተላለፈውን ውሳኔ ለመተግበር እየተደረጉ ያሉ ዝግጅቶች የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ መርሃ ግብሩ አካል ናቸው፡፡

በ2011 የበጀት ዓመት ወደ ትግበራ የገባው የመጀመሪያው ምዕራፍ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም፣ ብዙ የፖሊሲ ሃሳቦችን በውስጡ ያካተተ እና መጠነ ሰፊ የኢኮኖሚ ዓላማዎችንና ግቦችን ያሳካ ነበር። ቀሪ ሥራዎች ቢኖሩም፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ሚዛን መዛባትን ለማረም፣ የዕዳ ጫናን ለማቃለል፣ የሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለማሳደግ፣ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮችን ለማስፋፋት፣ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር እና መዋቅራዊ ማነቆዎችን ለማረም በተደረገው ጥረት ውጤቶች መገኘታቸውን መንግሥት ገልጿል። በቅርቡ የጸደቀው ሁለተኛው ምዕራፍ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ቀሪ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ ግብዓት እንደሚሆን ታምኖበታል።

እነዚህ የፖሊሲና የሕግጋት ማሻሻያዎች እና ሕጋዊ ማዕቀፎቹን መሰረት በማድረግም የተወሰዱ ተግባራዊ ርምጃዎች ኢኮኖሚው ወደተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ እንዲሸጋገር አዲስ ተስፋ ፈንጥቀዋል፡፡ በዚህም መሰረት ኢትዮጵያ በቅርቡ ወደተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብር ትግበራ ገብታለች፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብሩ በአራት ምሰሶዎች ላይ የተገነባ ነው፡፡ እነዚህም ምሰሶዎች የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን እና ዘላቂነትን የሚደግፍ ዘመናዊ እና ጤናማ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማዕቀፍ መመሥረት፤ ፈጠራን የሚያበረታታ ምቹ የኢንቨስትመንትና የንግድ ዘርፍ ከባቢ እና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፣ የሀገር ውስጥ ምርትና ምርታማነት አቅምን ማጠናከር እና ጥራት ያለው አገልግሎትን በብቃት ለማቅረብ የመንግሥትን አቅም ማሳደግ ናቸው።

በመንግሥት ይፋ የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ማብራሪያ እንደሚያሳየው፣ የፕሮግራሙ ዋና ዋና ቁልፍ ዓላማዎችና ግቦች የውጭ ምንዛሪ መዛባትን ማስተካከል እና የረጅም ጊዜ የውጭ ክፍያ ሚዛን ጉድለት ችግሮችን መፍታት፤ የገንዘብ ፖሊሲ ማዕቀፉን በማዘመን የዋጋ ንረትን መቀነስ፤ የዕዳ ተጋላጭነትን በመፍታት እና የሀገር ውስጥ ገቢን በማሳደግ ሀገራዊ የልማት ፍላጎቶቻችንን በሀገር ውስጥ አቅም ለማሳካት ምቹ መደላድል መፍጠር፤ የፋይናንስ ዘርፉን አካታችነት፣ ተወዳዳሪነትና ጤናማነት ማጠናከር እንዲሁም የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል፣ የአየር ንብረት ለውጥን በመቋቋም እና የምግብ ሉዓላዊነትን በማረጋገጥ ጠንካራ፣ አካታች እና ዘላቂ የኢኮኖሚ ሥርዓትን መገንባት ናቸው።

ማሻሻያው ለጠንካራ፣ በግሉ ዘርፍ ለሚመራ፣ ሁሉን አቀፍ ለሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት እና የሥራ ዕድል ፈጠራ መሠረት እንዲሆን ታቅዷል፡፡ ፕሮግራሙ በሚተገበርበት ወቅት ከፍተኛ እና የተረጋጋ የኢኮኖሚ ዕድገት እና ባለ ነጠላ አሃዝ የዋጋ ግሽበት ይኖራል ተብሎ ግብ ተጥሏል። ከዚህ በተጨማሪም የማሻሻያው ትግበራ የውጭ ምንዛሪ መዛባትን በማስተካከል፣ የፋይናንስ ዘርፉን ይበልጥ በማጠናከር፣ የዋጋ ንረትን በመቆጣጠር፣ የታክስ ገቢን በማሳደግ፣ የመንግሥትን ኢንቨስትመንት ውጤታማነት በማሻሻል፣ የባንክ ዘርፍን ተወዳዳሪነትና ጤናማነት በማጎልበት እና የንግድና ኢንቨስትመንት ከባቢን በማሻሻል በዓለም አቀፍ ደረጃ ዘመናዊና ተወዳዳሪ የኢኮኖሚ ሥርዓት የመገንባትን ሀገራዊ ግብ ለማሳካት እንደሚያስችል ተገልጿል።

> **የኢኮኖሚ ማሻሻያው ለኢንዱስትሪ ልማት አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው መገመት አይከብድም፡፡ ማሻሻያው ለኢንዱስትሪው አቅም የሚሆን የውጭ ምንዛሬ ያስገኛል፡፡ ትልልቅ ኩባንያዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ እድል ይፈጥራል**

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ዋና ዋና የፖሊሲ ርምጃዎች በገበያ ላይ የተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ተመን ሥርዓት፣ የፊስካል ፖሊሲ ማሻሻያ፣ በወለድ ተመን ላይ የተመሠረተ የገንዘብ ፖሊሲ ሥርዓት፣ የልማት ፋይናንስ ዕድሎች እና የመንግሥት ዕዳ አስተዳደር ማሻሻያ ናቸው፡፡ የማሻሻያ መርሃ ግብሩ በእነዚህ የፖሊሲ ርምጃዎች አማካኝነት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን እንደሚያስገኝ ታምኖበታል፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች መካከል አንዱ ኢንቨስትመንትን ማሳደግ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ከማሻሻያ መርሃ ግብሩ ዋና ዋና የፖሊሲ ርምጃዎች መካከል አንዱ በገበያ ላይ የተመሰረተ የውጭ ምንዛሪ ተመን (Floating Exchange Rate) ሥርዓት ትግበራ ነው፡፡ ይህ የፖሊሲ ርምጃ የውጭ ኢንቨስተሮችን በመሳብ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በማሳደግ እና የሀገሪቱን የንግድ ሥርዓት ከአጎራባችና ከአቻ ሀገራት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች የኢንቨስትመንት ሥራዎች ከሚከናወኑባቸው ስፍራዎች መካከል በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳሉ፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የመሳብ፣ የሥራ እድል ፈጠራን የማስፋት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን እውን የማድረግ ዋና ዋና መሠረታዊ ተልዕኮዎች አሏቸው፡፡ የሕግ ማዕቀፎች ዝግጅትና ትግበራ ከእነዚህ ፓርኮች ውጤታማነት ጋር ቀጥተኛ ትስስር አለው፡፡ ፈጠራን የሚያበረታታ ምቹ የኢንቨስትመንትና የንግድ ዘርፍ ከባቢና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ እና የሀገር ውስጥ ምርትና ምርታማነት አቅምን ማጠናከር የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብሩ ከተገነባባቸው ምሰሶዎች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡ ስለሆነም የኢኮኖሚ ማሻሻያው የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ውጤታማነት ለማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት የሰጠ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ፍስሃ ይታገሱ (ዶ/ር)፣ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ለአምራች ዘርፉ፣ በተለይም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የተሰማሩ ባለሀብቶች ምርታማነታቸው እንዲያድግና በሀገራዊ ኢኮኖሚው ላይ ያላቸው ድርሻ እንዲጨምር የሚያስችሉ እድሎችን እንደያዘ ይገልፃሉ።

ዋና ሥራ አስፈፃሚው እንደሚሉት፣ መንግሥት ባለፉት ጥቂት ዓመታት የወሰዳቸው የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ ርምጃዎች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የተሰማሩ ባለሀብቶችን ተጠቃሚ ያደርጋሉ። ማሻሻያዎቹን በብቃት በመተግበር ተጨማሪ ኢንቨስትመንትን መሳብ እንደሚገባም ይገልፃሉ፡፡ ‹‹በቅርቡ መተግበር የጀመረው በገበያ ላይ የተመሰረተ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለተሰማሩ /ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል፡፡ የውጭ ባለሀብቶች በጅምላና ችርቻሮ ንግድ እንዲሰማሩ መፈቀዱም የውጭ ባለሀብቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ለመሳብ ተጨማሪ እድል ይፈጥራል፡፡ የካፒታል ገበያ እንዲጀመር የሚደረጉ ዝግጅቶች ከዚህ ቀደም በባንኮች ላይ ተንጠልጥሎ የነበረውን ካፒታል ለማግኘት ያስችላል›› ይላሉ፡፡

ከኢኮኖሚ ማሻሻያው ዓላማዎች አንዱ የኢንቨስትመንት ፍሰትን ማሳደግ እንደሆነ የሚጠቁሙት የብሔራዊ ባንክ ገዥው አቶ ማሞ ምህረቱ፣ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለሚገኙም ሆነ ከፓርኮች ውጭ ለሚያመርቱ አምራቾች ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ በመሆን ምርትን፣ የወጪ ንግድንና ተወዳዳሪነትን እንደሚጨምርም ያብራራሉ። ‹‹ማሻሻያው ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን ያበረታታል፤ የማምረት ሥራቸውን እንዲያስፋፉና የገበያ ድርሻቸውን እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል፡፡ በኢንዱስትሪና በፍጆታ ዕቃዎች ምርት ዘርፎች የተሠማሩ ተኪ ኢንዱስትሪዎች፣ በተለይም በአሁኑ ወቅት ‹ኢትዮጵያ ታምርት› በተሰኘው ንቅናቄ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ በርካታ ኢንዱስትሪዎች ከማሻሻያው ተጠቃሚ ይሆናሉ›› ይላሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የኢኮኖሚ ማሻሻያው የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለመቅረፍ፣ የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና ሌሎች የግሉን ዘርፍ ለመደገፍ የወጡ በርካታ የለውጥ ርምጃዎችን ለማጠናከር እንደሚረዳም አቶ ማሞ ያስረዳሉ፡፡

የፐብሊክ ፖሊሲ ጥናት ባለሙያው ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ፣ ዶ/ር ‹‹የኢኮኖሚ ማሻሻያው ለኢንዱስትሪ ልማት አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው መገመት አይከብድም፡፡ ማሻሻያው ለኢንዱስትሪው አቅም የሚሆን የውጭ ምንዛሬ ያስገኛል፡፡ ትልልቅ ኩባንያዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ እድል ይፈጥራል። እነዚህ ኩባንያዎች ትልቅ የካፒታል አቅምና ሰፊ የገበያ መዳረሻ ያላቸው በመሆናቸው ሸማቹ ተጠቃሚ ይሆናል። ኪራይ ሰብሳቢነትን መጠንቀቅ ይገባል፡፡ በዚህ ችግር ምክንያት የግሉ ዘርፍ የተሰናከለባቸው ብዙ የአፍሪካ ሀገራት አሉ፡፡ በአጠቃላይ ሰላምና መረጋጋትን ማስፈን ከተቻለ ከፍተኛ የኢንቨስትመንት እድል እየተፈጠረ ነው›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል፣ መንግሥት በወሰዳቸው ርምጃዎች የአምራች ዘርፉ ተጠቃሚነትና እድገት እየተሻሻለ ስለመምጣቱ ይገልፃሉ። እሳቸው እንደሚሉት፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በርካታ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን በማድረግ የአምራች ዘርፉን ብሎም ሀገራዊ ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ዘርፈ ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በእነዚህ ዓመታት የአምራች ዘርፉን አፈፃፀም በማሻሻል በሀገር ውስጥና በውጭ ተወዳዳሪ ለመሆን በርካታ ተግባሮች ተከናውነዋል፡፡ የፖሊሲ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፤ ቅንጅታዊ አሰራሮችና የባለድርሻ አካላት ትብብሮች እንዲጠናከሩ፣ የኃይል አቅርቦት እንዲሻሻል፣ የሎጂስቲክስ ሥርዓቱ እንዲዘምን እና ለአምራች ዘርፍ የሚቀርበው የፋይናንስ መጠን እንዲጨምር ተደርጓል።

12 በመቶ የነበረው የአምራቾች የብድር ድርሻ ወደ 24 በመቶ ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡ የዘርፉን ውጤታማነት ለማሳደግ የተከናወኑት ተግባራት ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የሆኑ የአምራች ዘርፍ ተግዳሮቶችን ለማቃለል አስተዋጽኦ ነበራቸው፤ የዘርፉ ዓመታዊ እድገት 10 ነጥብ አንድ በመቶ እንዲሆን አስችለዋል፡፡ በአጠቃላይ በሁሉም ዘርፎችና ተቋማት የተደረጉ ማሻሻያዎች በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብር ላይ የተቀመጡትን እቅዶች ለማሳካት በሚያስችል መልኩ የተከናወኑ ናቸው። የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የተሰማሩ ባለሀብቶች የውጭ ምንዛሬ እንዲያገኙ እንዲሁም የገበያ መዳረሻዎቻቸውን እንዲያሰፉ እድል እንደሚፈጥርላቸውም ሚኒስትሩ ይናገራሉ፡፡

አቶ መላኩ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ምርቶች እሴት ተጨምሮባቸው ለገበያ እንዲቀርቡ ትልቅ ሚና እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡ ‹‹በ2016 የበጀት ዓመት ወደ ውጭ ከተላከው ምርት ውስጥ 78 በመቶ የሚሆነው በጥሬ የተላከ ነው፡፡ በምርቶች ላይ እሴት ጨምሮ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ይገባል፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ በአምራች ዘርፍ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች መግባት እና ኢንዱስትሪ ፓርኮችም በሙሉ አቅማቸው ማምረት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የምጣኔ ሀብት ማሻሻያዎችን የሚጠቀም ባለሀብት ያስፈልጋል፡፡ ባለሀብት ገብቶ ካልሰራበት ፖሊሲውም ሆነ መሠረተ ልማቱ ብቻውን ለውጥ አያመጣም፡፡ በተለይ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የተለየ ኃላፊነት አለባቸው›› ሲሉ አመልክተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር (ዶ/ር) ዐቢይ አሕመድ ማሻሻያውን በተመለከተ ሲያብራሩ ‹‹በቅርቡ የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የግሉ ዘርፍ በብዛት ኢትዮጵያ ውስጥ በኢንቨስትመንት ላይ እንዲሰማራ በር ይከፍታል። የምንዛሬ ገበያው እንዲስተካከል እያደረገ እንዲሁም ብዙ ሕገ ወጥ ሥራዎችን ወደ ሕጋዊነት እያመጣ ነው። በዶላርና በብር መካከል ያለውን ያልተገባ ዝምድና ለማረቅ ያግዛል›› ሲሉ ገልጸው ነበር፡፡

‹‹ኤክስፖርት በማድረግ፣ ገቢን በማስገባትና በማስፋት፣ አዳዲስ ኢንቨስትመንት በመሳብ፣ ከውጭ የሚላክ ገንዘብ (ሬሚታንስ) በሕጋዊ መንገድ እንዲመጣ በማድረግ ኢኮኖሚያችንን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያነቃቃ ይጠበቃል፡፡ በግሉ ዘርፍ ከፍተኛ መነቃቃት እየታየ ነው›› በማለት ተናግረዋል፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ጨምሮ በሌሎች መስኮች ላሉ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴዎች በርካታ ፋይዳዎች ያሉት ትልቅ ርምጃ ነው፡፡ የማሻሻያ ፕሮግራሙን በብቃት እና በውጤታማነት ለመተግበር መንግሥት ቁልፍ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎችን ማስቀመጡን ገልጿል። እነዚህ አቅጣጫዎች በላቀ አፈፃፀም እንዲተገበሩ ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥና በሌሎች መስኮች ያሉ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴዎች ለሚያጋጥሟቸው መሰናክሎች ዘላቂ መፍትሔ ማበጀት ይገባል፡፡

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ጎሜ

# ባጎረሰ የተነከሰ እጅ

**አሲሴሮ**

ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ላይ ነግሳ በቆየችባቸው ወቅቶች የበርካታ ወደቦች ባለቤት ነበረች፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በዋነኝነት አዶሊስ፣ ምጽዋ፣ አሰብ፣ ዘይላ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ዘይላ ሶማሊያ እንደ ሀገር ከመፈጠሯ በፊት ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት የባህር በር የነበረና ከዛግዌ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያ በወደቡ ስትጠቀም ኖራለች፡፡

አሰብ፣ ምጽዋ እና አዶሊስ የኢትዮጵያ በብቸኝነት ስትጠቀምባቸው የነበሩና ኤርትራ ስትገነጠል አብረው የሄዱ ናቸው፡፡ በተለይም አሰብ ኢትዮጵያዊ አፋሮችን ጨምሮ ከነወደቡ ኢፍትሃዊ ባልሆነ መልኩ ተላልፈው የተሰጡ ኢትዮጵያ ሀብቶች ናቸው፡፡ ይህ ኢፍትሃዊ ውሳኔም ባለብዙ ወደቦች ባለቤት የነበረችውን ሀገር ከነጭራሹ ወደብ አልባ አድርጎ አስቀርቷታል፡፡

ይህ ደግሞ ሀገሪቱን ለበርካታ ቀውሶች ዳርጓታል። የመጀመሪያው ኢኮኖሚያዊ ጫና ነው፡፡ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ በመሆኗ በርካታ ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች አጋጥመዋታል፡፡ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት አንድ ወደብ አልባና ወደብ ያለው ሀገር በሁሉም ነገር ተመሳሳይ የሆኑ ሁለት ሀገሮች በኢኮኖሚ ዕድገታቸው ሲነጻጸሩ ወደብ አልባው ሀገር 1በመቶ በኢኮኖሚ ዕድገቱ ወደ ኋላ ይቀራል፡፡ ይህም ማለት ወደብ ያለው ሀገር ኢኮኖሚውን በእጥፍ ለማሳደግ 24 ዓመታትን ሲፈጋበት ወደብ አልባው ሀገር ኢኮኖሚውን በእጥፍ ለማሳደግ 36 ዓመታት ይፈጅበታል፡፡ በሌላም በኩል ወደብ አልባ መሆን ብቻ የአንድ ሀገር የውጭ ንግድ መጠንን ከ33 በመቶ እስከ 43 በመቶ ሊቀንሰው ይችላል፡፡ በዚህ ችግርም ኢትዮጵያ በመፈተን ላይ ትገኛለች፡፡

በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪም ሆነ የእርሻ ውጤቶች የሚመረቱት ከወደብ በራቀ አካባቢ በአብዛኛው በመሃሉና በምዕራቡ የሀገሪቱ ክፍል ስለሆነ እነዚህን ምርቶች ወደ ወደቡ ለማዝለቅ ብዙ ወጪ ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም ከባድ ዕቃ ለማምረት ለሚፈልግ ኢንቬስተር ወደብ አልባዋ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ ምርጫ ልትሆን አትችልም፡፡

በሀገር ደረጃ ከላይ የተገለጸው እንዳለ ሆኖ ወደብ አልባነት ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የቀን ተቀን ኑሮ ጋር ቁርኝት አለው፡፡ በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ለተከሰተውና በቀኑ እንደሮኬት ለሚወነጨፈው የኑሮ ውድነት አንዱ ምክንያት የወደብ አለመኖር ነው። በየጊዜው በወደብ ላይ የሚጣለው ታሪፍና ቀረጥ መናር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውንና የሚወጣውን ሸቀጥ ዋጋ እንዲንር እያደረገው ይገኛል፡፡ በአንድ ወቅት ኢትዮጵያ በምትጠቀምበት የታጁራ ወደብ ላይ በአንድ ቅጽበት እስከ 25 በመቶ የዋጋ ጭማሪ መደረጉ ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው፡፡

የኢኮኖሚ ባለሙያዎች እንደሚናገሩትም ወደብ የሌላቸው ሀገራት ዓመታዊ ዕድገታቸው በ25 በመቶ የተገታ ከመሆኑም ባሻገር ወደብ አልባ ሀገሮች ወደ ውጭ የሚልኳቸው ምርቶች በአብዛኛው በአንድና ሁለት ምርቶች ላይ ብቻ የተወሰኑ ናቸው፡፡ ስለሆነም ከድህነት የመላቀቅ እድላቸው በጣም የመነመነ ነው። የውጭ ባለሀብትም አይመርጧቸውም፡፡ በወደብ ኪራይ እና በትራንስፖርት ምልልስ ለተጨማሪ ወጪ ስለሚዳረጉም ለሸቀጦች ዋጋ መናርና ለኑሮ ውድነት የተጋለጡ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የባህር በር አለመኖር ለኢኮኖሚና ለልማት ዋነኛ ዕንቅፋት መሆኑን ሁሉም ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ከሆነች ጀምሮም በየቀኑ ለወደብ ኪራይ ከ3 ሚሊዮን ዶላር በላይ በየዓመቱም ከነጥብ 6ቢሊዮን ዶላር በላይ ታወጣለች፡፡

ሌላኛው የወደብ አልባነት ጉዳት ደግሞ ከዲፕሎማሲ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ወደብ ያላቸውና የሌላቸው ሀገራት እኩል ተደማጭነት አይኖራቸውም። ኢትዮጵያም ከቀይ ባህር ከተወገደች ጀምሮ በዓለም ላይ ያላት ተሰሚኒት እየተቀዛቀዘ

**ሶማሊያ መንግሥት አልባ ሆና ለዘመናት ቆይታለች፡፡ ኢትዮጵያ ባደረገችው ጥረት እኤአ ከ2008 ጀምሮ ሶማሊያ መንግሥት መስርታ አንጻራዊ ሰላም አግኝታ ቆይታለች። ለሶማሊያ መረጋጋትና የሶማሊያን ሕዝብ ለመታደግ ሲባልም ኢትዮጵያ በሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮቿን አጥታለች**

እንደመጣና በምትኩ ጅቡቲን የመሳሰሉ ትንንሽ ሀገሮች የበለጠ ተሰሚነትን እያገኙ መጥተዋል፡፡

ሶስተኛው ችግር ደግሞ ወደብ አልባ ሀገራት የሚገጥማቸው የሉዓላዊነት ፈተና ነው፡፡ ወደብ አልባ ሀገራት እራሳቸውን ከጠላት ለመከላከል ይቸገራሉ። የራሳቸውም ሚስጢር አይኖራቸውም፡፡ በየዓመቱ ለወደብ ከምታወጣው በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በተጨማሪ ለሀገር ስትራቴጂክ የሆኑ ዕቃዎችን ለማስገባት ስትፈልግ የግድ ወደብ የሚያከራየው ሀገር ማወቅና መፍቀድ አለበት፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ሚስጢር ነው ብላ የምትደብቀው ነገር አይኖራትም ማለት ነው፡፡ እንደ ሀገር የምትይዛቸው ሚስጦሮቿ ሁሉ በወደብ ሰጪው ሀገር ዕውቅና ውስጥ የሚያልፉ ናቸው ብለዋል፡፡

ለምሳሌ አስፈላጊ የጦር መሳሪያዎች ኢትዮጵያ ማስገባት ብትፈልግ በወደቡ ባለቤት ዕውቅና ማግኘት አለበት፡፡ በአጠቃላይ ጉዳቱ ከኢኮኖሚ እስከ ሉዓላዊነት ድረስ ነው ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል።

እንደ ኢትዮጵያ ያለች ከ120 ሚሊዮን ሕዝብ እና በየጊዜው እየደገ የመጣ ኢኮኖሚ ያላት ሀገር እነዚህን ሁሉ ችግሮች ተሸክሞ እንደ ሀገር ለመቀጠል ትቸግራለች፡፡ ልቀጥል ብትልም አትችልም፡፡ ባለፉት 30 ዓመታት ስትኳዝበት በነበረው ሁኔታ በአንድ ወደብ ላይ ብቻ ጥገኛ ሆና መኖር ከማትችልበት ደረጃ ላይ ደርሳለች፡፡ ስለዚህም መፍትሔ መፈለጉ ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም፡፡

ስለዚህም ኢትዮጵያ ሰላማዊ አማራጮችን በመጠቀም ለሁሉም የቀጠናው ሀገሮች የባህር በር ጥያቄዋን አቅርባለች፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ሀገራት ግን በጎ ምላሽ የሰጠችው ሶማሊ ላንድ ብቻ ነች፡፡ ይህንኑ መነሻ በማድረግም የኢትዮጵያ መንግሥት ከሶማሊ ላንድ ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል፡፡ ይህንን ሁኔታ ግን የሶማሊ መንግሥት በበጎ መመልከት አልፈለገም፡፡ ወይንም ደግሞ የኢትዮጵያን ችግር ለመረዳት ፍላጎት አጥቷል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ከሆነችበት ቅጽበት ጀምሮ ለውስብስብ ችግሮች ተዳርጋለች፡፡ እነዚህ ውስብስብ ችግሮች ከዚህ በላይ ከቆዩ ከሀገሪቱ አልፈው የቀጠናው ችግሮች መሆናቸው አይቀርም፡፡ ስለዚህም ችሩ ተባብሶ ቀጠናውን ከማወኩ በፊት ሀገራቱ የኢትዮጵያን ችግር ተባብረው ሊፈቱላት ይገባ ነበር፡፡ ሆኖም በተለይ በሶማሊያ በኩል ያለው ሁኔታ ጸብ አጫሪነት የሚታይበት ነው፡፡

ሶማሊያ መንግሥት አልባ ሆና ለዘመናት ቆይታለች፡፡ ኢትዮጵያ ባደረገችው ጥረት እኤአ ከ2008 ጀምሮ ሶማሊያ መንግሥት መስርታ አንጻራዊ ሰላም አግኝታ ቆይታለች፡፡ ለሶማሊያ መረጋጋትና የሶማሊያን ሕዝብ ለመታደግ ሲባልም ኢትዮጵያ በሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮቿን አጥታለች፡፡

በፊት ‘AMISOM’ አሁን ደግሞ ‘ATMIS’ እየተባለ በሚጠራው የአፍረካ ኅብረት የሶማሊያ ሰላም ማስከበር ተልዕኮ በኩል ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ሰላም ጉልህ አስተዋጽኦ ስታደርግ ቆይታለች፡፡ በዚህ ተልዕኮም አብዛኛውን የሶማሊያ መሬት በመሸፈንና ከጥቃት በመከላከል የሶማሊያ ሕዝብ በሰላም ወጥቶ እንዲገባ፣ የሶማሊያ መንግሥትም ተረጋግቶ መንግሥታዊ ሥራዎችን እንዲያከናውን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ እንደተናገሩት 60 በመቶ የሚሆነውን የሶማሊያ ክፍል የሚጠብቀውና ከአልሻባብ ጥቃት የሚከላከለው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ነው፡፡

ኢትዮጵያ በሶማሊያ ጠንካራ መንግሥት እንዲፈጠር መስዋዕትነት ስትከፍል ቆይታለች። አልሻባብ የሁለቱም የጋራ ጠላት መሆኑ ደግሞ ሁለቱ ሀገራት በጋራ እንዲቆሙ የሚያስገድድ ነው፡፡

ሆኖም አሁን ያለው የሶማሊያ መንግሥት ይህን ሁሉ የተመለከተ አይመስልም፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ወደብና የባህር በር ለኢትዮጵያ ወሳኝ መሆኑንና የጎረቤት ሀገራትም ኢትዮጵያን እንዲተባበሯት ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢያቀርብም በግልጽ የተቀበለ ሀገር የለም፡፡

ስለዚህም በአሁኑ ወቅት 120 ሚሊዮን ሕዝብ በ2050 አካባቢ ደግሞ በዕጥፍ የሚያድግ ሕዝብ ተይዞ "ስለቀይ ባህር እና ስለ ወደብ አታንሳ፣ ዝም ብለህ ተቀመጥ" የሚል አፋኝ አመለካከት ሊኖር አይገባም፡፡ የሶማሊያ መንግሥት ኢትዮጵያ ከሶማሊ ላንድ ጋር የተፈራረመችውን የመግባቢያ ሰነድ ማክበር አሊያም ደግሞ የራሷን የባህር በርና የወደብ አማራጮች ማክበር ይገባታል፡፡ ከሁለቱ ውጭ መሆን ግን በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያውያን የሚቀበሉት አይደለም፡፡

ሶማሊያ በሺዎች ኪሎ ሜትር የሚቆጠር የባህር በር አላት፡፡ ግን ይህ ሁሉ ኪሎ ሜትር ለሶማሊያ ወደብ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል አይደለም፡፡ ስለዚህም ሶማሊያ ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለመሆን ከፈለገች ወደብ ከኢትዮጵያ ጋር ማልማት ትችላለች። ወይንም ደግሞ ለም መሬት ወስዳ በምትኩ ወደብ ልታቀርብልን ትችላለች፡፡ ብቻ አማራጩ ብዙ ነው፡፡

ዘይላ ሶማሊያ እንደ ሀገር ከመፈጠሯ በፊት ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት የባህር በር ነው፡፡ ከዛግዌ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያ በወደቡ ስትጠቀም ኖራለች፡፡ ለኢትዮጵያ ቅርበት አለው፡፡ ከሞቃዲሾ በርካታ ኪሎ ሜትሮችን የሚርቅ ስለሆነ ሶማሊያ ልትጠቀምበት አትችልም፡፡ ስለዚህም መነጋገር ከተቻለ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኘውን የዘይላን ወደብ ኢትዮጵያ ብትጠቀምበትና ሶማሊያም በምትኩ ጥቅም ብታገኝ ሁለቱም ሀገራት አሸናፊ መሆን ይችላሉ፡፡

ከዚህ በተረፈ ግን የኢትዮጵያን ፍላጎት አፍኖ አሸናፊ መሆን አይቻልም፡፡ ለሶማሊያ ሕዝብ በርካታ ውለታ ለዋለችው ኢትዮጵያ በየስፍራው እየዞሩ ስም ማጥፋትና በኢትዮጵያን ላይ ሀገራት የተሳሳተ አቋም እንዲይዙ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት የኢትዮጵያን ውለታ የዘነጋ ነው፡፡

ባለፉት 15 ዓመታት እንደታየውም የሶማሊያን ሰላምና ጸጥታ የማስከበር አቅም ያለው የኢትዮጵያ የጸጥታ ኃይል ብቻ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የጸጥታ ኃይል በሶማሊያ ተልኮ ወስዶ ከተሰማራ በኋላ አልሸባብ ክፉኛ ከመዳከሙም በላይ በአዲስ አበባ በተካሄዱ ተደጋጋሚ ውይይቶች ሶማሊያ አዲስ የሆነ መንግሥት እንድትመሰርት አስችሏታል፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረሰም የኢትዮጵያ የጸጥታ ኃይል 60 በመቶ የሚሆነውን የሶማሊያን ክፍል ከአልሻባብ ጠብቆ መንግስቷም የተሻለ መረጋጋት እንዲኖረው አስችሎ ቆይቷል፡፡

እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2008 የሶማሊያ መንግሥት ሲቋቋም ቀድማ ኤምባሲ የከፈተችና ዕውቅና የሰጠችው ኢትዮጵያ ናች፡፡ በተለያዩ ጊዜያትም በሶማሊያ ሰው ሠራሽና ተፈጥሮ አደጋዎች ሲያጋጥሙ የሶማሊያ ሕዝብን በሯን ከፍታ የምትቀበለው ኢትዮጵያ ብቻ ነች፡፡ ታዲያ ይህንን ሁሉ ውለታ ለምትውለው ኢትዮጵያ የሶማሊያ መንግሥት በተቃራኒው እየሰራ ያለው ኢትዮጵያን የማጠልሸት ዘመቻ እንቆቅልሽ ሆኖ ዘልቋል፡፡

ከምስራቅ አፍሪካ ውጭ ያሉ ሀገራት ግን ይህንን የጥላቻ ግንብ አፍርሰው በጋራ ለመልማት ጥረት ሲያደርጉ እያየን ነው፡፡ ለአብነትም ሞዛምቢክ እና ማላዊን ማየት ይቻላል፡፡

በደቡብ የአፍሪካ ክፍል የምትገኘው ሞዛምቢክ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኘውን የናካላ ወደብ፣ ወደብ አልባ ለሆነችው ጎረቤቷ ማላዊ ለማከራየት መስማማቷ ተገልጿል፡፡ ስምምነቱ ለሞዛምቢክ የወደብ ኪራይ ገቢ የሚያስገኝ ሲሆን ማላዊ ደግሞ አዲስ የእቃ ማጓጓዣ ወደብ እንድታገኝ ያስችላታል ተብሏል፡፡

የናካላ ወደብ በማላዊ፣ ዛምቢያ እና ሞዛምቢክ በጋራ እየተገነባ የሚገኝ የናካላ ልማት ኮሪደር አካል ሲሆን የፕሮጀክቱ ዋና አላማ ወደብ አልባ የሆነችውን ማላዊ ለማገዝ እና የቀጣናውን የልማት ትስስር ለማጠናከር ያለመ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## የአቴቴን ከሀገሬ

ሙሉጌታ ብርሃኑ


ሀገሬ ባሕል የወለዳት ጥበብ ናት፡፡ ሀገሬ በወግ ማዕረግ በተሸመነና በተሸሞነሞነ የጥበብ ሸንሸን አምራና ደምቃ የምትታይ የአደይ አበባ ፍካት ናት፡፡ ሀገሬ ያለ ተፈጥሮ የጥበብ እሴት ለመኖር የማይቻላት በለምለም መስክ ላይ ያረፈች እንቡጥ ፍሬ ናት፡፡ ልቧ በተፈጥሮ ፍቅር የተነደፈና በምድር ሁሉ ላይ ፍቅሯን እንደ ክረምት ዝናብ የምታረሰርስ የጥበብ ጅረት ናት። የቀስተ ደመናው መቀነቷ ከምድር እስከ ሰማይ ተዘርግቶ በቀለማት መስመር ሸንተረር እየሠራ ወደ ገነት ደጆች ያደርሳል፡፡

ሀገሬ ኢትዮጵያ የዓለምን የምስጢር ካዝና ቁልፍ ከመቀነቷ ላይ አስራ በቅኔ የተሞላች የጥበብ ፍኖት ናት፡፡ ስለ ባሕሏ፣ ስለ ወጓ፣ ስለ መልክና ስዕላዊ ውበቷ የሚነግሩን የጥንታዊ ቱውፊቶቿ ርዝራዥ ዛሬም አልፎ አልፎ ከየማህበረሰቡ ጓዳ ስር ተሸሽገው ይገኛሉ፡፡ ባሰረችው መቀነቷ፣ ባጠባችው ጡቶቿ ምልጃ ተረፉ እንጂ ገዳይ አሳዳጇማ ብዙ ነበር፡፡ የያኔው ታላቅነቷ የተገነባው ተፈጥሮን ከጥበብ፣ ጥበብን ከነብሷ ጋር አቆራኝታ ከሰማይና ምድሩ ጋር የምትገናኝበትን ያን የቀስተ ደመና መንገድና የጥበብ ድልድይ በመሥራቷ ነው፡፡ ተታለን በሞኝነት የጣልናቸው ከተፈጥሮ ግርጌና ጋራ ሲከወኑ የነበሩ ባሕላዊና ጥበባዊ ክዋኔዎቻችን የዚህ መንገድ ማሳለጫ ሰንሰለታማ መሹሊኪያዎች ነበሩ፡፡ በመንገዶቹ ላይ አሜኬላ አብቅለን ዘጋናቸውና መተላለፊያውን አሳጣናት፡፡ ያሉንን ሰምተን ከዚያ የገነት ደጃፍ ተቆራረጥን፡፡ መስሎን መቀነትን ረገጥነው፡፡ መስሎን ታላቅነታችንን ወደ ሸለቆ ወንዝ ወረወርነው፡፡ መስሎን የባዕድ አምልኮ ነው ስንል ከባዕዳን ጋር ባዕድ ሆነን ከረምን፡፡ እንደ መሰለንም... ጥበብን ፍለጋ ወደ ሰሜን ብንሄድ ደቡብ፣ ወደ ምሥራቅ ብንዞር ምዕራብ ዛሬም ርዝራዥ የጥበብ ፍሬዎችን እናገኛለን፡፡

በዛሬው የዘመን ጥበብ አምዳችን ላይ ቆመን ጥበብን ፍለጋ ጋራ ሸንተረሩን ስንማስን ከወዲህ ደግሞ ሰሞነኛ የታየን አንድ ነገር አለ፡፡ መነሻ የሆነችንን ዘንቢል አንጠልጥለን ከማሳም ከጫካም ጥንቅሽ ፍሬውን እየለቀምን በዙሪያ ገባው ለመዳከር ግድ ነው። የጥንቅሽ ፍሬው መገኛ ከዘጋቢ ፊልም ላይ ነው። ፊልሙም "አቴቴ አያና ሐዎታ" ይሰኛል። ይህንን ዘጋቢ ፊልም በተመለከተም መስከረም 4 ቀን 2017 ዓ.ም ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጥቶበታል፡፡ ጥበባት የሚወለዱበት የሀገራችን ባሕል የሚቀዳው በአራቱም አቅጣጫ ከሚገኙት ብሔር ብሔረሰቦች መካከል ነውና "አቴቴ"ም ወደ ኦሮሚያ ባሕልና ትውፊቶች ይመራናል። የኦሮሞን የባሕል ጥበባት አጉልቶ በማውጣት በሀገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍ በማድረግ የሚታወቀው ኑቢያ ፊልም ፕሮዳክሽን አሁን ደግሞ ከኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዓለም አቀፍ የእይታ አድማስ የታሰበለትን "አቴቴ አያና ሐዎታ"ን በመሥራት ዝግጅቱን አጠናቋል፡፡ በትናንትናው ዕለትም በሸራተን አዲስ ተመርቆ በሀገር ውስጥ ለመጀመሪያው ጊዜ ለእይታ በቅቷል፡፡ በቀጣይም በዓለም አቀፍ የፊልም ፌስቲቫሎች ላይ የመግባት ዕድሉን በማመቻቸት ሀገርና ባሕልን ይዞ ከፍ የማለት መሻት አለው፡፡

ጥንቱን የባሕልና ጥበባት ማህቶት ሆና ለኖረች ሀገራችን ዘጋቢ ፊልሞች አቻ የሌላቸው መስታወቶች ናቸው፡፡ የሚሠሩት አስቀድሞ በታሪክና ጥናት ወደኋላም ወደፊትም ታሽተውና በእውነት ኬሻ ላይ ተንጋለው በመሆኑ ቱባውን ነገር ከነ ሙሉ ግርማ ሞገሱ ቁልጭ አድርገው የማሳየት ኃይል ስላላቸው ከሌላው የፊልም ዓይነት ለየት ይላሉ፡፡ ፊልሞች ሀገርና ወግ ባሕል፣ ጥበብና ጥንታዊነትን አውጥቶ ለዓለም የማሳየት አቅም ቢኖራቸውም እንደ ዘጋቢ ፊልሞች በቀጥታ እንደ ወረደ ስለማይቀርቡ ከግቡ አንጻር ዘጋቢ ፊልሞች ለዚህ ተመራጭ ናቸው፡፡ ዓለም አቀፍ የምርምር ተቋማትና ምሁራንም በፍለጋቸው ውስጥ ዋቢ አድርገው ከሚነሱባቸው ነገሮች መካከል ዘጋቢ ፊልሞች ከአንበሳዎቹ መካከል ናቸው፡፡ ከማንም በላይ ለኛ ወሳኝ ቢሆንም ሠርቶ ከማሳየት አኳያ ግን ገና እሳቱም አልነደደም፡፡

እኛ ስለ እኛ ከሠራናቸው በላይ እነርሱ ስለኛ የሠሩት ይልቃል፡፡ ጓዳ ጎድጓዳውን በሚያውቀው ባለቤቱ ባለመሠራታቸው ሀፍረት ከመሆኑም በላይ የእውነታ መወላገዶችና መፋለሶች ይፈጠራሉ፡፡ በኛው የፊልም ባለሙያዎች በየአጋጣሚው ተሠርተው ለእይታ የበቁ በርካታ ዘጋቢ ፊልሞች ቢኖሩም ትኩረት ሰጥቶ በባለቤትነት የሚመራው አካል ግን የለም፡፡ በፊልም




ኢንዱስትሪው ውስጥ አንድ አካል አድርጎ ለመሥራት ጥረት ቢደረግበት ኖሮ ልንመለከት የምንችላቸው ታላላቅ ነጥቦች ቢኖሩን ነበር፡፡ ፊቱን ወደ ተደበቁትና ወደ ተሰወሩት የባሕል ምሽጎች አዙሮ ቢገባበት አይቶ የሚያሳየን ተአምር አይጠፋም ነበር፡፡ አሁን አሁን ግን ግድ ሊለው የሚገባ ይመስለኛል፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ ከተሠሩት መካከል እንኳን ወድቆ የወደቀ አንድም የለም፡፡ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ተፈላጊነታቸው ከፍ ያለ ነው፡፡ ተሠርተው ከቴሌቪዥን መስኮቶች ውስጥ ብቅ ባሉ ቁጥር ከህጻን እስከ አዋቂ በተመስጦ እንደሚመለከታቸው ከዚህ ቀደም በይፋ የቀረቡ ዘጋቢ ፊልሞች ማሳያ ናቸው፡፡ ዘጋቢ ፊልሞች የሚሠሩት ከፍ ባለ ጥናትና ምርምር እንደመሆኑ በታሪክ ውስጥ እንደ አንድ ሰነድ ይጠቀሳሉ፡፡ ስለ ጉዳዩ ጠለቅ ያለ ዕውቀት ያላቸው ግለሰቦች ደግሞ በማኅበረሰቡ ውስጥ ይገኛሉ። ያለውን ነገር ለማውጣት ይፈልጋሉ ግን ደግሞ አቅም ያጣሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሀገራቸውን ባሕል ተኮር ጥበባትን አውጥቶ የማሳየት ፍላጎት ያላቸው ባለሙያዎችም ሆኑ ባለሀብቶች በውጭና በአራቱም ማዕዘናት ይገኛሉ፡፡ ችግሩ ግን ያ ነገር ደጃቸው ድረስ ካልመጣ በስተቀር አስሶ ማግኘቱን አይታትሩበትም። እንግዲህ ሻጭና ገዢ ሳይገናኙ...የሚባለው ለዚህ ዓይነቱ ነው፡፡

አሁን ለእይታ የደረሰው "አቴቴ" ዘጋቢ ፊልም ታሪክና መነሻውን መሠረት አድርጎ የተነሳው በኦሮሚያ የገዳ ሥርዓት ውስጥ በሚገኘው የስንቄ ባሕል ቢሆንም ቅሉ የመላው ኢትዮጵያ አንደኛው ትውፊት ነው፡፡ እንደ ኦሮሞ ማኅበረሰብ ቢሠራም ዓለም የሚመለከተው ግን እንደ ኢትዮጵያ ነው፡፡ አቴቴ ማለት በኦሮሞ አልፎም በኢትዮጵያ የባሕል ጥበብ የተወለደችና የወለደች እናት ናት፡፡ ስንቄ ከገዳ ባሕልና ወግ ለእናት የተበረከተና የትውልድ ስንቅ የሆነ ዘንግ ነው፡፡ ስንቄ የሰላም ጦር ነው፡፡ ስንቄን የያዘች እናትም እውነተኛ የሰላም አምባሳደር ናት፡፡ መቼቱን በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በሚገኝ የተፈጥሮና ጥንታዊ የባሕል ክዋኔ ላይ በማድረግ በዋናነትም የአቴቴን ወይንም የስንቄን ሥርዓት ያንጸባርቃል፡፡ በገዳ ውስጥ አቴቴ፣ በአቴቴ እጅ ደግሞ ስንቄ አለ፡፡ አቴቴ የመጀመሪያው ባለ ስንቄ ለመሆን የበቃች እናት ናት፡፡ ይህቺ እናትም ያንን ዘንግ ከትውልድ ትውልድ ለሴት ልጇ ስታወርስ ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡ "ስንቄ" ልዩ በሆነ ማንነት ባሕልን ከሥነ ጥበባዊ ትውፊት ጋር አቆራኝቶ የያዘ በትር ነው፡፡

ስንቄ ሁልጊዜም ቀጥ ያለና ቀጭን ነው፡፡ እንዲህ ለመሆኑ የራሱ የሆነ ምክንያትም አለው፡፡ ቀጥ ማለቱ ቀጥተኛዋን እውነትን የሚያመለክት ሥነ ጥበባዊ ውበት ነው፡፡ እውነት ብትቀጥንም አትበጠስምና መቅጠኑም ለዚሁ ነው፡፡ ስንቄ ከእንጨት የተሠራ ቀጭን በትር ብቻ አይደለም፡፡ በባሕልና ሥነ ጥበብ፣ በእደ ጥበብና የታሪክ ቀለማት አሸብርቆ ውበት የፈሰሰበትም ነው፡፡ "አቴቴ አያና ሐዎታ" መሠረት ያደረገው በገዳ ሥርዓት ውስጥ ያለውን የእናቶችን ብሎም የሴቶችን ሚናና ከፍተኛ የሆነ ተፈጥሯዊ የስልጣን ኃይል እንዳላቸው የሚያሳይም ጭምር ነው፡፡ ፊልሙን ሠርቶ ለማጠናቀቅ ሁለት ዓመታትን የፈጀ ሲሆን 4 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጎበታል። በሮብሰን ዋቤ ዳይሬክት ተደርጎ በተሰናዳው በዚህ ዘጋቢ ፊልም ሌሎች እውቅ የፊልም ባለሙያዎችም ዐሻራቸውን አኑረውበታል፡፡ ከመቶ በላይ የሆኑ ሰዎች ተሳትፈውበታል፡፡ በቅድመ ዝግጅቱም ሆነ በፊልሙ ውስጥ በዋናነት የታሪክ ባለቤት የሆኑትን የስንቄ እናቶችን አስቀድሟል፡፡ ዘጋቢ ፊልም እንደመሆኑ ታሪካዊው ታሪክ እንዳይፋለስ እውቅ የታሪክና ጥናት ተመራማሪዎች፣ የአባገዳ አባቶችንና ሌሎችንም ያሳተፈ ቅድመ ጥናታዊ ምርምሮች ተካሂዶበታል፡፡

የራስን ጥሎ የሰው አንጠልጥሎ... ለምን? እኛ የማይነጥፍ ባሕል አለን፡፡ ጥበብ አለን፡፡ ግን ከምናውቀው የማናውቀው፣ ከምንጠቀምበት የማንጠቀምበት ልቆ ይገኛል፡፡ እንደ ሀገራችን የኪነ ጥበብም ሆነ ሥነ ጥበብ ታሪክ ማሸቆልቆል የፈጠነው ባሕላዊ ትውፊቶቻችንን ቸል ማለት ስናበዛ ነው፡፡ የኛ ጥበባት ያለ ባሕላዊ ትውፊቶቻችን ህልውና የሌላቸው ባዶ ጣሳ ናቸው፡፡ አንዳችም ሳይዝ በነኩት ቁጥር ሁሉ ሲንቋቋ ይኖራል፡፡ የረገጠው ሁሉ ያጨማድደዋል። የመጣ ንፋስ ሁሉ እየገፋ ይወስደዋል፡፡ ከጥበባት ውድቀት በፊት የቀደመው የባሕል ውድቀት ነው። ባሕል በወደቀበት ቅጽበት ጥበባት ይሰበራሉ፡፡ ዛሬም ድረስ በውል ያላጤነው ነገር ይኼው ነው። ለምንድነው ኪነ ጥበባት የቀዘቀዙት? ... ሥነ ጥበባትስ ለምን ተዳከሙ? የምንል አብዛኛዎቻችን ስለ ባሕልና ወጎቻችን አናነሳም፡፡ የችግሩን ህብለ ሠረሰር ስላልጨበጥነው ምላሽና መፍትሔውም እንቆቅልሽ ሆኖ ይቀጥላል፡፡

በባዕድ አምልኮ ስም መርገው እንዲያስጠላን ካደረጉን በኋላ ባዕዳን ለራሳቸው ወስደው ዛሬ የሚዘንጡባቸው በርካታ ትውፊታዊ ጥበባት እነርሱ ጋር አለን፡፡ ነገሩ "ሊበሏት የፈለጓትን አሞራ ጅግራ ናት ይሏታል" እንደሚባለው ነው፡፡ ምራቅ የዋጡባቸውን ነገሮች በሙሉ እንዴት አስቀያሚና ጸያፍ እንደሆኑ ነግረውናል፡፡ አምነን በራቅናቸው ቁጥር አብደን እንደ ጨርቅ ጥለናቸዋል፡፡ የተቀሩትም በጥቂቶች እምቢታ ተርፈው ለዚህ በቁ እንጂ ዛሬ ላይ የምናወራለት ምንም ባሕል፣ ምንም ጥበብ አይኖረንም ነበር፡፡ "አፍንጫ ሲመታ ዓይን ያለቅሳል" ነውና ባሕል ሲነካ ጥበብ መጮህ አለባት፡፡ አለበለዚያ ለአንደኛው የመጣው ደራሽ ጎርፍ ሁሉንም ጠራርጎ ይሄዳል፡፡ ባሕልና ጥበብ ሥጋና ደም አንድ ናቸው፡፡ የሰው ልጅ ሰው ሆኖ የሚቆመው በሥጋና ደሙ ነው፡፡ ሀገር ለመቆም የምትችለው በባሕልና ጥበብ ነው፡፡ ባሕል ሲነካ ጥበብ ትደማለች፡፡ ጥበብ ስትደማ ባሕል ትቆስላለች። በመጨረሻም በሁለቱ የቆመች ሀገር ወደፊት በግንባር ተላትማ ትዘረራለች፡፡

አቴቴ አምልኮ ወይንስ የባሕል ጥበብ? የአንዳንዱ አንዳንድ ነገር... የተሳሳተ ሀዲድ፣ የተሳሳተ ባቡር ነው። በዚህ መስመሩን ጥሶ ባለፈ ባቡር እየተሳፈሩ፤ የአቴቴ ባሕልና ሥርዓት ሃይማኖታዊ የባዕድ አምልኮት ነው ሲሉ በእሾህ ላይ ተደግፈው ሸንጥ ይገትራሉ፡፡ ይህን ለማስረዳት ሌላ የተለየ ምንም ሳያስፈልግ ይህን ማየት ብቻ በቂ ነው...በገዳ ሥርዓትም ሆነ በስንቄ ውስጥ የሚገኙት ሁሉ የየራሳቸው ሃይማኖት ያላቸው ናቸው። ሙስሊም፣ ክርስቲያን እንዲሁም ዋቄዎችም አሉበት። ወደኋላ መለስ ለማለት ከቻልን አሉባልታው የኛ አይደለም፡፡ ስንቱን በእጅ የያዝነውን ወርቅ እንደ ህጻን እያሞኙ አስጥለውን ዛሬ እዬዬ! ከምንልላቸው ስለምንስ አንማርም? ትናንት ለዛሬ መማሪያ ካልሆነ የትናንት መኖርስ ጥቅሙ ከምኑ ላይ ነው? ይሁንና በአቴቴ የባሕል ሥርዓት ውስጥ ያለው በእናት ወግ የተከሸነ ተፈጥሮ አዘል የባሕል ጥበብ ነው፡፡ ከክረምት ወራት የተፈጥሮ መስተጋብር ጋር የተቆራኘም ነው። እናትነትና የክረምት ተፈጥሮ ሁለቱም አንድ የሚያደርጋቸው ልዩ መስተጋብር አላቸው፡፡ ይሄ ዝናባማ ወቅት ከእናትነት ብሎም ከሴትነት ጋር ያለው ልዩ መስተጋብር በጥበብ አዘል ሴትነት በክረምቱ ወራት ሲገለጥ ያስተዋልን ስንቶች እንሆን...

የሀገሬ የጥበብ ወገብ በለምለም ሳርና ቅጠል መቀነቱን አስራ በአሸንዳና ሻደይ እሽክም! የምትለው ክረምት ላይ ነው፡፡ ክረምቱ ሊያልፍ ምድር በአደይ አበባ ስትንቆጠቆጥ ለመሰነባበቻው በእንቁጣጣሽ አበባየሆሽ ቀጠሮ ይዘው ይገናኛሉ፡፡ እኚህም ሌሎችም ሁሉ ከተፈጥሮ ጋር የተጋመደ የራሳቸው የሆነ ሚስጥራዊ ጥበብ አላቸው፡፡ አቴቴም ከሴትነት ተፈጥሮ ጋር በክረምት መቀነት ከታሰሩ ከእነዚህ ጥበባዊ ትውፊቶች መካከል አንደኛው ነው፡፡ የአቴቴ ሥርዓት በተፈጥሮ ውስጥ የእናትነትንና የሴትነትን ጥበብ መከወኛ እንጂ እንደ አንዳንዶች አሉባልታ ሃይማኖታዊ የባዕድ አምልኮ አለመሆኑን ራሳቸው ስንቄዎቹ ይናገራሉ፡፡ "ከባለቤቱ በላይ ያወቀ ቡዳ ነው" የሚለውን አባባል በማሰብ እውነታውን ለባለቤቱ ብቻ እንስጠው፡፡ "...ኢትዮጵያ ወደ ራሷ ባሕል ስትመለስ ሰላሟም ይመለሳልና ጥሩ ባሕል ብቅ ሲል ጭንቅላት የሚመቱትን እንቃወማለን!" ያሉትም የስንቄ እናቶችን በመወከል በፊልሙ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ የተሳተፉ አንድ እናት ነበሩ፡፡

በገዳ ሥርዓት ውስጥ የሚገኘው የአቴቴ ስንቄ ትውፊታዊ ባሕልና ተፈጥሮ መራሽ ጥበብ ነው፡፡ በተፈጥሮ መስተጋብር በሚካሄደው ባሕላዊ ሥርዓት ውስጥ አብዛኛዎቹ የሚገለጹት በትውፊታዊ ክዋኔዎች ነው፡፡ በክዋኔዎቹ ውስጥ ደግሞ ኪነ ጥበብና ሥነ ጥበብ ነብስ ዘሪ ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ሥርዓት ውስጥ እነዚህን ነገሮች እንደ ማጣፈጫ ቅመም ተነስንሰው እናገኛቸዋለን፡፡ በገዳ ውስጥ ያለው የስንቄ ባሕል ለመለመ ማለት በተዘዋዋሪ ጥበባት አደጉ ማለት ነው፡፡ ጥቂት ለማሰላሰል ከዓዳን ሀገራችን ወደ አዘቀጡ መንደርደር የጀመረችው ስንቄን የመሳሰሉትን ከተውንበት ጊዜ አንስቶ ነው፡፡ እርስ በርስ ለመበላላት ጥርስ ያበቀልነው ተፈጥሮንና ጥበብን ከባሕል ጋር አዋህደን መብላት ካቆምንበት ጊዜ ይነሳል፡፡ ምን ሁከት ተነስቶ ለያዥ ለገናገዡ፣ ለአዋቂ አዛውንቱ እዝጎ! አሻፈረኝ ቢል፤ አንዲት ስንቄን በእጇ የጨበጠች እናት ወጥታ ድምጽዋን ያሰማች እንደሆን ግን እየተርበደበደ እግሯ ስር ይደፋል፡፡ ጥበባዊ የሰላም ኃይል ያላትና ያለው ሥርዓት ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ስንቄ የሴቶች የፍትህና የነፃነት አርማ ነው፡፡ ከየትም ትምጣ፣ የትም ተወልዳ የትም ትደግ አንዲት በማኅበረሰቡ ውስጥ የምትገኝ ሴት መብቷ ተጥሶ በደል የደረሰባት እንደሆን አቴቴ ስንቄዋን ይዛ ትቆምላታለች፡፡ ዘንጓን ከፍ አድርጋ ስለ ነፃነቷ ትሟገትላታለች፡፡ "ሰላም ለሀገሬ! ሰላም ለሕዝቤ! ሰላም ለቤቴ!" ሰላም...ሰላም....ሰላም! ይሄ የስንቄዎቹ የአቴቴ ህብረ ዜማ ነው፡፡ ዘጋቢውን ተመልክተን የተዘጋውን ሌላም እንክፈት፡፡ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ባሕሏን በጥበብ ይዘን አምሯል ሸገኑ! እንበል፡፡

**እቴ ሜቴ! እቴ ሜቴ!**
**ሆኗል ይሁን ከአቴቴ፤**
**በሀገሬ ...**
**ጥበብ ሞልቷል ከእናቴ፡፡**

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## አካል ጉዳተኞች እና የመገናኛ ብዙኃን ሽፋን

ዋስልኝ አየለ

በብዙ መድረኮች ላይ እና በመገናኛ ብዙኃን ውይይቶች እንደምንሰማው አካል ጉዳተኞችን እና መገናኛ ብዙኃንን በተመለከተ በተደጋጋሚ የሚሰማው ቅሬታ በቂ ሽፋን አላገኙም የሚል ነው፡፡ ቁጥሩን በመናገርም ይህን ያህል አካል ጉዳተኛ ባለባት ሀገር የመገናኛ ብዙኃን አካል ጉዳተኛን በተመለከተ ያላቸው ፕሮግራም ግን ይህን ያህል ብቻ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ራሱ የተሳሳተ ነው፡፡

ለአካል ጉዳተኞች ሽፋን መስጠት ማለት ‹‹የአካል ጉዳተኞች›› የሚል ስያሜ ያለው ራሱን የቻለ (እነርሱን ብቻ የተመለከተ ማለት ነው) ፕሮግራም ማዘጋጀት ማለት መሆን የለበትም፡፡ ከዚህ ይልቅ መሆን ያለበት እና መበረታታት ያለበት በየትኛውም ፕሮግራም ላይ እነርሱን አካታች የሆነ ይዘት ማካተት ነው፡፡ ፕሮግራሙ የመዝናኛ ወይም የኢኮኖሚ ወይም የፖለቲካ ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲህ አይነት ፕሮግራም ላይ አካል ጉዳተኞችን ማሳተፍ ወይም እነርሱን የተመለከተ ነገር ማቅረብ ማለት ሽፋን መስጠት ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የኢኮኖሚ ጉዳይ የሚተነተንበት ፕሮግራም ላይ ከአካል ጉዳተኞችም አንፃር መተንተን ማለት ነው፡፡

አለበለዚያ ግን በሳምንት ወይም በአሥራ አምስት ቀን አንድ ጊዜ በሚካሄድ አካል ጉዳተኞችን የተመለከተ ፕሮግራም ብቻ በማዘጋጀት ሽፋን ሰጠን ማለት አይቻልም፡፡ በየትኛውም ነገር ላይ ከማንኛውም ኅብረተሰብ ጋር እኩል ማድረግ የሚቻለው በእንዲህ አይነት አሰራር እንጂ እነርሱን ብቻ የሚመለከት ፕሮግራም በማዘጋጀት አይመስለኝም፡፡

አካል ጉዳተኝነት በሆነ ዓውድ የሚታይ አንድ የኅብረተሰብ ክፍል ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ወጣቶች፣ ሴቶች፣ መምህራን፣ መሐንዲሶች፣ ጋዜጠኞች.... የሚባሉ ምድቦች አሉ፡፡ ወይም የሰሜን ኢትዮጵያ፣ የደቡብ፣ የምሥራቅ.... እየተባለ የባህል እና የአየር ንብረት ልዩነት እንደሚነገረው ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፤ በፕሮግራሞች ውስጥ ‹‹በምሥራቁ የሀገራችን ክፍል፣ በጎንደር አካባቢ፣ በሐመር ባህል....›› እየተባለ ይወራል፡፡ ልክ እንደዚህ ሁሉ የሆነ ነገር ስናብራራ ወይም ስንተነትን ‹‹ለምሳሌ ዓይነ ሥውራን፣ ለምሳሌ ድምጽ መስማት ለማይችሉ፣ ለምሳሌ የእግር ጉዳተኛ የሆኑ....›› እያልን ነገርየውን ከእነርሱ አንጻር መቃኘት ማለት ነው፡፡ እንዴት ለእነርሱ ምቹ ይሁን? እያልን መጠቆም ማለት ነው፡፡

አካል ጉዳተኝነትን ከልክ በላይ ማክበድ እና መፍራት ለአካል ጉዳተኞችም ምቾት የሚሰጥ አይሆንም፡፡ ለምሳሌ፡- የቴሌቭዥን የካሜራ ባለሙያዎች የመብራት ምጥጥን የሚያመቻቹት በሰውየው የቆዳ ቀለም ልክ ነው፡፡ ለጥቁር ሰው፣ ለቀይ ሰው... እየተባለ እንደ ሰውየው ሁኔታ ይደረጋል፡ ፡ አካል ጉዳተኝነትንም ልክ እንደዚህ ማየት ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- እግሩ ላይ ጉዳት ያለበት ሰው ደረጃ መውጣት አይችልም፤ ስለዚህ ከንፈር ከመምጠጥ ይልቅ ወይም ከልክ በላይ አዝኖ ‹‹አይዞህ!›› ከማለት ይልቅ፤ ቀለል አድርጎ ለእርሱ የሚመች ነገር ማድረግ ማለት ነው፡፡ ታዲያ ቀለል አድርጎ ሲባል ነገሩን ማቅለል ማለት አይደለም፤ እሱማ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ነው፤ ቀለል ማድረግ ማለት ለሰውየው የምናሳየውን ድርጊት ነው፡፡ ከልክ ያለፈ ከንፈር መጠጣ ልክ ያልሆነ ስሜት ይፈጥራል፡፡

ወደ መገናኛ ብዙኃን ሽፋን ስንመለስ፤ ሌላው በተደጋጋሚ አከራካሪ የሆነው እና አሁን ድረስ የጠራ መልክ ያልያዘው የቃላት አጠቃቀም ነገር ነው፡፡

በነገራችን ላይ እዚህ ላይ አንድ ልብ መባል ያለበት ነገር እነዚህ አወዛጋቢ የቃላት አጠቃቀሞች የመጡት ከክፋት አይደለም፡፡ ምናልባት አካል ጉዳተኞች ሆን ተብሎ ሊመስላቸው ይችላል፡፡ ግን ነገረየው የመጣው ከልክ ያለፈ ጥንቃቄና ጭንቀት ከማብዛት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ‹‹ዓይነ ሥውር›› የሚለው ቃል ለረጅም ዘመን አገለገለ፤ እናም ሰዎች ያለዘብን መስሏቸው፣ በተሻለ አገላለጽ የገለጽን መስሏቸው ‹‹ማየት የተሳነው›› ማለት ተጀመረ፡፡ ይህ የቃል አጠቃቀም እየቆየ ሲሄድ ነገሩን በጥልቀት ማሰብ ተጀመረ፡፡ እናም ‹‹ማየት የተሳነው›› መባል የለበትም ተባለ፡፡ ምክንያቱም ዓይነ ሥውር ማለት አካላዊ ዓይናቸው አያይም እንጂ ልበ ብርሃን ናቸው፡፡ በሥውር ያያሉ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ‹‹ዓይነ ሥውር›› የሚለው አገላለጽ ነው መሆን ያለበት ተብሏል፡፡

አሁንም ግን አንዳንድ መገናኛ ብዙኃን ላይ ‹‹ማየት የተሳናቸው›› ሲባል እንሰማለን፡፡ ይህን የቃል አጠቃቀም የሰማ አንድ ሰው ሊናደድ ይችላል፤ የሚያናድደው ግን ‹‹ዓይነ ሥውር›› የሚለው ነው መሆን ያለበት የሚለውን አለመስማታቸው እንጂ ከክፋት አይደለም፤ በእነርሱ ቤት አለዝበው መጠቀማቸው ነው፡፡

‹‹መስማት የተሳናቸው›› የሚለው ግን አሁንም በአገልግሎት ላይ ያለ ይመስለኛል፡፡ ምናልባት ‹‹ድምጽ መስማት የተሳናቸው›› ቢባል ይሻል ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ቀጥታ ድምጽ አይሰሙም እንጂ ውስጠ ብርሃን ናቸው፡፡ በነገራችን ላይ ገጠሩ ማህበረሰብ ለዚህ ድርጊት አንድ አጠቃቀም አላቸው፡ ፡ ‹‹ጆሮው ትንሽ ያዳምጣል›› ይላሉ፡፡ ‹‹ያዳምጣል›› የሚለው ቃል በጣም ገላጭ ይመስለኛል፡፡ እንደ ብዙዎቻችን የሚጮኸውን ነገር ሁሉ አይሰማም፣ በትኩረት ለእርሱ የሚሆነውን ነገር ለይቶ ነው የሚሰማ የሚል ይዘት ይኖረዋል፡፡ ጆሮው ያዳምጣል የሚሉት በከፊል የሚሰማውን ሰው ብቻ አይደለም፤ ሙሉ በሙሉ በምልክት ቋንቋ የሚግባባውንም ጭምር ነው፡፡ ‹‹ጆሮው አይሰማም›› ከማለት ይልቅ ‹‹ያዳምጣል›› በሚለው ይግባባሉ ማለት ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ግን አንድ ለስድብነት የሚያገለግል ቃል ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች ይህን ቃል ሲጠቀሙ ድምጽ መስማት የማይችሉ ሰዎችን የሚያስቀይም ይመስላቸዋል፡፡ ምናልባትም የሚቀየሙም ሊኖሩ ይችላሉ፤ ዳሩ ግን በፍጹም አይገኝም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ያንን ቃል የሚጠቀሙት የአንድን ሰው አላዋቂነት፣ መሃይምነት፣ የነገሩንን ነገር የማይሰማ መሆኑን ለመግለጽ እንጂ ድምጽ ከመስማት አለመስማት ጋር አይገናኝም፡፡ እየሰማ የማይሰማ ለማለት ነው፡፡ በምንም ነገር ቢነግሩት የማይረዳ ለማለት ነው፡፡ ምንም እንኳን የትኛውም ስድብ ነውር ቢሆንም ይህኛውን ግን ድምጽ ከማይሰሙ ሰዎች ጋር ማገናኘት ልክ አይደለም፡፡ ዋናው ይዘት ያለው ከቃሉ ሳይሆን ከተነገረበት ዓውድ ነው፡፡ ግልጽ ለማድረግ ሌላ ምሳሌ እንጠቀም፡፡

ለምሳሌ አንድ ሰው ‹‹አህያ!›› አለኝ እንበል፡፡ አህያ ታታሪ ሰራተኛ ናት፣ አህያ ብርቱ እና ጠንካራ ናት፡፡ ይህን እውነታ ይዤ ‹‹አህያ! ስላልከኝ አመሰግናለሁ!›› ብዬ ብናገር ራሴን ማሞኘት ነው፡፡ ነገሮችን በበጎ ማየቱ ጥሩ ሆኖ ሳለ፤ ‹‹አህያ!›› ብሎ የሰደበኝ ሰውዬ ግን ጥንካሬዬን እና ታታሪ ሰራተኛ መሆኔን ለመግለጽ ሳይሆን አላዋቂ ወይም መሃይም ወይም በነውር ቃል ‹‹ደደብ›› ለማለት ነው፡፡ ስለዚህ ዋናው ነገር ተሳዳቢው አካል ቃሉን የተጠቀመበት ዓውድ እንጂ ቃሉ ብቻውን አይደለም፡፡ ጆሮው ድምጽ መስማት የማይችል ሰው ምንም የሚሰደብበት ምክንያት የለም!

የመገናኛ ብዙኃን እና የአካል ጉዳተኝነትን ነገር ስናጠቃልል፤ የቃል አጠቃቀምን በተመለከተ ከአካል ጉዳተኞች ጋር መመካከርና ማህበራትን ማማከር ያስፈልጋል፡፡ አጠቃላይ ሽፋንን በተመለከተ ግን ለአካል ጉዳተኞች ሽፋን መስጠት ማለት በሳምንት አንድ ቀን የአየር ሰዓት መስጠት ሳይሆን በአጠቃላይ ይዘቶች ውስጥ ጉዳዩን አካታች ማድረግ መሆን አለበት!

# ዓለም አቀፍ

## በሊባኖስ በመገናኛ መሳሪያዎች የተፈጸመው ጥቃትና መነሾው

በጋዜጣው ሪፖርተር

በሊባኖስ "ፔጀር" የተሰኙ የመረጃ መለዋወጫ ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ፍንዳታ የዘጠኝ ሰዎችን ህይወት ቀጥፎ ከ2 ሺህ 800 በላይ ሰዎችን አቁስሏል።

"ፔጀር" በመባል የሚታወቁት በእጅ የሚያዙ የሬዲዮ የመገናኛ መሳሪያዎች በብዛት በሄዝቦላ ታጣቂዎች ዘንድ ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው። መገናኛዎቹ ሰሞኑን በተለያዩ ስፍራዎች በተመሳሳይ ሰአት በመፈንዳት በሰዎች ላይ ጉዳት አድርሰዋል፡፡

ከሟቾቹ ውስጥ ስምንቱ ተዋጊዎቹ እንደነበሩ የገለጸው ሄዝቦላህ ለፍንዳታው እስራኤልን ተጠያቂ አድርጓል።

የሊባኖስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በበርካታ የሀገሪቱ ክፍሎች የተከሰተውን ፍንዳታ "የእስራኤል የሳይበር ጥቃት" ነው ብሎታል።

እስራኤል ዝምታን ብትመርጥም የሊባኖስ የደህንነት ምንጮችን የሚጠቅሱ ዘገባዎች ግን ቴል አቪቭ ጥቃቱን ከጅምሩ እስከፍጻሜው መርታለች ብለው እንደሚያምኑ አመላክተዋል።

ሬውተርስ ያነጋገራቸው የሊባኖስ የደህንነት ባለስልጣን የእስራኤሉ የስለላ ድርጅት (ሞሳድ) የመረጃ መለዋወጫ መሳሪያዎቹ ለሊባኖሱ ሄዝቦላህ እንዲደርሰው ማድረጉን ይገልጻሉ።

5 ሺህ የሚደርሱት "AR-924" የተሰኙት መልዕክት መለዋወጫ መሳሪያዎች ወደ ሊባኖስ ከመግባታቸው ከወራት በፊትም የሚፈነዱ መሳሪያዎች ተቀብሮባቸዋል ነው ያሉት።

በተመሳሳይ ጊዜ እንዲፈነዱ ትዕዛዝ የሚሰጡ ምስጢራዊ መልዕክቶችም በመሳሪያዎቹ ውስጥ እንዲገቡ መደረጉን ያነሳሉ።

የደህንነት እና የሳይበር ጉዳዮች ተንታኞች እስራኤል የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎቹን ባትሪዎች በተመሳሳይ ሰአት እንዲግሉ አድርጎ ፍንዳታን ያስከተለ የሳይበር ጥቃት መፈጸሟን እየገለጹ ነው።

"AR-924" ምንድን ነው? አምራቹ ኩባንያስ?

የሊባኖሱ ሄዝቦላህ ተዋጊዎቹ በእስራኤል የሳይበር ጥቃት ኢላማ እንዳይሆኑ የስማርት ስልኮችን እንዳይጠቀሙ አድርጓል።

በምትኩም በድምጽ እና በጽሁፍ መልዕክት ለማስተላለፍ የሚውሉና ደህንነታቸው የተጠበቁ ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን እንዲጠቀሙ ሲያደርግ ቆይቷል።

ከነዚህ መሳሪያዎች መካከልም "AR-924" የተባሉ "ፔጀር" ተጠቃሽ ናቸው።

አነስተኛ መጠን ያላቸው የግንኙነት መሳሪያዎቹ በድጋሚ ኃይል በሚሞሉ ሊቲየም ባትሪዎች የሚሰሩ መሆናቸውንና ባትሪያቸው እስከ 85 ቀናት የመቆየት አቅም እንዳለው አምራቹ ያወጣው መረጃ ያሳያል።

ይህም እንደ ሊባኖስ ባሉ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ በስፋት በሚታይባቸው ሀገራት ተመራጭ መረጃ መለዋወጫ መሳሪያ አድርጎታል።

"ፔጀርስ" ከስልኮች በተሻለ በተለያዩ ገመድ አልባ ኔትወርኮች መስራታቸውም በዓለም አቀፍ ደረጃ በርካታ ሆስፒታሎች አሁንም ድረስ ዋነኛ መልዕክት ለመለዋወጥ ተመራጭ እንዲያደርጓቸው ምክንያት ሆኗል።

የታይዋን የኢኮኖሚ ጉዳዮች ሚኒስቴር ባወጣው መግለጫ ከነሃሴ 2022 እስከ ነሃሴ 2024 ድረስ 260 ሺህ "AR-924" ፔጀርስ ወደተለያዩ የአውሮፓና አሜሪካ ሀገራት መላካቸውን ገልጿል። ይሁን እንጂ አምራቹ "ጎልድ አፖሎ" ወደ ሊባኖስ በቀጥታ ምርቶቹን እንደላከ ነው ባወጣው መግለጫ




የጠቆመው።

በትናንትናው እለት በሊባኖስ የፈነዱት መሳሪያዎች በሃንጋሪ መዲና ቡዳፔስት የተመረቱ መሆናቸውንም ጎልድ አፖሎ ይፋ አድርጓል።

የቡዳቤስቱ "ባክ ኮንሰልቲንግ" የተባለው ኩባንያ የጎልድ አፖሎ የምርት ስያሜ ለመጠቀም ፈቃድ ቢያገኝም የሚያመርታቸው "ፔጀርስ" ዲዛይንና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች የተለዩ በመሆናቸው ኃላፊነቱን አልወስድም ብሏል የታይዋኑ ኩባንያ።

ሄዝቦላህ ለ"ፔጀር" ፍንዳታው ምን ምላሽ ሰጠ?

የሊባኖሱ ቡድን በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ያነጣጠረው የሳይበር ጥቃትና ፍንዳታን ከእስራኤል ውጭ ማንም ሊፈጽመው አይችልም ብሏል።

በሊባኖሳውያን ንጹሃን እና በተዋጊዎቹ ላይ ለተፈጸመው ጥቃት አጸፋዊ እርምጃ እንደሚወስድም በዛሬው እለት ባወጣው መግለጫ ዝቷል።

የሊባኖስ ሆስፒታሎችን አጨናንቆ ኢራን፣ ቱርክ፣ ግብጽ፣ ኢራቅና ሶሪያ ተጎጂዎችን ተቀብሎ ለማከም ዝግጁ መሆናቸውን ያሳወቁበት ከባድ ጥቃት ቡድኑ በጋዛ ለሚገኙ ፍልስጤማውያን የሚያሳየውን ተቆርቋሪነት እንደማይቀንሰውም ገልጿል።

ተንታኞች እስራኤል የሊባኖሱን ጥቃት ለባላንጣዎቿ ከወታደራዊ ባሻገር የሳይበር አቅሟ መፈርጠሙን ለማሳየት እንደተጠቀመችበት ያምናሉ።


የኢትዮጵያ ፖስታ
Ethiopost
እንኳን ለአዲሱ አመት
በሰላም አደረሳችሁ!
፳፻፲፯ 2024
በነፃ ይደውሉ
8536
www.ethio.post